<u>አስተያየትና የመፍትሄ ሀሳብ (ፕሮፖዛል)</u>

# *ይኸውና! ኤርትራ ሞተች።*
# *ትግል ለሀገር ትንሳኤ!!*

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)
ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን

ብረመን፡ ጃንዋሪ፡ 2015
(ጥር 2007)

Copyright © 2015 by Tesfatsion Medhanie
የደራሲ መብት © 2015 ተስፋጽዮን መድሃኔ

# ማብራሪያና ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ እኔ እንደ ግለሰብ በራሴ ተነሳሽነትና ፍላጎት ያዘጋጀሁት ነው። በስተጀርባዬ ሆኖ የገፋፋኝ ማንም ኃይል ወይም የፓለቲካ ድርጅት የለም። በመሆኑም፡ በጽሑፉ ላይ የሰፈረውን ይዘትም ሆነ ስርጭት በሚመለከት ኃላፊነት የምወስደው እኔ ራሴ ብቻ መሆኔን በቅድሚያ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ይህ መልእክት በስዕለ ድምጽ፡ ማለት በአውዲዮ ቪዲዮ፡ የተቀረጸ ሲሆን በጽሁፍ ደረጃም በትግርኛና በአማርኛ ይኸው ተሰራጭቷል። ይህንን ጽሑፍ መጀመርያ በትግርኛ አዘጋጅቼ ለመጨረስ፡ ሀገራዊና ህዝባዊ ፍቅር ያላቸው ኤርትራውያን ወገኖቼ በተለያየ መንገድ ድጋፋቸውን ሰጥተውኛል። አንዳንዶቹ መረጃ በማቀበል ሲሳተፉ ሌሎች ደግሞ ጽሑፉን ገና በግርድፉ እያለ ወስደው በማንበብና ጥያቄዎችን ከማቅረብ ባሻጋር ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችንም ጭምር ለግሰውልኛል። ሌሎቹም እንደዚሁ መልእክቱን በኮምፒዩተር ተጽፎ ከተጠናቀቀ በኋላ፡ ከመሰራጨቱ በፊት ወስደው በጥንቃቄ በማንበብ የፊደላት ግድፈቶችን አርሚል።

ጽሁፉ ከትግርኛ ወደ አማርኛ ሲተረጐም ስማቸውን መጥቀስ የማያስፈልገኝ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቼ በተለያዩ መንገዶች ትብብሮች አድርገውልኛል።

በዚሁ አጋጣሚም ይህንን ጽሑፍ እውን ለማድረግ ለተባበሩኝ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ በጎ አመለካከት ያላቸው ወገኖቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)

ብረመን፤ ጃንዋሪ 2015 (ጥር 2007)

***__አስተያየትና የመፍትሄ ሀሳብ (ፕሮፖዛል)__***

# *ይኸውና! ኤርትራ ሞተች።*
# *ትግል ለሀገር ትንሳኤ!!*

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)
ብረመን ዩኒቨርስቲ፣ ጀርመን፡

*በአሁኑ ጊዜ ከኤርትራ የመጣን ዜጋ "ሀገር-ቤት እንዴት ነው?" ብለህ ብትጠይቀው "ሀገርማ ሞታለች" የሚለው መልስ የተለመደ ሆኗል።*

*ለነገሩማ አብዛኛዎቻችን በሀገሪቱ ቁልጭ ብሎ ሲታይ የነበረውን እውነታ ለማመን አልፈለግንም ነበር እንጂ፡ ኤርትራማ ከሞተች ቆይታለች እኮ!! ከተወሰኑ ዓመታት በፊት፡ አንድ በቅርብ አውቀው የነበረ ጨዋ ሽማግሌ ከኤርትራ ወደ አሜሪካ ለጉብኝት ሄዶ በነበረበት ጊዜ በቴሌፎን ተገናኝተን ስናወራ፡ "ሀገር እንዴት ነው" ብዬ ስጠይቀው፡ ትንሽ ለስለስ ባሉ ቃላት "ሀገር ከስታለች" የሚል መልስ እንደሰጠኝ አስታውሳለሁ። ይሁን እንጂ፡ በመሬት ላይ የነበረው ሁኔታ ከመክሳት አልፎ የባሰ እንደነበር ጠንቅቆ የሚያውቅ ቢሆንም፡ ምናልባት እኔን ላለማሳዘን ብሎ ይመስለኛል፡ በደፈናው "ሀገር ከስታለች" ነው ያለኝ። ዛሬ ያ አንጋፋ የሀገሬ ሽማግሌ በህይወት የለም፤ አልፏል። አሁን በህይወት ቢኖርና በድጋሚ "ሀገር እንዴት ነው" ተብሎ ቢጠየቅ ኖሮ: የኤርትራ ሞት ፈጽሞ ሊደበቅ የማይችልበት ደረጃ ደርሶ ገሃድ የወጣ ጉዳይ ስለሆነ: እሱም በበኩሉ የሚሰጠው መልስ "ሀገር ከስታለች" ሳይሆን "ሀገር ሞታለች" የሚል እንደሚሆን አያጠራጥርም።*

*አዎ!! አላማችን አሁን ኤርትራ ሞተች ብለን ሙሾ ለማውረድና አንገታችንን ደፍተን ለመቆዘም አይደለም። የሁላችንም አንገብጋቢ ጉዳይና አላማ ይህች የሞተች ሀገር እንዴት ብላ ዳግም ነብስ እንደምትዘራና: ትንሳኤዋ እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል መላ መፈለግ ነው። በሌላ አነጋገር፡ የጥረታችን ራእይና አላማ የኤርትራን ትንሳኤ እውን ማድረግ ነው።*

*የኤርትራን ትንሳኤ እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል ለመገንዘብ "ኤርትራ እንዴት ለሞት ተዳረገች?" የሚለውን ቁልፍና ማነቆ ጉዳይ በቅድሚያ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። እኔም ይህ ግንዛቤ የፈጠረውን ተነሳሽነት መሰረት በማድረግ "ይኸውና!! ኤርትራ ሞተች።ትግል ለሀገር ትንሳኤ!!" በሚል ርእስ አጠር ያለና የመፍትሄ ሀሳብ (ፕሮፖዛል) ያካተተ ወቅታዊ መልእክት እነሆ አቀርባለሁ። ይችን መልእክት ሳቀርብ ገንቢ ውይይት ለመክፈት በሚል ልባዊ ምኞት መሆኑን ላሰምርበት እወዳለሁ።*

Copyright © 2015 by Tesfatsion Medhanie
የደራሲ መብት © 2015 ተስፋጽዮን መድሃኔ

***እውነት ነው! ሞት፡ እንደ ሕልፈተ-ህይወት፡ አንድ ዓይነት ክስተት ሆኖ፡ በተለያየ ሁኔታ ወይም መልክ ያጋጥማል። ሞት - በሰብአዊ ፍጡር: ወይም በእንስሳትና በአጠቃላይ ህይወት ባላቸው ፍጡራን ላይ - በእርጅና ይደርሳል፣ወይም በበሽታ ይደርሳል፣ ወይም በአደጋ ይደርሳል፣ወይም ደግሞ በግድያ ይደርሳል። የአንድ ሀገር ወይም የአንድ ሕብረተ ሰብ ሞትም እንደዚሁ ነው። የኤርትራ ሞት በእርጅና ወይም በበሽታ የመጣ አይደለም። በድንገተኛ አደጋም አይደለም። ኤርትራ የሞተችው ተገድላ ነው። ገዳዮችዋም ኢሳያስ አፍወርቂ እና ህዝባዊ ወያኔ ይባላሉ።***

***የዚሁ ጽሑፍ ዓቢይ ርእስን "ይኽውና!!" በሚል ቃል የጀመርኩት ያለ ምክንያት አይደለም። ላለፉት በርካታ ዓመታት - ለሩብ ክፍለ ዘመን ያህል ማለት ነው - የኢሳያስ አፍወርቂ ቡድን አካሄድ ኤርትራን ሊያጠፋ የሚችል መሆኑን በተደጋጋሚ ስገልጽላችሁ መቆየቴ የሚታወስ ነው። የኢሳያስ አፍወርቂ መንግስት በሚያራምደው ጸረ ሀገራዊ ፓሊሲ ምክንያት፡ ኤርትራ ወደ መፈረካከስ እንዳታመራ፣ ችግሩ በዚሁ መልክ ከቀጠለ ደግሞ ኤርትራን እንደ ሀገር ህልውናዋን የሚያከተም ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችልም የነበረኝን ጥልቅ ስጋት ሳሰማ ነበር። ሆኖም በርካታ ሰዎች ይህን አባባሌንና ሐሳቤን ስላልተቀበሉት ነገሩ መልኩን ቀይሮ፡ ወደ አላስፈላጊ ንትርክ: ምልልስና መራገም ገብተን ቆይተናል። አሁን ግን ሁላችንም - ቢያንስ አብዛኞቻችን - ኤርትራ የሞተች ሀገር መሆንዋን እየተገነዘብንና እያመንን መሆናችንን ስለተረዳሁ "በሉ! ሲፈራ የነበረው ነገር ደረሰ፣ ይኽውና" በማለት ወቀሳና ጥያቄ አዘል በሆነ መልኩ መልእክቴን ላቀርብላችሁ አግባብ ያለው ሆኖ አግኝቿለሁ።***

## ***፩፡ አንቺ የዛሬይቱ ኤርትራ!! እውነት ነጻነት ማለት ይህ ነውን?***

***የሀገራችን ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ምን ያህል አሳዛኝ: አሳፋሪና አስከፊ መሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች: መድረኮችና በተለያዩ የብዙሃን ማገናኛዎች አማካይኝነት በተደጋጋሚ የተባለለትና የተነገረለት ጉዳይ ነው። ስለሆነም በዚሁ ጽሑፍ በዝርዝር መጥቀሱ አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን የዚህ ጽሁፍ መልእክት የተሟላና የጠራ ቅርጽ እንዲኖረው፡ ወደ ዝርዝር ነጥቦች ሳልገባ የዛሬይቷን ኤርትራ የሚመለከቱ አንኳር አንኳር የሆኑት ወቅታዊ ጉዳዮችን በአጭሩ መዳሰስ ጠቃሚ መስሎ ታይቶኛል።***

1. ***የህዝባችን የኑሮ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ፡ እያሽቆለቆለና እየመረረ በመሄድ ላይ ነው። በተለመደው ተራ የዕለት ተዕለት አነጋገር፡ የህዝቡ የኑሮ ሁኔታ ከትላንት ወዲያ ይልቅ ትላንት ይብስ ነበር፤ ከትላንት ይልቅ ዛሬ ይብሳል፤ ከዛሬ ደግሞ ነገ የባሰና የከፋ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም። ህዝቡ ላለፉት 23 ያህል ዓመታት የተሞከረው*** *ሂደት የሚያሳየው ይህንኑ ነው። እንደ ምግብ: ውሃ: መብራት፡ መጠለያ: ጤናና: ሰብአዊ ደህንነት የመሳሰሉት* ***የህዝቡ ወሳኝና የሞት ሽረት የሆኑት መሰረታዊ ፍላጎቶች በሙሉ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆሉና እየተመናመኑ በመሄዳቸው ምክንያት አሁን ኤርትራ የወደቀች ሳይሆን የሞተች ሀገር ሆና ትገኛለች[1]። በአሁኑ ጊዜ በአፍሪቃ ቀንድ፡ የህዝብዋ መቃብርና ሲኦል***

1. *ማርቲን ፕላውት (ጋዜጠኛ) ስለኤርትራ ወቅታዊ ሁኔታ በጻፈው አንቀጽ በነዳጅ እጥረት ምክንያት የአስመራ ከተማ ጎዳናዎች በፈረስ-ጋሪና በእጅ-ጋሪ (ዓረብያ) ተሞልቷል" በማለት ከሀገር ውስጥ ያገኘውን*

የሆነች ሀገር ብትኖር ኤርትራ ናት። ሶማልያ እንኳን ብትሆን፡ ለሃያ ዓመታት ያህል እየታመሰች፡ ገደል አፋፍ ላይ ደርሳ የነበረችው ሀገር፡ ዛሬ ዳግም ህይወት ዘርታ: በሁለት እግርዋ ቆማ: እየተንገዳገደችም ቢሆን፡ ዳዴ ማለት ጀምራለች።

2. ከላይ በተጠቀሰው አስከፊ የኑሮ ውድነትና በሀገሪቱ የተተከለው አፋኝና ትውልድ ገዳይ ስርዓት ምክንያት ህዝቡ፡ በተለይም ወጣቱ ትውልድ - ሴቱም ሆነ ወንዱ - ከቄአቸው እየፈለሱ ወደ ሌሎች ሀገሮች እየተሰደዱ ይገኛሉ። በስልጣን ላይ ያለው የኢሳያስ መንግስትም ሆን ብሎ ኤርትራውያን ተስፋ ቆርጠው የገዛ ሀገራቸውን ለቀው ወደ ስደት እንዲፈልሱ የሚያደርግ ጎጂና አስፈሪ ዕቅድ በመተግበር ላይ ነው፤ አርምጃዎችም እየወሰደ ይገኛል። በዚህ ሁኔታ ተማርረው የተሰደዱት ለጋ ወጣቶች በማያውቁት የባዕድ ሀገር ሲገቡ የሚደርስባቸው የሚዘገንንና የሚያስደምም ግፍ: መከራና እንግልት በቃላት ለመግለጽም ይከብዳል። ሳይወዱ በግድ የወሲብ አመጽ የሚፈጸምባቸው: ተጋድመው እየታረዱ ኩላሊታቸውን የሚነጠቁ: በምድረ በዳ ሲጓዙ ውሃና ምግብ አጥተው ደርቀው የሚቀሩ: በጀልባ ታጭቀው ሲጓዙ በባህር ሰጥመው የሚቀሩ ያሉት ኤርትራውያን ወጣቶች ናቸው። የኢሳያስ መንግስት ይህ ሁሉ ሳያሳስበው ጭካኔውንና ጭቆናውን እያከረረ ነው[2]። ይህ፡ ካሁን በፊት በአንዳንድ ጽሑፎቼ እንደጠቀስኩት፡ ኢሳያስ አፈወርቂ ኤርትራን ለማጥፋትና ለመግደል ዕቅድ ይዞ የተነሳ ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ህዝብ ላይ ጥልቅ የሆነ ጥላቻ እንዳለውም የሚያሳይ ነው።

3. በአጨቋቆን ዘዴው ከፋሽሽቶች የማይለይ የኢሳያስ ስርዓት ጨካኝነቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያከረረ የሚሄድበት ያለ ምክንያት በህዝቡ እየተጠላና ህዝቡን እንደ ጦር እየፈራ በመምጣቱ ነው። ድሮውም ቢሆን ህዝባችን ከልብ ያልተቀበለው አምባገነን መሪ በአሁኑ ጊዜ ከተወሰኑ ወንጀለኞች: አድር-ባዮችና ከጥቂት የዋሆች በስተቀር ሌሎች በማንነታቸውና በሀገራቸው ከሚኰሩ ኤርትራውያን የሚጠጉት የሉም። የኢሳያስ መንግስት በህዝቡ ዘንድ ባለው ተቀባይነት በውል ሲገመገም እውነትም የወደቀ መንግስት ነው።

4. የኢሳያስ መንግስት፡ ህዝቡን በማደናገርና በማስፈራራት የይምሰል ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም፡ ዛሬ እንደ በፊቱ በታማኝነትና በተቆርቋሪነት የሚዋጋለትና የሚሞትለት ኤርትራዊ ሰራዊት የለውም። ይህንን ሁኔታ በደንብ የተገነዘበው ኢሳያስ አፍወርቂ በኤርትራዊ ሰራዊት ላይ እምነት የለውም፤ ኢሳያስ በአሁኑ ጊዜ የሚተማመንበት ኃይል የባዕድ ነው። ለምሳሌ በተለያየ ምክንያት ወደ ውጭ የሚመጡና እንዲሁም በኤርትራ ውስጥ በሕቡእ የሚንቀሳቀሱ ሀገራዊያን የፓለቲካ ተቃዋሚ የሆኑት ሰዎች እንደሚገልጹት፡ በሀገራችን የጸጥታ አስከባሪዎች ሆነው፡ በከተማዎቻችን ጎዳናዎች ላይ ተሰማርተው ነዋሪውን ህዝብ እያስቆሙ የሚፈትሹና የማንነት መታወቂያ አምጣ እያሉ አሳረ መከራውን

---

ምንጭ በመጥቀስ ገልጸዋል። MartinPlaut,(November17,2014)

2 . በተባበሩት መግንስታት የተሰየመች ሪፓርተር ባቀረበችው ዘገባ በአንድ ወር እስከ 4000 ኤርትራውያን ሀገራቸውን ጥለው ወደ ውጭ እንደሚሰደዱ ተገልጸዋል። የዚሁ ፍልሰት መንሲኤ በሀገሪቱ ያለው አ ስ ከ ፊ ጭ ቆ ና መሆኑ አለም አቀፋዊ ታዛቢዎችም ጠቁሟል። Vittorio Longhi, (Oct. 3, 2014).

እያሳዩት የሚገኙ፡ “የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዲምህት)” በሚል ሽፋን የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ድርጅት ናቸው።

“ዲምህት” የሚናገሩት ቋንቋ ትግርኛ ቢሆንም ኤርትራውያን አይደሉም። መጀመሪያ በኤርትራ ውስጥ ገብተው መደራጀት ሲጀምሩ፡ አላማቸው ጸረ ወያኔ ትግል አካሂደው፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት መሆኑን በማስመሰል ነበር[3]። የታጠቁት ጦር መሳሪያ በሙሉ ዘመናዊ ነው። ቁጥራቸው እጅግ በርካታ ነው፤ ከሃያ ሽሕ እስከ አርባ ሽሕ ይገመታል። ኑሮዋቸው: ይዞታቸውና ሁኔታቸው ሁሉ ሲታይ እንደ ቅልብ የዘውድ ወታደር የተሟላ ነው። በተለያዩ የኤርትራ ክፍሎች ይገኛሉ። አንዳንድ የውስጥ ታዛቢዎች አክለው እንደሚገልጹት ከሆነ ከትግራይ ክልል ራቅ ባሉ ቦታዎች በሳሕል አውራጃ: በአፍዓበትና በሌሎች ስፍራዎች ሳይቀር፡ ልዩ ወታደራዊ ጦር ሰፈርና ማሰልጠኛ ማዕከል አላቸው።

“ዲምህት” ኤርትራውያንን ለማደናገር ሲባል ጸረ ወያኔ የሚመስል የውሸት ቅስቀሳ አንዳንዴ የሚያሰሙ ቢሆንም፡ ጎልቶ የሚታይ ወታደራዊ እንቅስቃሴ የላቸውም። ዋና “ተልእኮዋቸው ወይም አጀንዳቸው” ሌላ ነው[4]። ባጭሩ፡ ዲምህት ወያኔን የሚቃወሙ እንቅስቃሴ ሳይሆኑ የኢሳያስ መንግስት በኤርትራውያን የዓመጽ ማዕበል እንዳይጠቃ ወይም በህዝባዊ ኃይል ከስልጣኑ እንዳይፈነገል የሚጠብቁና የሚከላከሉ የትግራይ ሰዎች ናቸው ።

5. የኤርትራ አንድነት አሁንም አደጋ ላይ እየወደቀ ነው። ሌላ ቀርቶ በተቃዋሚ ኃይሎች አካባቢም፡ የብሄር ብሄረሰብና የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን፡ ከዚያም የወረደ አካሄድና አመለካከት እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ነው። ከዚህም አልፎ አውራጃዊነት: ጎጠኝነትና የዘር ሐረግ መሰረት ያደረገ የአደረጃጀት ስርዓት አዲስ ፋሽን ሆኖ በይፋ ዘመቻ እየተካሄደበት መሆኑን ተስተውሏል። የዚሁ ውጤትም በባህልና በቋንቋ አንድ በሆነው ትግርኛ ተናጋሪው የከበሳ (ደገኛው) ህዝብ እንኳን ሳይቀር፡ የጥላቻና የማከፋፈል እንክርዳድ ዘር እየተዘራ ይገኛል። ይህ ዓይነቱ መጥፎ አሻራና ክስተትም ከኢሳያስና ወያኔ የረጅም ጊዜ ዕቅድና አጀንዳ ጋር ተደምሮ፡ በሀገራችን የወደፊት ዕጣ ፋንታ ላይ ሊኖረው የሚችል ትርጉምና ተፅዕኖ በጣም አደገኛ መሆኑን መገመቱ አያዳግትም። በዚሁ ነጥብ ዙሪያ ወደኋላ ላይ በሰፊው እመለስበታለሁ።

ከዚሁ አደገኛና መርዘኛ አካሄድ ጋር በተያያዘ በኤርትራ ደንከልያን - ማለት ዓፋርን - በሚመለከት እየተነሳ ያለውን መሰሪ ፓለቲካዊ ክስተትም በጥሞና መገንዘቡና ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። ከአንድ ዓመት ገደማ በፊት በዚሁ በዲያስፓራ አንድ “ኤርትራዊ ሀገረ-አፋር በስደት” (Eritrean Afar State in Exile — EASE) የሚባል አለም-አቀፋዊ ድርጅት እንደተቋቋመ ታውቋል። ድርጅቱም በሰነዱ ላይ በይፋ ካስቀመጣቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች አንዱ በአለም-አቀፋዊ

---

3. ዲምህት፡ በኦፌሳላዊ ድህረ ገጻቸው (ዌብሳይታቸው) እንዳሰፈሩት፡ አላማቸው “ዴሞክራስያዊ ስርዓት ያላት አንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት…ፖለቲካዊና የትጥቅ ትግል በማጠናከር….ጸረ ህዝብ የሆነውን የወያኔ/ማለሊት ስርዓት ከስልጣን ማስወገድ“ መሆኑን ገልጸዋል። www.tpdm.org - AIM

4. Martin Plaut, October 25, 2014

ሕግ መሰረት "የአፋር ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰንና ራስ ገዝ" ማረጋገጥ ነው[5]። በአጠቃላይ የድርጅቱ ዋና አላማና ግብ ደንከሊያን በአፋር ተወላጆች ቁጥጥር ስር እንዲውል ማድረግ ነው ይላል። በዚሁ የአፋር አለም አቀፋዊ ድርጅት ትልቅ ሚና ከሚጫወቱት አንዱ ፕሮፌሰር ጆዘፍ ማግነት የሚባል ካናዳዊ ነው። ፕሮፌሰሩ፡ "አፋር፡ ማለት ደንካልያ፡ በተለይም ከ1995 ጀምሮ፡ በኤርትራ የባዕድ አገዛዝ (ኮሎኒ) ስር ወድቆ ያለ ቦታ ነው" ብሎ በይፋ የሚሟገት ሰው ነው[6]።

ይህ የአፋር አለም-አቀፋዊ ድርጅት ከሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አንዱ በኤርትራ ውስጥ "የሕገ መንግስታዊ ጽገና" ነው። የጥገናው ዋና ይዘትም በኤትኒክ ፌዴራሊዝም ላይ የተመሰረተ "የብሄር ብሄረሰቦች መብት (ሪጅናል አውቶኖሚ)" ማረጋገጥ የሚል ነው[7]።

በነገራችን ላይ፡ ባለፉት ዓመታት - ማለትም ከ1993 ዓ.ም ጀምሬ - በተለያዩ መድረኮችና አጋጣሚዎች በፕሮፌሰር በረከት ሀብተስላሴ ሊቀመንበርነት የተመራው ኮሚሽን የነደፈው ሕገ መንግስት መሰረታዊ ስህተት እንዳለውና የተፋለሰ መሆኑን ገልጬላችሁ ነበር። ይሁን እንጂ፡ እስካሁን ድረስ ፕሮፌሰር በረከት ይሁን ሌላ የኮሚሽኑ አባል የተነደፈችው ሕገ መንግስት ተግባር ላይ እንድትውል ከመፎረፎጥ በስተቀር የአነዳደፉ ሂደት ፈጽሞ ስህተት እንደነበረ አልተቀበሉም። እንዲያውም ላቀረብንላቸው ገንቢ ሀሳብና አስተያየት ጆሮ ዳባ በማለት አግባብ ባለው መንገድ አንዳችም መልስ አልሰጡም።

አሁን እነዚህ የደንከልያ ወይም ዓፋር የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት የሚጠይቅ እንቅስቃሴ በተደራጀ መልኩ ከተጀመረ ወዲህ ግን ፕሮፌሰር በረከት ያችን "ሕገ መንግስት" በሚመለከት አንድ አሳሳቢ ነገር አሰምቷል። እ.አ.አ በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም በካናዳ በኦታዋ ከተማ ውስጥ በተካሄደው ስብሰባ ላይ ከካናዳዊው ጆዘፍ ማግነት ጋር ሕገ መንግስቱን በሚመለከት አንድ መግባባት ላይ የደረሰ ይመስላል። ስለ ስብሰባው የወጣው ዘገባ እንደሚያመለክተው፡ ሁለቱ ሰዎች፡ ማለት ፕሮፌሰር በረኸትና ፕሮፌሰር ጆዘፍ ማግነት፡ "ሕገ መንግስቷ"፡ በሀገሪቱ የሚገኙ በቁጥር ከዘጠኝ በላይ ለሆኑት ብሄሮች እውቅና ለመስጠት ትችል ዘንድ፡ አብረው እንደገና ሊጽፏት በመርሕ ደረጃ ተስማምቷል" በማለት ገልጾዋል[8]። ይህ ዘገባ ልክ ከሆነ፡ የተደረሰው ስምምነት ድንገተኛ (ያልተጠበቀ) ከመሆኑም አኳያ ትንሽ የሚያሳስብ ነገር ነው። ፕሮፌሰር በረኸት፡ በእኛ በተቃዋሚዎች በኩል ሲቀርብ የነበረውን አስተያየትና ወቀሳ ወደ ጎን ትቶና ጆሮ ዳባ ብሎ፡ አፋሮችና

5. Eritrean Afar State in Exile (EASE), "Restoring the Dignity of Red Sea Afar People democratically", p.5
6. ፕሮፌሰር ጆስፍ ማገነት ግንቦት 24, 2013 በኦታዋ፡ ካናዳ ያቀረበው ዲስኩር (Professor Joseph Magnet May 24, 2013 Speech Ottawa Canada በ www.youtube.com
7. Eritrean Afar State in Exile (EASE), "Restoring the Dignity of Red Sea Afar People democratically", p.7
8. Ahmed Y. Mohamed, Historic Meeting of International Foreign Affairs Experts Leads to Landmark Agreeement To Re-write Eritrean Constitution", Red Sea Afar Democratic Organization (RSADO), Oct. 28, 2012

የቅርብ አማካሪያቸው የሆነው ጆዞፍ ማግነት ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ "ሕገ መንግስቷ" እንደገና እንድትጻፍ ሲስማማ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ የሆነ ተፅዕኖ ያለ ይመስላል። ከአሰብና ደንከሊያ፡ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የኤርትራን አንድነትና ሉዓላዊነት ስጋት ላይ የሚጥል የተጠነሰሰ አኩይና መሰሪ አጀንዳ እንዳይኖር እጅግም የሚያጠራጥር ጉዳይ ነው።

6. ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ስላለው ዝምድና እርስ በራሳቸው የሚጋጩ ሐሳቦች እየተሰሙ ናቸው። በአንድ በኩል የሁለቱ አጎራባች ሀገሮች መንግስታት፡ ማለትም የኢሳያስ አፍወርቂና የወያኔ መንግስታት፡ መቀራረብን በተመለከተ፡ አስፈላጊነትና ዝግጁነት እንዳለ በተደጋጋሚ በአደባባይ ሲነገር ይደመጣል። ከዚህም አልፎ ዲፕሎማሲያዊ እርምጃዎች በሚስጢር እየተካሄዱ እንደሆነም የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አልፎ አልፎ ይታያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ነገሮችን ከላይ ላዩ በጨረፍታ ሲታዩ ሁለቱ ሀገሮች እንደገና ወደ ዉጊያ እንዳይገቡ ያሰጋል የሚያሰኙ የተለያዩ መግለጫዎችና ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ይሰማሉ።

*መቀራረብን በሚመለከት፣*

(ሀ) የታወቁ ኢሳያስን የሚወክሉ ባለስልጣናት ከኢትዮጵያ ጋር ዝምድና ለመመስረት ፍላጎት እንዳላቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች መግለጫ ሲሰጡ ተደምጧል። ራሱ ኢሳያስ አፍወርቂም ኤርትራ ከኢትዮጵያ የኤለክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት እንዳላት ባለፈው መስከረም 2013 ዓ.ም አካባቢ ገልጸ እንደነበር ይታወሳል። በቅርብ ጊዜም ኢሳያስ በሱዳኑ ፕረዚዳንት በዑመር አልበሽር አማላጅነት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለመታረቅና ለመግባባት ጥያቄ አቅርቦ እንደነበርና ዑመር አልበሽርም፡ ሁለቱን ወገኖች ለማቀራረብ ሙከራ አድርጎ እንደነበር ተገልጸዋል። በኢትዮጵያ በኩልም እንደዚሁ የተለያዩ ባለስልጣናት በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሰላም ለማስፈን የተቻላቸውን ጥረት ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ሲገልጹ ተሰምቷል። የአሁኑ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሐይለማሪያም ደሳለኝ ከኤርትራ መንግስት ጋር ለመግባባት ሁሉም ነገር ለማድረግ፡ ብሎም እስከ አስመራ ድረስ ሄዶ ለመነጋገር ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለው ገልጸ ነበር[9]።

(ለ) በምዕራቡ ዓለም በኩልም በህግዲፍና በወያኔ መካከል ይፋና ግልጽ የሆነ መቀራረብ (ሰላም) እንዲኖር የሚደግፉ ሀሳቦች አልፎ አልፎ እየተገለጹ ናቸው። ለምሳሌ በጆርጅ ሀርበርት ቡሽ አስተዳደር ዘመን፡ የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስቴር የነበረ ሀርማን ኮሀን "ኤርትራ አሁን ካለችበት ከዓለም ተነጥላ ከመኖር ይልቅ ከአለም-አቀፋዊ ማሕበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ ይኖርባታል" ሲል ምክሩን ለገሶ ነበር[10]። ከጥቂት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበረ ደቪድ ሽንም የሀርማን ኮሀን ምክር በመሰረተ ሐሳቡ የሚጋራ መሆኑን ቢገልጽም፡ በመሬት ላይ ያለው ሁኔታ ግን ቀላል እንዳልሆነ

---

9. "Can Ethiopia and Eritrea finally find peace?",Al Jazeera 08. 12. 2012 www.aljazeera.com)
10 . Herman J. 'Hank Cohen, africanarguments.org, Dec. 16, 2013'

ተናግሮ ነበር። ዓሰብን ወደብ አልባ ሆና ለቀረቺው ኢትዮጵያ ክፍት ለማድረግ ይቻል ዘንድ በሁለቱ ወገኖች መካከል ውይይት ቢጀመር ጠቃሚ መሆኑን ሀሳብ አቅርቦ ነበር[11]።

አሳሳቢ የሚመስሉ ሁኔታዎችና ክስተቶችም አሉ፣

(ሀ) የኢሳያስና የወያኔ መንግስታት ነጋ ጠባ እርስ በራሳቸው ሲካሰሱና ሲሰዳደቡ ይሰማሉ። እንዲሁም በአንዳንድ አጎራባችና አዋሳኝ ቦታዎች ላይ፡ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱና ከዚያ ጋር በተያያዘ የቃላት ጦርነትና ማስጠንቀቂያዎች ይስተጋባሉ።

(ለ) በቅርቡ በነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሃይለማርያም ደሳለኝ "በአፍሪቃ ቀንድ የግብረ ሽበራ መናሃሪያ የሆነች ሀገር ኤርትራ ናት። ስለዚህ ሰላም ለማግኘት ሲባል ኢትዮጵያ የኢሳያስን መንግስት ከስልጣን ለማስወገድ የሚያስችል አዲስ ስትራተጂ አውጥታለች" ሲል ገልጸዋል[12]። ይህ ዓይነቱ አነጋገር በመሰረቱ አዲስ ነገር ባይሆንም፡ ከወትሮው የተለየ፡ ትንሽ ጠጠር ባለ ሀይለ ቃል ስለቀረበ፡ ለብዙ ሰው ምናልባትም ጦርነት ሊያስከትል ይችላል የሚል ግምት እንዲኖረው አድርጎት ነበር።

እነዚህ እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ መግለጫዎችና ክስተቶች ይኑሩ እንጂ፡ በመሬት ላይ ያለውና ያልተለወጠው እውነታ የሚያመለክተው፡ በሁለቱ መንግስታት መሀከል ያለው ሁኔታ የሰላም መሆኑን ነው። ስለዚህ በቃላት ደረጃ የሚወረወሩ ማስጠንቀቂያዎችና ማስፈራሪያዎች ቢደረደሩም፡ ኢሳያስና ወያኔ በእርግጥ ወደ ጦርነት ሊገቡ እንደሚችሉ በተጨባጭ የሚያሳምኑ ምልክቶች የሉም።

ከላይ ከቁጥር 1 እስከ 6 የተጠቀሱ በሀገራችን ላይ የተንሰራፉ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን በአግባቡ ለመገንዘብ ከሁሉም በፊት ፓለቲካዊ መሰረታቸውን ለይቶ ማወቅ የግድ ይለናል። በኔ አመለካከት የሀገራችንን ችግሮች ፖለቲካዊ መሰረት ወይም መነሾ ለይቶ ለማወቅ የሚከተሉትን ሶስት የተዛመዱ ርእሶች በአግባቡ ማገናዘብ ያስፈልጋል። እነሱም .........

1. የትግራይ ትግርኚ ጽንሰ ሀሳብ ታሪክና ዕድገት
2. የወያኔ መንግስት አመጣጥና ተልእኮ
3. የኢሳያስ አፈወርቂ ባህርያትና የስልጣን ጥማት ናቸው።

11. David Shinn, fricanarguments.org/ January 13, 2014
12. Tsenat Interview with PM Hailemariam Desalegn, August 9, 2014 (aigaforum.com Blog)

## ፪፡ ትግራይ-ትግርኚ በኤርትራና በትግራይ

ትግራይ-ትግርኚ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በ40ዎቹ በእንግሊዞች ግፊት የተስተጋባና የተስፋፋ ነገር ነበር። በመሰረቱ እንግሊዞች የፈለሰፉት ግን አልነበረም። እንግሊዞች ሀገራችንን ከመያዛቸው በፊት፡ የኢጣሊያ መንግስት ቀደም ብሎ ቀይሶት በነበረ የውጭ ጉዳዩ መመሪያ ላይ የተንተራሰ ነበር። ይህንን ነጥብ ቀደም ብዬ በ2012 ዓ.ም ባስተላለፍኩት መልእክት በዝርዝር ገልጨዋለሁ።

በ40ዎቹ ገደማ ብቅ ካሉ የፓለቲካ ማሕበራት አንዱ፡ በአካባቢው ስያሜ "ኤርትራ ንኤርትራውያን" (በእንግሊዞች ዘንድ ደግሞ "ሊበራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ") እየተባለ ይጠራ የነበረ ነው። ማሕበሩ በዋናነት ይዞ ይንቀሳቀስበት የነበረ አላማና አቋም ትግራይ ትግርኚ በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነበር። አላማውም ኤርትራን እንደመናሃሪያና መነሻ በመጠቀም መረብን ተሻግሮ ትግርኛ ተናጋሪዎች የሚኖሩባቸው ቦታዎች ሁሉ በአንድ ግዛት በማጠቃለል በታላቅዋ ብሪታኒያ ሞግዚትነት ስር ከቆየ በኋላ፡ አንድ ሉዓላዊ ሀገር ሆነው እንዲቀጥሉ ነበር። ይህ ኣለውሃ-ምላሽ እየተባለ ሲጠቀስ የነበረው ዕቅድ ነው።

ሁኔታዎች ተቀያይረው "ኤርትራ ንኤርትራውያን" ተብሎ ይጠራ የነበረው የፓለቲካ ማሕበር በተለያዩ ምክንያቶች ነጻነት የሚለውን አጀንዳ ትቶ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደረሽን የመቀላቀል ሀሳብ ከተቀበለ በኋላ፡ ትግራይ ትግርኚ የሚለው ዕቅድ ተጣለ። እንደ ጽንሰ ሀሳብም ቀስ በቀስ እየከሰመ ሄደ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ማስታወስ ያለብን አስፈላጊ ነጥብ አለ። እሱም የትግራይ ትግርኚ ጽንሰ ሐሳቡ በይበልጥ ይብላላ የነበረው በተወሰነ የኤርትራ ደጋማው ክፍል መሆኑ ነው። በትግራይ በኩል፡ አንዳንድ መሳፍንቶች ለተወሰነ ጊዜ አስበውበት ነበር የሚባል ቢሆንም፡ በቁጥር ይህ ነው የሚባል የተንቀሳቀሰለት አካል አልነበረም።

ትግራይ ትግርኚ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ለተወሰነ ዓመታት ተዳፍኖ ከቆየ በኋላ፡ በ70ዎቹ አጋማሽ እንደገና እንዳዲስ መነሳት ጀመረ። ሓሳቡ እንደገና ማንሰራራት የጀመረው በወቅቱ በትግራይ ከተፈጠረው የፓለቲካ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ነበር። በዚያን ጊዜ በትግራይ መጀመርያ ተነስቶ የነበረው የፓለቲካ ንቅናቄ ያ በነመምህር ዮሃንስ ተክለ ሃይማኖት ይመራ የነበረው "ግምባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ" - ግገሓት - (በአማርኛ ሲተረጎም "የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር - ትነአግ- TLF)" ተብሎ የሚጠራ ነበር። ግገሓት በወቅቱ ያሰራጨው "ቅያ ትግራይ-ትግርኚ" የሚል ጥናታዊ ዘገባ እንደሚያሳየው፡ድርጅቱ ኤርትራና ትግራይ አንድ አካል ሆነው ከኢትዮጵያ ተገንጥለው ነጻ እንዲሆኑ የሚል የጸና አቋም ይዞ ይንቀሳቀስ ነበር[13]። በድርጅቱ (ግገሓት) አገላለጽና እምነት መሰረት "ትግራይ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሰር ተይዛ የቆየች ናት። ስለዚህ የትግራይ ጥያቄ የቅኝ ግዛት (ኰሎኒያል) ጥያቄ ነው። መፍትሄውም ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ከኤርትራ ጋር በማዋሃድ አንድ ሀገር ማድረግ" ነበር። ግገሓት አላማውን በህዝቡ ዘንድ ለማስተዋወቅ በራሪ ጽሑፎችና መጽሄቶች በመጠቀም መልእክቱን ያሰራጭ ነበር። ለምሳሌ በወቅቱ ያስተጋባቸው ከነበሩት ዋና ዋና መፈክሮች

13. ገብሩ አስራት፡ ገጽ 47

ውስጥ “ሓድነት ኤር-ትግራይ“ “የኤርትራና የትግራይ አንድነት ይለምልም“ : ወዘተ የሚሉ ነበሩ[14]።

ግገሓት በኤርትራ ጉዳይ ላይ የነበረው አመለካከትና አቋምም “የማያወላውል” ነበር። በግገሓት አመለካከት “የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት (ኮሎኒያል) ጥያቄ” ነበር። ከዚህ አመለካከትና አቋም በመነሳት በወቅቱ ከጀብሃ ጋር ጥሩ ዝምድና ነበራቸው። ነገር ግን ጀብሃዎች “ትግራይ-ትግርኚ” የሚለውን የ”ግገሓት” አቋም አይደግፉም ነበር[15]።

ግገሓት በእንቅስቃሴ ላይ እያለ “ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ” (ተሓህት) የተባለ ሌላ የፖለቲካ ንቅናቄ በትግራይ ተፈጠረ። ይህ ሄዶ ሄዶ ራሱን “ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)” ብሎ የሰየመና አሁንም በኢትዮጵያ ስልጣን ይዞ የሚገኝ ድርጅት ነው። ከጅምሩ በግገሓትና ተሓህት መካከል ልዩነቶችና አለመግባባቶች የሚመስሉ ነገሮች ነበሩ። ሁለቱን በተጓዳኝ በትግራይ ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ በኋላ በሂደት ተግባብተው እንዲቀላቀሉና አንድ ድርጅት እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ደርሰው ነበር። በስምምነቱ ሂደት ላይ ከተግብቡባቸው አንኳር ነጥቦች አንዱ፡ የትግራይ ጥያቄ የቅኝ ግዛት (ኮሎኒያል) ጥያቄ ነው የሚለው አነጋገር የተሳሳተ መሆኑ ነበር። ስለዚህም የትግራይ ጥያቄ የብሄር ጥያቄ ነው የሚል አቋም በሁለቱም ይፋዊ ተቀባይነት አገኘ።

የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከት በሁለቱ - በግገሓትና ተሓህት - መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት አልነበረም። ሁለቱም ድርጅቶች “የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያዊ ነው። መፍትሄውም የኤርትራ ነጻነት ማረጋገጥ ነው” ነበር የሚሉት። ስለዚህ በኤርትራ ጉዳይ ላይ መከራከርና መደራደር አልነበራቸውም።

ይሁን እንጂ፡ የሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች - ግገሓትና ተሓህት (ወያኔ) - አንድነት ሩቅ ሳይሄድ የግገሓት መሪዎች የፈጸሙት ወንጀል አላቸው በሚል ሰበብና ጥርጣሬ ተኝተው እያሉ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደረገ፤ ወዲያውኑም እርምጃ ተወሰደባቸው። በዚሁ ሁኔታ የግገሓት ህልውና አከተመ[16]። ግገሓት ጠፍቶ በተሓህት (ወያኔ) ተተካ።

ተሓህት - ያሁኑ ወያኔ - በየካቲት 1976 ዓም ባወጀው ማኒፌስቶ ላይ እንደሚያመለክተው የትግሉ ዋና አላማ “ነጻ ዲሞክራሲያዊት ረፑብሊክ ትግራይ” መመስረት ነበር[17]። ይሁን እንጂ፡ ይህን የነጻ ሪፓብሊክ ሀሳብ አብዛኞቹ የድርጅቱ ታጋዮች አልተቀበሉትም ነበር። በዚህ ምክንያት ከ6 ወር በኋላ ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ነጻ ሪፓብሊክ መመሰረት የሚለው አንቀጽ እንዲወጣ ተደርጓል[18]። ስለዚህ የትግራይ ጥያቄ የብሄር ጥያቄ ነው የሚል አነጋገር የድርጅቱ ይፋዊ አቋም ሆነ ማለት ነው።

---

14. ዝኒ ከማሁ፡ ገጾች 47-48
15 .ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 48
16 .ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 64
17. Tigray Manifesto, February 1976 p. 25 (በእጅ የተጻፈ)
18. ገብሩ አስራት፡ ገጾች 51-52

ተሓህት (ወያኔ) "ትግራይ ኮሎኒ አይደለችም"፣ "ትግራይ ከኢትዮጵያ አትለይም" እያሉ ግገሓትን ቢቃወሙም ቅሉ ይህንን በሚመለከት ከመሪዎቹ አንዳንዱ ከግገሓት የተለየ ሀቀኛ አቋም ነበራቸው ብሎ ለማመን ያጠራጥራል። ለምሳሌ አቶ ስብሃት ነጋ በመጀመሪዎቹ የትጥቅ ትግሉ መድረኮች፡ "የትግራይ ጥያቄ ልክ እንደ ኤርትራ የቅኝ ግዛት (ኮሎኒያል) ጥያቄ ተደርጎ መወሰድ አለበት" የሚል ሀሳብ በመሰንዘሩ ሀይለኛ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር[19]።

ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ነጻ ሪፓብሊክ ስለመመስረቱ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ፡ የወያኔ ይፋዊ አቋም፡ በቁም-ነገሩ፡ ከግገሓት አቋም ትርጉም ባለው መጠን አይለይም። በአጭሩ ትግራይን በሚመለከት የወያኔ አቋም ትግራይ እንደ ብሄር "የራስህን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል" መብትዋ የተጠበቀ ነው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ "ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ" ጨቋኝ መንግስት ስልጣን ላይ ከመጣ ተገንጥላ የራስዋን ነጻ ሪፓብሊክ መመስረት ትችላለች የሚል ነው። በኢትዮጵያ የሚመጣው መንግስት ዴሞክራሲያዊ መሆኑንና አለመሆኑን የሚወስኑት ደግሞ ራሳቸው የወያኔ መሪዎችና መሰሎቻቸው ናቸው። በግልጽ ለመናገር! ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ መንግስት ማለት ወያኔ በባለቤትነት የማያዘው ወይም የማይቆጣጠረው መንግስት ማለት ነው።

ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ፡ "ወያኔ" ስለሚለው ስያሜ አጠቃቀም ላቀርበው የፈለግኩት ማብራርያ አለ። ይህንን ማብራርያ መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑን የተረዳሁት በቅርቡ አቶ ገብሩ አስራት በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ፡ ወያኔና ህወሓት አንድ አይደሉም የሚል ነጥብ አስምሮበት ባየሁ ጊዜ ነው። አቶ ገብሩ እንደጻፈው ወያኔ አመጽን ወይም እምቢታን የሚገልጽ ነው። ህወሓት ግን የድርጅቱ ስም ነው። ድርጅቱ ወያኔ የሚል ቃል በስሙ ላይ የጨመረበት ዋናው ምክንያት ህዝቡ በ ልብ ተማርኮ እንዲነሳሳና ከህወሓት ጐን እንዲሰለፍ ነው።

ገብሩን ያሳሰበው ችግር፡ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ተቃዋሚዎች የትግራይ ህዝብና ህወሓት ሳይለዩ ሁሉንም በጋራ ወያኔ እያሉ የሚጠሯቸው መሆኑን ነው። የትግራይ ህዝብና ህወሓት ለያይቶ አለማየት፡ ትልቅ ስህተት ስለሆነ ትኩረት ልሰጠው የሚገባ ነጥብ ነው።

ይህ ነጥብ ሊያከራክር እንደሚችል ይገባኛል። ሆኖም እስከ ዛሬ ድረስ ህወሓትን ወያኔ እያሉ በአጭሩ መጥራት በኤርትራውያን መካከል የተለመደ ሆኖ ቆይቷል። ይህንን ብለን ስንጠራ ግን ህወሓትንና የትግራይ ህዝብን አንድ አድርገን አላየንም። በርግጥም አንድ አይደሉም። ልክ ህግዲፍን በአጭሩ ሻዕቢያ"፡ ተሓኤን ደግሞ ጀብሃ እያልን እንደምንጠራቸው ሁሉ፡ ህወሓትንም ወያኔ እንለዋለን። በዚሁ ጽሑፌም በተመሳሳይ ይህንን ድርጅት አንዳንድ ቦታ ህወሓት በሌላ ቦታ ደግሞ ወያኔ ብዬ ጠቅሼዋለሁ።

በስተኋላ ላይ በዝርዝር እንደምገልጸው፡ ይህ አሁን በኢትዮጵያ ያለው መንግስት በወያኔ ቁጥጥር ስር የተያዘ ነው። ሕግ አውጪ"፡ ሕግ ተርጓሚና ፈጻሚ አካላት በሙሉ በተለያየ መልኩ በወያኔ የተያዙ ናቸው። የሀገሪትዋን ኢኮኖሚም የሚቂጣጠሩት ወያኔዎች

19. Aregawi Berhe, P. 159, note 72.

ናቸው። አንዳንድ የነርሱ ታማኞችና ተስፈኞች ለሆኑት፡ የሌሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦች አባላት የሆኑ ግለሰቦች የተወሰነ ስልጣን ይሰጥዋቿል። እነዚህ በወንበር ላይ የሚቀመጡ ታማኞች ግን ትርጉም ያለው ስልጣንና ኃይል የላቸውም። ለይስሙላ ብቻ በወንበር ላይ የተቀመጡ ናቸው። ውስጡና ሓቁ ሲታይ ግን፡ በስተጀርባ ወይም በጎን በአመራር በምክትል፡ በረዳትነት ወይም በሌላ ስም ተቀምጠው የመወሰንና የመተግበር ዓቅምና ኃይል ያላቸው ያው የህወሓት አባላት ናቸው። ከዚሁ እውነታ በመነሳት በዚሁ መልእክት በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በብዙ ቦታዎች " የወያኔ መንግስት" ብዬ ጠቅሼዋለሁ።

ወያኔዎች፡ ከ1991 ጀምረው በኢትዮጵያ ያለውን መንግስት ስለተቆጣጠሩት፡ ሕገ መንግስቱን ለራሳቸው አላማ በሚስማማና ለእንቅስቃሴያቸውና ፖሊሲያቸው ማስፈጸሚያ በሚያገለግል መልኩ ተነድፎና ተቀርጾ እንዲጸድቅ አድርጓል። ከሁሉም በላይ ጎልቶ የሚታየውና ለዚሁ ምሳሌ የሚሆነው፡ በሕገ መንግስቱ ላይ በሰፈረው አንቀጽ 39 መሰረት ለብሄር ብሄረሰቦች የተፈቀደው የእስከ መገንጠል መብት ቁልጭ ብሎ እንዲቀመጥ መደረጉ ነው። በዚህ መሰረት ደግሞ፡ ወያኔ በፕሮግራሙም ጭምር እንዳሰፈረው ሁሉ ትግራይን ገንጥሎ ነጻ ሪፓብሊክ ማድረግ ይችላል ማለት ነው።

ሆኖም ትግራይ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ሉዓላዊት ሀገር ሆና ለብቻዋ መቀጠል እንደማትችል ስለአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካ መጠነኛ ግንዛቤ ያለው ሰው ሁሉ በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ነው። ትግራይ ከተገነጠለች፡ ዞሮ ዞሮ ከኤርትራ ጋር ለማበር መሆኑን በቀላሉ መገመት ይቻላል። ይህ እውነታ በርከት ያሉ ኤርትራውያን የፖለቲካ ተዋንያን ሲያወሱት የነበረ ነው። ለምሳሌ መንሆት ወልደማርያም በሕዳር 2002 በዓወተ.ኮም በእንግሊዝኛ ቋንቋ በጻፈው አንቀጽ እንደሚከተለው ይላል።

> *"ህወሓት የትግራይ ነጻ ሀገር ህልውና ለማመቻቸት ሲል የብሄር ብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የሚል መሰረተ ድንጋይ አስቀምጧል። ይህም በሀገሪቱ የጸደቀውን "ኤትኒክ ፌዴራሊዝም" (ethnic federalism) መሰረት ባደረገው ሕገ መንግስት የተደገፈና የታቀፈ እንዲሆን ተደርጓል። ትልቁ አላማም ሃገረ ትግራይን ለማቋቋም አንዳንድ የኤርትራ ቦታዎችን ቆርሶ ወደ ትግራይ ማካለል ነው። ባለፉት ዘመናት የትግራይ ትግርኚ ሕልም እውን ለማድረግ የተደረጉ ሙከራዎችና የነበራቸው ተስፋም አልተሳካም። ለወደፊት ግን ገና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ሆኖ ይኖራል።"*[20]

የትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ ሲተገበር ኤርትራን የሚፈረካክስ ነው። ለዚህ ዋነኛ ምክንያት የሚሆነው ደግሞ ኤርትራ የእስላምና የክርስትያን ሃገር መሆንዋ ነው። የትግራይ ህዝብ በሞላ ጎደል ክርስቲያን ስለሆነ ትግራይ ትግርኚ ተግባር ላይ ሲውል የኤርትራ ሙስሊሞች በቁጥር ተበልጠን በክርስቲያኖች ተውጠናል እንደሚሉ የታወቀ ነው። በቁጥር ተበልጠው እንዲዋጡ ስለማይወዱ ደግሞ ከመገንጠል ሌላ አማራጭ ሊታያቸው አይችልም። ስለዚህ በዚሁ ሁኔታ ኤርትራ የምትባል ሀገር ልትኖር አትችልም።

---

20. Menhot Woldemariam, awate.com

ትገነጣጠላለች"፣ ትጠፋለችም። በብዙዎች ኤርትራውያን አመለካከት ዘንድም አሁን በሂደት ያለው ጉዳይ ይህ ነው።

በግልጽ አልተነገረም እንጂ፡ እንደነ አቶ ስብሃት ነጋ የመሳሰሉ የወያኔ መሪዎችን በተመለከተ ድሮውንም የትግራይ ማኒፌስቶ አላማና ግብ ይህንን ለማሳካት ነበር የሚሉም አሉ።

በተጨማሪም ስለየትግራይ ማኒፌስቶ ቀደም ብሎ ከተገለጸው በመጠኑም ቢሆን ለየት ያለ ሁተታ (version) አለ። በዚሁ ሁተታ ውስጥ በዝርዝር ለመግባት አልፈልግም፤ የሚከተለውን አጭር ነጥብ መግለጽ ግን አስፈላጊ ነው። ይህ የትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ ቀደም ብሎ በተገለጸው መልኩ ላይሳካ ይችላል ከሚል ስሌትና ጭንቀት የተነሳ አንዷት ደንከልያን (ዓፋርን) የምትመለከት ቀጭን አማራጭ ገመድ ያለች ትመስላለች። እሷም በአጭሩ ደንከሊያ (ዓፋር) - የዓሰብ ወደብን ጨምሮ ማለት ነው - "በቅኝ ግዛት ተይዟል" "ከመጠን በላይ የብሄር ጭቆና ደርሶባቸዋል" ምንትሴ" በማለት "የራስ ዕድል በራስ የመወሰን መብት" በሚል ጥያቄ መሰረት ከኤርትራ እንድትገነጠል ይደረጋል። ከተገነጠለች በኋላ ደግሞ ለብቻዋ ትሆናለች ወይም ከኢትዮጵያ ጋር ትቀላቀላለች። ትግራይ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ለብቻዋ በምትሆንበት ጊዜ ደግሞ ደንካሊያ የትግራይ ሪፑብሊክ አካል ትሆናለች። እንግዲህ ይህቺ ቀጭን ሀሳብ ናት በቀጭን ክር ተንጠልጥላ በድብቅ እንደ አማራጭ የተያዘቺው።

ይህቺ አማራጭ ቀደም ብሎ ከተገለጸው የትግራይ ትግርኚ ዕቅድ በትንሽ ነው የምትለየው። በተለይም መጪው የኤርትራ ዕድልን በሚመለከት በመሰረቱ አትለይም። በሁለቱም መንገዶች ማለት በትግራይ-ትግርኚም ሆነ በደንከሊያ በኩል በታሰቡት አማራጭ መንገዶች ኤርትራ ሄዶ ሄዶ በመጨረሻ ተበታትና ነው የምትቀረው።

የትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ በእርግጠኝነት እንዳለ ከአንዳንድ የወያኔ መሪዎች ገለጻዎች የሚንጸባርቅ ነው። ለምሳሌ በግንቦት ወር 2014 በታተመው የቃለ መጠይቆች ስብስብ አቶ ስብሃት ነጋ ኤርትራን በሚመለከት በሰጠው ሀሳብ ላይ ያሰመረበት አመለካከት ይህ ዕቅድ እንዳለ ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

አቶ ስብሃት የባድመ ቀውስ ትልቅ መነጋገሪያ ሆኖ: ኢሳያስ ደግሞ ሰላማዊ መፍትሄ አልቀበልም ብሎ አፈንግጦ በነበረበት ጊዜ፡ ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ የኃይል እርምጃ እንዳትወስድ የሚቻለውን ያህል አድርጎ ነበር። አሁንም ቢሆን፡ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር መዋጋት አልነበረባትም ባይ ነው። የአቶ ስብሃት ነጋ አቋም መነሻው የኤርትራና የትግራይ ዝምድና ህያው ነው የሚል አመለካከት ነው። አቶ ስብሃት "ትግራይኮ ካለ ኤርትራ አትኖርም፤ ኤርትራም እንደዚሁ"[21] በሚል አክራሪ እምነቱ የታወቀ ሆኗል።

የአቶ ስብሃት አባባል በአሁኑ ጊዜ የመጣው ዝም ብሎ አይደለም። አባባሉ ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኋላ በወያኔ መሪዎች አካባቢ የትግራይ መገንጠልና ከኤርትራ ጋር ሊኖራት የሚችል ዝምድናን በሚመለከት ውስጥ ለውስጥ እየተካሄደ ያለው መመሳጠር

21. ስብሃት ነጋ፡ቃለ-መጠይቅ ዮናስ በላይ አበበ፣ ገጽ 54

መግለጫ ነው የሚሉ አስተያየቶች አሉ። ዮናስ በላይ በተጠቀሰው የቃለ መጠይቅ ስብስብ ላይ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፡ ስለዓሰብ ወደ ኤርትራ መሄድ ተጋሩ ያሰሙት ተቃውሞ የለም በማለት ያቀረቡትን ክርክር በመጥቀስ፡ የራሱን አስተያየት አክሎ ገልጸዋል። ዮናስ በመመሳጠር ላይ ያሉትን ቡድኖች "ሸፍቶች" ብሎ ነው የሚገልጻቸው። ሸፍቶች ተብለው የተገለጹትም በወያኔ አመራር ውስጥና ከዚያ ውጭ ያሉ የትግራይ ብሄራዊ ስሜት እንደ ፓለቲካ መሳሪያ እየተጠቀሙ ለያይተህ ግዛ የሚለውን ፈሊጥ የሚተገብሩና የሚዘምቱ ጸረ-ህዝብ ናቸው። ዮናስ ፕሮፌሰር መስፍን ያቀረቡትን ክርክር በመጥቀስ፡:-

> *"ሸፍቶቹ ከመለስ ሞት ወዲህ፡ የዓሰብ ወደብ በኤርትራ እንድትቆይ ያደረግነው ምናልባት ከኢትዮጵያ ከተገነጠልን ወደ ኤርትራ መቀላቀላችን ስለማይቀር ነው ብለው ውስጥ ለውስጥ ወጣቶችን እንደሚቀሰቅሱበት ቢያውቁ ምን ይሉ ይሆን? ስብሃት ነጋ፡ "ትግራይ ያለ ኤርትራ፡ ኤርትራም ያለ ትግራይ መኖር አይችሉም" ያሉትን የዚሁ ሴራ አንድ መግለጫ ነው።" ይላል[22]።*

ይህ ዓይነቱ መመሳጠር የትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ ለመተግበር ቅድመ ዝግጅት ሲደረግ እንደቆየና አሁንም እየተደረገ እንዳለ የሚያሳይ ነው።"

ካሁን በፊትም ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ይካሄድ የነበረው ዝግጅት በተደጋጋሚ በአለም-አቀፋዊ መጽሄቶችም ሳይቀር ተጋልጧል። ለምሳሌ በ2007 ኢንዲያን ኦሽን ኒውስ ለተር (ION) የተባለ መጽሄት በአንድ ወቅት ባቀረበው ዝርዝር ሪፓርት ላይ እንደገለጸው መለስ ዜናዊ ያዘጋጀውና ከፍተኛ የወያኔ መሪዎች ተቀብለው ያጸደቁት 22 ገጾች ያሉት ሚስጢራዊ ሰነድ ለፈጻሚት ኮሚቴ (አስተዳደር) አባላት እንደተሰራጨ ገልጸዋል። የተሰራጨው ሰነድ ክልል ትግራይ አስፈላጊ ከሆነ ለብቻዋ ለመቆም እንድትችል ጥረት እንዲደረግም ያሳስባል። በተጨማሪም ሚስጢራዊ ሰነዱ ከኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ዝምድና መደረግ አለበት ይላል። የION ሪፓርት አያይዞ የሚስጢራዊ ሰነዱ ይዘት ከትግራይ ትግርኚ አላማ ጋር የሚስማማና የሚተሳሰር ነው ይላል። በተጨማሪ ሪፓርቱ ትግራይ ትግርኚ "ከ20 ዓመት በፊት" - ማለት ህዝባዊ ግንባር እና ወያኔ ገና በትጥቅ ትግሉ በነበሩበት ጊዜ የተወሰኑ ተጋሩና ኤርትራውያን ያጸደቁት ዕቅድ እንደነበረ ይገልጻል[23]።

በኋላም፡ በመስከረም 2013 - ማለት ከመለስ ዜናዊ ህልፈት አንድ ዓመት ገደማ ቆይቶ - የትግራይ- ትግርኚ ዕቅድ በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ እንደገና ION አጋለጠ። በተጠቀሰው ጊዜ አንድ የታወቀ የወያኔ አባል ወደ ፍራንክፈርት ከተማ፡ ጀርመን፡ ድረስ መጥቶ በነበረበት ጊዜ ተጋሩና የወያኔ ደጋፊ የሆኑት ኤርትራውያን ብቻ የተሳተፉበት ሕቡዕ ሊባል የሚችል ስብሰባ በማካሄድ መልእክቱን አስተላልፏል። የመልእክቱ ዋና ይዘት ደግሞ "በትጥቁ ትግል ዘመን እነዚህ ትግራይ ትግርኚ አብረን ጸረ ደርግ ታግለን አሸንፈናል፣ አሁንም "የትግራይ-ትግርኚ ህብረት መታደስ አለበት"፣ ዛሬም እንደ ትላንቱ አብረን መታገል አለብን" የሚል ነበር[24]። ይህ ዓይነቱ አባባል ገና በጥንስስ

22. ዮናስ በላይ አበበ፡ ገጾች 81-82፣ የግርጌ ጽሁፍ 84
23. Indian Ocean Newsletter, No. 1211, March 31, 2007
24. Indian Ocean Newsletter October 02, 2013

ላይ እየተካሄደ ያለው የትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ ነጸብራቅ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የተከታተሉ ኤርትራውያን ይመሰክራሉ።

አሁን ደግሞ - ማለት ጥቅምቲ 30, 2014 - አቶ ስብሃት ነጋ ራሱ፡ ከአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ (የትግርኛ አገልግሎት) ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ፡ አንድ ከበድ ያለ ትርጉም የተሰጠው አነጋገር አሰምቷል። የተነገረው ቃልም፡ በትጥቅ ትግሉ የኤርትራ የነጻነት ጥያቄን የሚመለከት ነበር። ከላይ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የህወሓት አቋም "ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት (ኮሎኒ) ስር የወደቀች ሀገር ናት፣ ስለዚህ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት (ኮሎኒያል) ጥያቄ ነው" የሚል ነበር። እስከ ዛሬ ድረስም ይፋዊ አቋማቸው አልተቀየረም። አሁን ግን አቶ ስብሃት የድርጅቱን አቋም በሚጻረር መልኩ "የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው የሚለው የህወሓት ፓሊሲ እንደገና መመርመር አለበት" ሲል ተናግሯል። አቶ ስብሃት በኤርትራ ነጻነት ላይ አሁንም የጸና እምነት እንዳለው ይግለጽ እንጂ የተናገረው ነጥብ ግን ብዙ ኤርትራዊያንን አሳስቧል።

አቶ ስብሃት እንዲህ ዓይነቱን ከባድ አነጋገር ያላንዳች ነገር ዝም ብሎ እንደመጣለት ያነሳው አይደለም። አሁን ደርሶ እንዲህ ማለቱ፡ አላማው የኤርትራና ትግራይ ("ኢትዮጵያ") ዝምድናን በሚመለከት የሆነ ሀሳብ ወይም ግምቶችን ለማስተጋባትና ለማስተላለፍ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።

ወያኔ የኤርትራ ጥያቄ "መፍትሔው… ነጻነት ነው" ሲሉ ነበር። ይህንን ሲሉ ደግሞ መነሻቸው የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው የሚለው አቋም ነበር። ዛሬ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አልነበረም ከተባለ፡ መፍትሔውም የግድ ነጻነት አልነበረም ማለት ነው ብሎ መደምደም ተገቢ ወይም ትክክል ይሆናል። የአቶ ስብሃት አባባል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ሳትገነጠል ችግሩን መፍታት የሚቻልበት መንገድ ነበር ወደሚለው ሀሳብ መርቶ፡ አሁንም በሌላ መልኩ ኤርትራ ከሌላው አካል ጋር ብታብር መጥፎ አይደለም የሚለውን ሀሳብ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚሞክር ይመስላል። በተጨባጭ አነጋገር የኤርትራ ከጎረቤትዋ ከትግራይ ጋር በሆነ መልኩ መዋኸድ መገመት የሚቻል ለማድረግ የሚሞክር ነው። ስለሆነም የአቶ ስብሃት አነጋገርም ለራሱ የትግራይ- ትግርኚ ዕቅድ ለማመቻቸት እየተደረገ ያለ ዝግጅት አካል ነው የሚመስለው።

ወያኔ የትግራይ-ትግርኚን ዕቅድ ሚስጢራዊ ለማድረግ ቢሞክሩም መደበቅ አልቻሉም። የዕቅዱ መኖርና ሂደት ጊዜና ሁኔታ እየጠበቀ ከብዙ ነገሮች ጋር እየተዛመደ ብቅ ብቅ ማለቱ አልቀረም። በዚሁ ጽሑፍ ላይ በሚቀጥሉት አንዳንድ ክፍሎች ተመልሰን እንደምናየው ሁሉ፡ ወያኔ ኤርትራን በሚመለከት በተደጋጋሚ የወሰዱትና አሁንም ገና እየወሰዱት ያሉት እርምጃዎች ከትግራይ ትግርኚ ዕቅድ ጋር የተያያዘ ነው።

የዚህን ዕቅድ ሂደት ወያኔ ብቻውን ተግባራዊ ለማድረግ እንደማይችል ግልጽ ነው። የታለመው ዕቅድ ግቡ እንዲመታ ከተፈለገ ወያኔ የግድ ኤርትራዊ ሸሪክ ያስፈልገዋል። በኤርትራ በኩል፡ የወያኔ ሸሪክ በመሆን በሂደቱ ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት የሚችል ኃይል ተወደደም ተጠላም ኢሳያስ አፈወርቂ ነው። ብዙዎች ለተለያየ አላማና ፍላጎት የኤርትራን ትግል ሲከታተሉ የቆዩት ታዛቢዎች፡ የኢሳያስና የወያኔን ዝምድና በዚሁ በትግራይ-ትግርኚ ዕቅድ ዙሪያ የተመሰረተ መሆኑን ያመላክታሉ።

## ፫፣ ኢሳያስ አፍወርቂ፣ ልዕለ-አምባገነን

በሀገራችን ላይ የተንሰራፋው ገሃነማዊ ሁኔታ ከኢሳያስ አፍወርቂ ህልውና ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ያለው ሁኔታ በድምር ሲታይ ኢሳያስ ማለት የኤርትራ ሞት ማለት ሆኖ ይገኛል። ይህ ሰው በአሁኑ ጊዜ ኤርትራ ውስጥ የሚታወቀው እንደ አንድ የተረገመ ፍጥረት ነው። በአብዛኛው የዓለም ዙሪያ የሚገኙ፡ የአውሬ ተግባራቱንና ቅጥ አልቦ አመለካከቱን የተከታተሉና በውል ያስተዋሉ ጋዜጠኞችና ሌሎች ታዛቢዎች ኢሳያስን እንደ አንድ ያልተለመደ ነገር ወይም ስግንጥር አድርገው ነው የሚመለከቱት።

*"ኢሳያስ አንድ ግለ ሰብ ነው፤ ስለእሱ ብዙ መናገር ወይም ለእሱ ይህን ያህል ትኩረት መስጠት አስፈላጊ አይደለም "* የሚሉ እንዳሉ እናውቃለን። የዚህ ዓይነት አስተያየት የሚያስተጋቡ ሰዎች - እውነት ከልባቸው ከሆነ - በጣም የዋሆች ናቸው። ይህ ሰው እንደ ግለሰብ ሀገራችንን ተቆጣጥሮ የበታች ሽሪኮቹንና ታዛዦቹን እያሰማራ፡ ሕብረተ ሰባችንን ሲገድል የነበረና አሁንም ሲገድል የሚገኝ ነው። በእርግጠኝነት ለመናገር፡ ኢሳያስን ሳይጠቀሱና ሳይገልጹ የኤርትራን ተጨባጭ የሞት ሁኔታ መተንተን አይቻልም።

ግለ ሰቦች በታሪክ ሚና አላቸው - ገንቢ ይሁን አፍራሽ። ይህ ሲባል ግን የግለ ሰቦች ሚና በሕብረተ ሰቡ የታሪክ ሂደትና ተጨባጭ ሁኔታ የሚገዛ መሆኑን ሊሰመርበት ይገባል። አንድ ግለ ሰብ፡ በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚና ተጨባጭ ሁኔታ መሆን የሚቻለውን ክንዋኔ፡ እርሱን በሚያነሳሳው ጥቅም መሰረት፡ ሊያዘገየው ወይም ሊያቀላጥፈው ይችላል። በቅርቡ ታሪካችን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና የነበራቸውና አሁንም ያላቸው ግለ ሰቦች አሉ፤ ከነሱ አንዱም ኢሳያስ አፍወርቂ ነው።

ኢሳያስ ከትግራይ የትውልድ ሀረግ ቢኖረውም ቅሉ በኤርትራ ተወልዶ ያደገ ስለሆነ ኤርትራዊ ዜጋ ነው። ስለዚህም የኢሳያስን ትውልዳዊ ማንነት ማንሳቱ ወይም መተንተኑ አስፈላጊ ባልሆነ ነበር። ነገር ግን ኢሳያስ ራሱ የመረጠው አላማና እያራመደው የቆየና አሁንም እየተገበረው ያለው ጸረ ሃገራዊ ፖሊሲ፡ የትግራይ ትውልደ ሐረጉን እንደ አንድ መስፈርት ወይም መገለጫ ወስደን ልንጠቅሰው ተገድደናል።

በአሁኑ ጊዜ ዜጎቻችን ኢሳያስን የሚያነሱትና የሚያወሱት በተለያየ ስም ነው። አምባገነን" ዲክታተር" ፈላጭ-ቆራጭ" ወዘተ ብለን እንጠረዋለን። ኢሳያስን ለመግለጽ ሊመጥን የሚችል ያ "ታይራንት - tyrant — " የሚለው የእንግሊዝኛ ስነ ቃል ነው። ይህ ቃል "ሥልጣን ብኃይል ነጥቆ ወይም በማታለልና በማጭበርበር ጠቅልሎ በመያዝ.... ጭቆናና ገደብ አልባ አፈና" የሚያደርስን መሪ የሚገልጽ ነው[25]። ሥልጣን በአንድ ግለ ሰብ እጅ የተጠቀለለ ነው። "ፍትሕና የሕግ የበላይነት" የሚባል ነገር የለም[26]። በተለያዩ የእንግሊዝኛ-ትግርኛ መዝገበ-ቃላት tyrant "አምባገነን" የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። እውነቱን ለመናገር ግን ኢሳያስ አምባገነን በማለት ብቻ የሚታለፍ አይደለም። ኢሳያስ ገደብ አልባ የሆነ ጭካኔ ያለውና የሚፈጽም ልዕለ-አምባገነን ነው።

ታዋቂው የጥንታዊት ግሪክ ፈላስፋ አሪስቶትልና እንዲሁም ሌሎች ተመራማሪዎች፡ ስለ አንድ የላቀና ገደብ አልባ የሆነ አምባገነን ጸባያትና ባህሪያት ያደረጉት ትእዝብት በአሁኑ ጊዜ ያሉትን ጨካኝ ገዢዎችንም በትክክል የሚገልጽ ነው። እነ አሪስቶትል የላቁ

25. Rod Hague & Martin Harrop, p. 32
26. Roger Scruton, p. 473

አምባገነኖችን በሚመለከት ካስቀመጡት ጸባያት ውስጥ የሚከተለው ይግኘበታል። አንድ የላቀ ወይም የከፋ አምባገነን በራሱ እምነት እሱ ከሁሉም በላይ ነው። ከርሱ ጋር ለመወዳደር የሚቃጣ ሊኖር አይፈቀድም። በራሳቸው የሚተማመኑ! በማንነታቸው የሚኮሩ! ወኔና ስብእና ያላቸው ምርጥ ዜጎችን ይጠላል። ይፈራቸዋልም። ሰለሆነም ለሁሉም በጥርጣሬ ዓይን በማየት ጫና ለማድረግ ይሯሯጣል። ሌላ ቀርቶ የቅርብ ጓደኞቹና ታማኞቹ የሆኑት ሰዎችንም ጭምር አያምናቸውም፤ ስልጣኑ የሚጠበቀው በነሱ መሆኑ ቢታመንም። እንዲያውም በየጊዜው የጥቃቱ ሰለባ ከሚሆኑት ዜጎች የገዛ ጓደኞቹ ናቸው። ይህንን ጥቃት የሚፈጽምበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ከማንም በላይ እኔን ለመፈታተንና ለመጣል ኃይልና ችሎታ ያላቸው፡ እነርሱ ናቸው ብሎ ሰለሚያምን ነው[27]። በሀገሪቱ ላይ ጠንካራ የአፈና መዋቅሮችንና መረቦችን በመዘርጋት በዜጎች ላይ ጥብቅ ስለላና ክትትል ያዘወትራል። በህዝቡ ዘንድ ፍርሃትና ሽብር እንዲነግሱ ያደርጋል፤ በህዝቡ መካከል ጥላቻ፡ መናቆርና ጥርጣሬ እንዲኖር ያደርጋል[28]፤ ህዝቡ ተወያይቶ በስልጣኑ ላይ አመጽ እንዳይፈጽምና ሌላ ነገር እንዳያስብ ሆን ብሎ ማለቂያ የሌለው ፕሮጀክት በመፍጠር ባገዛዙ አጀንዳ እንዲጠመድ ያደርጋል። የተለያየ ግብር በመጫንም ሆነ ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ህዝቡን ያደኸያል፤ ከሁሉም በላይ ጎጂ የሆነው ደግሞ ለአንድ አምባገነን ጦርነት መጫር የሚያስደስተውና የሚያረካው መሆኑ ነው፤ ለዚሁ ምክንያቶች ከሆኑት አንዱ በውጊያ ጊዜ ህዝቡ የሃያል መሪ አስፈላጊነት የሚታየው መሆኑን ነው[29]። አምባገነን የሚሰራው ስራ ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም ብሎ ሳይሆን ለራሱ ጥቅም ነው፤ አልፎ አልፎ ግን እግረ መንገዱን ለህዝብም የሚያገለግሉ ስራዎች እንዲከናወኑ ሲያደርግ ይታያል። ይህ የሚሆነው ግን ስራዎቹ እንዳጋጣሚ በዚያን ወቅት ለራሱም ይበልጥ ጠቃሚና አስፈላጊ ስለሆኑ ነው[30]።

ከላይ ከተጠቀሱት ልዕለ-አምባገነንን የሚመለከቱ ባህሪያትና ጸባያት ብዙዎቹ በማያወላውል መልኩ በኢሳያስ አፍወርቂ ይገኛሉ። ኢሳያስ ስለራሱ ከመጠን በላይ ከፍተኛ ግምት ነው ያለው። በራሱ አመለካከት እሱን የሚመጣጠንና የሚወዳደር ቀርቶ አጠገቡም የሚደርስ ሰው የለም፤ እንዲያውም እርሱ ከኤርትራ ራስዋ በላይ ነው![31]። ነጻ ምሁራንንና: ሌሎች ዓቅምና ወኔ ያላቸውን ሰዎች ሁሉ አምርሮ ይፈራል፤ ይጠላቸዋልም። ከዚህ ዓይነቱ የአውሬ ባህሪያትና ጸባያት በመነሳት እንደነዚህ የመሳሰሉ ጥሩ ራእይና እውቀት ያላቸው ምርጥ ኤርትራውያን ከ70ዎቹ መጀመርያ አንስቶ በብዛት ገድሏል[32]። ከራሱ በስተቀር የሚያምነው ሰው የለውም። እንደነዚያ ጂ-15 የሚባሉ እስረኞችን የመሳሰሉና ሌሎች የረጅም ዓመታት ጓደኞቹንና የትግል ጓዶቹን በብዛት በስውር አጥቅተዋል፤ ገድሏልም። ሌላውን ትተን ለምሳሌ ያህል ናይዝጊ ክፍሉ የሚባል ለስንት ዓመታት በቅርብ ሲያገለግለው የነበረ ሰው በለንደን ህይወቱ ካለፈ በኋላ አስካሬኑን እንኳን ወደ ኤርትራ

---

27. የአሪስቶትል አስተያየቶች በ "DianaHsieh" ድርሰት ይገኛሉ።
28. ዝኒ ከማሁ
29. ዝኒ ከማሁ
30. Hank Edmondson
31. ጴጥሮስ ሰሎሞን ለዳን ኮነል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነሐሴ 23, 2001 በሰጠው ቃለ-መጠይቅ ላይ ይህንን ሓቅ ጠቅሶታል። ጴጥሮስ አለ፣ "Our dear president. Now, he says that Eritrea is less than the President.The President is more than Eritrea".(DanConnel: ገጽ135) ይህ ማለት "ክቡር ፕረዚደንታችን፣ አሁንማ ኤርትራ ከፕረዚደንቱ ታንሳለች ይላል፣ ይህ ማለትም ፕረዚደንቱ ከኤርትራ ይበልጣል ወይም ይተልቃል" ማለት ነው።
32. ኢሳያስ በምሁራን ላይ ከፈጸማቸው አንዳንድ ግፎች በተስፋይ ተምነዎ መጽሐፍ ተገልጸዋል። (ተስፋይ ተምነዎ፤ 2013)

እንዳይገባ በመከልከል ለማመኑ የሚያዳግት ኢሰብአዊነት አንጸባርቋል። በሀገራችን ውስጥ የተተበተበ የስለላ መረብ በመዘርጋት ህዝቡን - በቤተሰብ ደረጃ እንኳን ሳይቀር - እርስ በርሱ እንዳይተማመን አድርጓል[33] ህዝቡ ስለ ሀገሩ ጉዳይ ተወያይቶ መፈትሔ ለማግኘት መንቀሳቀስ እንዳይችልና ጥያቄ እንዳያነሳ ማለቂያ የሌላቸውን የተለያዩ ዓይነት ፕሮጀክቶች አሸክሞታል፤ ለምሳሌ ወጣቶቹን ወደነዊዓና ምዕንጢር ሲያጉራቸው፣ ትላልቆችን ደግሞ ያለ ክፍያ በወታደራዊና ሌሎች አገልግሎት እንዲሰማሩ አድርጓል። በሀገር ውስጥና በውጭ ዓለም የሚገኙ ኤርትራውያንንም የተለያዩ የግብር ዓይነቶችን አስገድዶ በማስከፈል ለድህነት ዳርጓል። ከዚህም አልፎ ኢሳያስ አስፈላጊ ያልሆኑትን ጦርነቶች እየጫረ ህዝባችንን አስጨርሷል፤ አጎራባች ሀገሮችን አንድ ባንድ እያጠቃ ወጣቶቹን ወደ ጦርነት ይማግዳቿል። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ሀገራችን እፍረት ተከናንባ ህዝባችን ደግሞ የከፋ ህይወት እየገፋ መገኘቱ ነው።

ይህ ሁሉ ጣጣ ባይኖር ኖሮ ኤርትራ የት መድረስ ትችል እንደነበር ቆም ብለን ስናስታውስ፣ ኢሳያስ ከሞላ ጎደል ፈጽሞ ለህዝብ የሚጠቅም ነገር የሰራው ስራ የለም ማለት ይቻላል። በትጥቅ ትግሉ ዘመን በሳሕል በረሃዎች መንገዶች የተሰሩት የሕክምና አገልግሎቶችም ይሰጡ የነበሩት ኢሳያስ ወደ ስልጣን እንዲመጣ አስፈላጊነት ስለ ነበራቸው ነው። "ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ የሰለጠነና ተራማጅ ድርጅት ነው፣ ኢሳያስ ደግሞ "አንዱ ምርጥና አስተዋይ መሪ ነው" ተብሎ እንዲመለክ ነበር ዋናው አላማ። በኢሳያስ የምትመራ "የዛሬይቱ ነጻ ኤርትራ" ሕክምና፡ ይሁን ሌሎች ለህይወት መሰረታዊ አስፈላጊነት ያላቸው አገልግሎቶች የጎደሉባት የወደቀች ሀገር መሆንዋ እውነትም ቀደም ሲል በሳሕል የነበረው ዕድገት አላማው ኢሳያስን ወደ ስልጣን ለማውጣት ብቻ እንደነበር የሚያሳይ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው።

እነዚህ እውነታዎችን ግምት ውስጥ ስናስገባ የኢሳያስ አፍወርቂ በሕብረተ ሰባችን መፈጠርና ህላዌ - እንደ መጥፎ አጋጣሚ - ቂልፍ ነገር ሆኖ እናገኘዋለን።

## ፩፡ የኤርትራ ደካማነት እንደ ፖለቲካ ማህበረ-ሰብ

ኢሳያስ በትጥቅ ትግሉ ሂደት ላይ ለማደግ፡ ብሎም በየጊዜው የተለያዩ ዕቅዶቹንም ለማሳካት የቻለውና አሁንም ለማስፈጸም የሚችለው ያለው፣ ኤርትራን ተነቃፊ (ወይም ለአደጋ እንድትጋለጥ) የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎችን በመጠቀም ነው። የተጠቀመባቸው ሁሉንም ታሳቢዎችንና አጋጣሚዎችን በዝርዝር ማስቀመጡ አስፈላጊና ለግንዛቢያችን የሚረዳ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። ሆኖም በዚሁ መልእክት የምርምር ጥረታችን መሰረታዊ በሆኑት ጥቂቶች ነጥቦችና ታሳቢዎች የተወሰነ ይሆናል።

ሀ.) ከሁሉም በፊት ጎልቶ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የኤርትራ ሀገራዊነት ደካማ መሆኑ ነው። ሃገራዊነት ሲባል በአንድ ሕብረተ-ሰብ ውስጥ በሆነ ታሪካዊ ወቅት ብቅ የሚል ክስተት አይደለም። ሀገራዊነት በአንድ አካባቢ የሚኖር ሕብረተ ሰብ በመካከሉ የኢኮኖሚና የታህታይ መዋቅር ግንኙነቶች በጥብቅ ሲወሃሃዱ በዝግመት የሚነሳ ዕድገት ነው። በአጭሩ ሃገራዊነት፣ የሕብረተ-ሰቡ ውስጣዊ ዝምድና ታሪካዊ ሂደት

33. ስለ የህዝባዊ ግንባር የስለላ ክፍል ተግባራትና እንቅስቃሴ በነባር ታጋይ የማነ ተክለገርግስ የቀረበውን ሰፊ ዘገባ በአሰና.ኮም (Assena.com) ማየት ይቻላል።

የወለደው የጋራ ኢኮኖሚያዊ ህይወት በጋራ የማንነት ስሜት ታጅቦ ሲገኝ እውን የሚሆን ሁኔታ ነው።

ካሁን በፊት ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው ሁሉ ኤርትራ በራስዋ ውስጣዊ ታሪካዊ ሂደት አልፋ በረጅም ጉዞ ተሰባስባ የተቀረጸች ሀገር አይደለችም። የኢጣሊያ የባዕድ መንግስት የተለያዩ ወገኖችዋን ተቆጣጥሮና አሰባስቦ ኤርትራ በሚል ስም የፈጠራትና ያቆማት ጂኦግራፊያዊ አካል ናት። የዚህን ዓይነቱ የሀገር አፈጣጠርና አመጣጥ ሂደት ኤርትራን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። በቅኝ ግዛት ተይዘው የነበሩት የተለያዩ የአፍሪቃና ሌሎች ሶስተኛ ዓለም ሀገሮችም የተሰባሰቡበትና የተቀረጹበት ታሪካዊ ሂደት ከሀገራችን ጋር አንድ ነው። ስለዚህ የኤርትራንም ሆነ የሌሎቹን ሶስተኛ ዓለም ሀገሮች ሀገራዊነት የረጋ ታሪካዊ መሰረት ያለው አይደለም። ማንኛውም ሶስተኛ ዓለም ሀገር አንድ ጠላት ሊያፈርሳት ከተነሳ በቀላሉ ልትፈራረስ ትችላለች። ስለዚህም የኤርትራና በተመሳሳይ ታሪካዊ ሂደት የመጡ ሶስተኛ ዓለም ሀገሮች ሀገራዊነት ደካማ በመሆኑ ብዙ እንክብካቤና መከላከያ የሚያስፈልገው ነው።

የኤርትራ ሀገራዊነት ደልዳላ መሰረት የሌለው መሆን ከሁሉም በላይ የጠቀመው ኢሳያስን ነው። ኢሳያስ በትጥቅ ትግሉ ወቅት አስቀድሞ በሰፊው ያሰራጨው ከፋፋይ የሆነ ቅስቀሳ በተወሰነ የሕብረተ ሰባችን ክፍል ላይ ተጽዕኖ ፈጠረ። ድሮውንም ቢሆን የጸናና የጠነከረ ኤርትራዊ ሀገራዊነት ያልነበራቸው ሰራዊቱንና ሌሎች የድርጅቱን ተከታዮች በቅስቀሳው በቀላሉ ከፋኝ አሳመናቸው፤ አንዳንዶቹንማ ጸረ ህዝባቸውና ሀገራዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ጸረ የራሳቸው ጥቅምም እንዲሰለፉና እንዲሰማሩ አድርጓቿል። ዛሬም ቢሆን፡ ሀገር እየጠፋች መሆንዋን እያዩ የቅስቀሳው ሰለባ በመሆን ኢሳያስን የሚደግፉ ኤርትራውያን አሉ።

በተ.ሓ..ኤ (ጀብሃ) ውስጥም ደካማ ሀገራዊነት መገለጫው የሆነ ችግር ነበረ። እነዚያ ችግሮችንም ኢሳያስ በተለያዩ መንገዶች በሚገባ ተጠቅሞባቿል። ይህንን ነጥብ በሚመለከት ወደ ኋላ ላይ እመለስበታለሁ።

**ለ)** ሀገራዊነቱ ደካማ በሆነ ሕብረተ ሰብ የሀገሪቱን ህልውናና ግስጋሴ ጠብቆ ወደፊት ለመግፋት ትልቅ ሚና መጫወት ከሚችሉ የማሕብረሰቡ ክፍል ውስጥ ዋናው ያ የሰለጠነው አካል (Elite) ሲሆን በተለይም የተማረው ክፍል ነው። በሶስተኛ ዓለም ሀገሮች የተማረው ክፍል ሀገራዊነትም ከተራው ህዝብ ያደገ ቢሆንም ደረጃውና ጥንካሬው ግን እንደ በምዕራቡ ዓለም ሀገሮች ያለው ኤሊት አይደለም። ኤርትራ በዕድገቱ ብዙም የሚያስመካ የምሁር ክፍል ወይም ሌላ የሰለጠነ ቡድን የላትም፤ አሉ ከሚባሉት ድሮውም ቢሆን ሀገራዊነታቸው ያላደገ የነበረ ምሁራን ደግሞ አብዛኛዎቹ፡ በተለያዩ ምክንያቶች፡ በፖለቲካው መስክ ሃላፊነታቸውን አልተወጡም።

ኢሳያስ የኤርትራ ምሁራንን ደካማነት ተጠቀመበት። ከ70ዎቹ አንስቶ በራሱ ድርጅት (ሻዕቢያ) እና በተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ (ተ.ሓ.ኤ) ውስጥ የነበሩትን ሀቀኛ ሀገራዊነትና አርበኝነት የነበራቸው አርቆ አሳቢና ልበ-ሙሉ ምሁራን አጥፍቷቸዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ እነዚያን ወኔም ሆነ ሕልና የሌላቸው ምሁራን ይሉኝታ በሌለው አኳሃን ተጠቅሞባቿል[34]። እንደነዚህ የመሳሰሉት አድር-ባይ ምሁራንን በሀገር

34. ዶ/ር አብርሃም ጳውሎስ ህዝባዊ ግንባር ውስጥ የቅን ምሁራኑ እጣንና አልምጥ የሆኑት ነጋዴ ምሁራን ሚናን በተመለከተ የሚከተለውን ትክክለኛ መግለጫ ይሰጣል።

ውስጥም ሆነ በውጭ በማሰማራት ከአንዳንድ የወያኔ መሪዎች ጋር የነበረውንና ያለውን እኩይ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ለማገልገል ሲባል የኤርትራ ትግል እንዲጠለፍ አድርጓል።

ሐ) ብሄረ-ሰባዊ ልዩነቶች በራሳቸው - ማለት በባህሪያቸው - አሉታዊ አይደሉም። የኤርትራ ሕብረተ-ሰብ በድምሩ ሲታይ በሁለት ዓበይት ሃይማኖታዊ ማህበረ-ሰቦችና በዘጠኝ ብሄረ-ሰቦች የቆመ ነው። ይህ አቋቋም በራሱ መሰረታዊ ችግር የሌለው ቢሆንም፡ በኤርትራ ላፍራሽና ጸረ-ሃገራዊ ዕቅድ ማስፈጸሚያ ሆኗል። ኢሳያስ ከጅምሩ ሲነሳ እነዚህ ልዩነቶችን እንደ መሳሪያ አድርጎ የተጠቀመባቸው መሆኑ በሚገባ መታወስ አለበት። ፍጹም የሱ ታዛገሮች የነበሩትን የህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ህግሓኤ) ታጋዮች: ሀገራዊ ፓለቲካዊ ድርጅት የሆነውን "ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ (ተሓኤ)" "ዓማ" እያሉ በመጥራት: እስላማዊና ባዕዳዊ ድርጅት አድርገው በማየት: በመጨረሻም እንደ ድርጅት ከምድረ ገጽ ማለት ከኤርትራ መሬት መጥፋት አለበት እያሉ በጥላቻ ለመምታት እንዲሰማሩ አድርጓል። ይህ ዓይነቱ ሰይጣናዊ ተግባር በዚህ ብቻ አላበቃም። በሀገር ደረጃ ስልጣን ከያዘ በኋላም ሀገራዊያን የፓለቲካ ተቃዋሚዎችን ለመምታት "ጂሃዳውያን" "እስላማዊ አክራሪነት"ወዘተ እያለ ስም በማጥፋት የአምባገነናዊ ስርዓቱን ህልውና ለማቆየት እንደ አመክንዮ ተጠቅሞበታል። አሁንም ገና እያመካኘ ይገኛል።

መ) ከዚሁ ጋር በተሳሰረ መልኩ ሲታይ: ኤርትራ በደቡብ በኩል የኢትዮጵያ አካል ከሆነቺውና ህዝብዋ ትግርኛ ተናጋሪ ከሆነው የትግራይ ክፍለ ሀገር ጋር የምትዋሰን መሆንዋ አሁን ባለው የፓለቲካ ሁኔታ ትልቅ መሰናክል ነው። የትግራይ ህዝብ በኤትኒካዊ ማንነቱ: በባህልና በሃይማኖት ከደገኛው (ከበሳ) ትግርኛ ተናጋሪ የኤርትራ ህዝብ ጋር አንድ ነው። እንደ ደንቡ ከሆነ ይህ ጉርብትናና ተዛምዶ ለራሱ ትልቅ ጸጋ ሊሆን የሚችል ነው። ይሁን እንጂ፡ የህዝብ ባላንጣ የሆኑት "ኢሳያስና ወያኔ" በሚያራምዱት ፖለቲካ ምክንያት፡ ለኛ ለኤርትራውያን ጸጋ ሳይሆን የማያባራ ችግር ሆኖብን ይገኛል። ይህቺ ትግራይ የምትባለው ክፍለ ሀገር፡ በኢትዮጵያ ለስልጣን የሚፎካከር ወያኔ የሚባል ድርጅት ወልዳለች። ይህ ዓይነቱ ምኞት ወይም ፉክክር ታሪካዊ መነሻና መግለጫ ስላለው ብዙም የሚያስገርም አይደለም። ሆኖም፡ ወያኔ ወይም አመዛኙ የአመራሩ ክፍል፡ በኢትዮጵያ ስልጣን ለመቆጣጠር ካልተሳካለት ለብቻው ተገንጥሎ ነጻ ሪፓብሊክ ለመመስረት ዕቅድ ያለው ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ

---

".ሐያላኑና ጀግኖቹ ምሁራን ኤርትራውያን፣ በትጥቅ ትግሉ ሜዳ ከ70ዎቹ ጀምረው በህዝባዊ ግንባር ውስጥ ሆነው ይታገሉ የነበሩት በኢሳያስ ተገድሏል። በውጭ ዓለም እየኖሩ ከህዝባዊ ግንባር ጎን ተሰልፈው ይታገሉ የነበሩት ምሁራን ኤርትራውያን በታጋይ ምሁራን ወንድሞቻቸው ላይ ይደርስ የነበረውን አሰቃቂ ግድያንና ግፍን ሲቃወሙ አልታዩም። እንዲያውም በአንጻሩ ለኢሳያስ ዝናና ክብር ነበር እስካሁን ድረስ የሚያቀነቅኑና የሚወድሱ።"...

"......ምሁራን ኤርትራውያን በተለይም ከህዝባዊ ግንባር ጋር ተሰልፈው ሲታገሉ የነበሩ ከነውረኛ፣ ትምክሕተኛና ከፋፋይ የሆነ የኢሳያስ አፍወርቂ ትምህርት ሳይላቀቁ ህዝባቸው በአለንጋ እየተገረፈ ሳለ እስካሁን ድረስ በአሜሪካና በአውራà "መንግስታችን" እያሉ ዳንካራ ሲመቱ መታየታቸው አሳፋሪ የሆነ ታሪክ ነው። ስለዚህ ምሁራን ሕልናቸውን ልዕለ አምባገነን በሆነው ኢሳያስ ቁጥጥር ስር እንዲገባና በንብረትነት እንዲያዝ በመፍቀድ ... በከበሮ፡ማሲንቆና ዳንኪራ መጓዛቸው አስደማሚ ነገር ነው።" (አብርሃም ጳውሎስ፡ ገጽ .525)

መዘዙ ኤርትራን የሚበታትን ነው። ዕቅዱ ታሪካዊ መነሻም ሆነ በቂ የሆነ አሳማኝ ምክንያቶች ያለው ስላልሆነ፡ እውነትም የሚያስደምም ነው። ኢሳያስ አፍወርቂ፡ ለራሱ በአመዛኙ ትውልደ ትግራይ ያለው ስለሆነ ወያኔን የሚያነሳሳው ውስጣዊ ግፊትን (ወይም ምኞትን) የሚጋራ ነው። ኢሳያስ ከድሮ ጀምሮ አስገራሚና አስደማሚ በሆነው ኤርትራን የሚበታትን ጽንሰ ሀሳብም የተወሰኑ የወያኔ መሪዎች ሸሪክ መሆኑ ያለፈው ታሪኩና ያሁኑ ጉዞው ይመሰክራሉ።

የወያኔ አካሄድ መመሪያ "የብሄር ብሄረ ሰብ ፖለቲካ" (politics of ethnicity) የሚል መርህ ወይም እምነት (ዶክትሪን) ነው። ይህ በመሆኑም የከበሳ (ደጋማው) ኤርትራ ጉርብትና በወያኔ ቁጥጥር ስር ካለቺው ትግራይ መሆኑ በተግባር ትልቅ ችግር ሆኖ ይገኛል። ኢሳያስ አፍወርቂም በበኩሉ ይህንን ኤትኒካዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታ ተጠቅሞ በወቅቱ በታጋዮች ዘንድ የነበረውን ኋላቀርነት በቀላሉ ሊገለገልበት ችሏል። በመጨረሻም፡ ታጋዮቹ ትንሽ ጭንቀት እንኳን ሳይሰማቸው ከወያኔ ጋር አብረው ኤርትራውያን ወንድሞቻቸውን እንዲጨፈጭፉ አድርጓል።

ሰ.) የኤርትራ ጀኦግራፊያዊ አቀማመጥ በምዕራባዊ የቀይ ባህር ዳርቻ መሆኑ ወሳኝ ሁኔታ ነው። ይህ አቀማመጥ ለብዙ ነገር ቁልፍ (ስትራተጂያዊ) ስለሆነ የሩቅና የቅርብ የባዕድ መንግስታት ሊቆጣጠሩት የሚፈልጉት ነው። እንዲያውም አሜሪካ: እስራኤልና ሌሎች የምዕራብ ዓለም መንግስታት፡ የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከት የወሰዱት - አሁንም የሚተገብሩት - ፖሊሲ ይህንን ስትራተጂያዊ አቀማመጥ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ኢሳያስም ከድሮ ጀምሮ የራሱን ዕቅድ ለማሳካት የቻለው ከምዕራቡ ዓለም ሓይሎችና ሸሪኮቻቸው ከሆኑት የመሃከለኛ ምስራቅ መንግስታት እርዳታ ነው። ይህንን እርዳታ ሊያስገኙለት ከቻሉ ትልልቅ ነገሮች አንዱ የኤርትራ አቀማመጥ በቀይ ባህር ዳርቻ መሆኑ ነው።

ኢሳያስ ከላይ ባጭሩ የተገለጹትን የተለያዩ ድክመቶችና ሁኔታዎች በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅሞባቿል። ይህን ለማድረግ የቻለም ልዕለ-አምባገነን በመሆኑ ነው ለማለት የሚቻልበት ነጥብ አለ። እንዴት? አሁን በኤርትራ ላይ ያለው መላቅጡን ያጣ ጋጥወጥ አስተዳደር በማየት ብዙ ሰዎች "ህዝባዊ ግንባር ድሮ ነው በጽናት የተቀናጀና አመርቂ ድርጅት የነበረ እንጂ አሁንማ ስርዓትና ማዕዝን የሌለው ሆኗል" ይላሉ። በኔ አመለካከት ይህ አባባል የዋህነት ነው። ኢሳያስ በሜዳ ጊዜ ሲተገብረው የነበረወን ዕቅድ ነው አሁንም እያራመደ ያለው። ያረማመዱ መልክና ይዘት ግን ባሁኑ - በ"ነጻነት" - ጊዜ በሜዳ ዘመን ከነበረው ይለያል።

ቻርለስ ፐጉይ የተባለ በ19-20 ክፍለ-ዘመን ይኖር የነበረ ፈረንሳዊ ጸሐፊ "tyranny is always better organized than liberty" ብሎ የገለጸው ነጥብ አለ። "ልዕለ አምባገነንነት ሁል ግዜ ከነጻነት በበለጠ የተደራጀ ነው" ማለት ነው። ይህ ነጥብ ኤርትራውያን ደህና አድርገው ሊያስተውሉበት የሚገባ ጥልቅ ቁም ነገር ያዘለ አነጋገር ነው። በትጥቅ ትግሉ ጊዜም ሆነ ከ"ነጻነት" በኋላ፡ የኢሳያስ አካሄድ በጣም በተደራጀ አገባብ ወደ አንድ የረጅም ጊዜ አላማ በሚያተኩር መልኩ የተቃኘ ነው። የረጅም ጊዜ አላማው ደግሞ እሱ መንግስታዊ ስልጣኑን እንደጨበጠ ኤርትራን ሆን ብሎ አዳክሞ (አመንምኖ) ከሰነጣጠቀ በኋላ ሂዶ ሂዶ በሌላ አካል እንድትተካ ለማድረግ ነው። በትጥቅ ትግሉ ዘመን የኢሳያስ ጥረት ለረጅም ጊዜ አላማው የሚሆን መንገድ መጥረግና ማመቻቸት ነው የነበረው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሜዳውን ለብቻው መያዝ ነበረበት። ሜዳውን ለብቻው ጠቅልሎ ለመያዝ ደግሞ ጀብሃን ማጥፋት ነበረበት። ጀብሃን የማጥፋት እንቅስቃሴ እውነትነት:

አግባብነትና በቂ ምክንያታዊነት ያለው መሆኑን ለማስመሰል ሲባል ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ በሁሉም መስክ ከጀብሃ የበለጠ መስሎ መታየት ነበረበት። በመሰረቱም፡ ጀብሃ መዳከም ነበረበት። ስለዚህ የጀብሃን ዕቅዶች ማደናቀፍ፣ ከፍተኛና ጠንካራ የሆኑትን የጀብሃ የካድረ አባላትን ማፈንና መግደል፣ ለስምረትና ለትብብር የሚደረገውን እንቅስቃሴና ተነሳሽነት ማጨናገፍና አሻፈረኝ ማለት፣ ከጀብሃ ጋር ነጋ ጠባ ዉጊያ በመክፈት ዕረፍትን ማሳጣት: ወዘተ የመሳሰሉትን አደናቃፊና አውዳሚ ተግባራት መፈጸም የኢሳያስን የረጅም ጊዜ አላማ ለማሳከት አስፈላጊ ነበሩ። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ሰፊው የድርጅቱ ታጋዮችን: ካድሬዎችንና: የይስሙላ መሪዎችን በጥብቅ የሚቆጣጠር: ከብረት የጠነከረ አደረጃጀት: ያስፈልገው ነበር፤ በእርግጥም ነበረው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ በተጨማሪ መታወቅ ያለበት ነገር አለ። እሱም በራሱ በህዝባዊ ግንባር ውስጥ በኢሳያስና በሰፊው ታጋዮች መካከል የአላማ ልዩነት እንደነበረ ነው። ታጋዮቹ ለኤርትራ ነጻነት እየታገልን ነው የሚል እምነት ነበራቸው። የኢሳያስ አላማ ግን የኤርትራ ነጻነትና የወደፊት ህልውና ሳይሆን ዞሮ ዞሮ ኤርትራን መበታተንና በሌላ አካል መተካት ነው የነበረው። ኢሳያስ በእምነት የያዘውን ስውር አጀንዳ ደብቆ የኤርትራ ነጻነት የሚል መፈክርና ካርድ እንደ ሽፋን ወይም የማታለያ ዘዴ ይጠቀምበት ነበር። ውስጣዊ ልዩነቱንና ጉዱን ጠንቅቆ የሚያውቀው ኢሳያስ ብቻ ነበር፤ ሰፊው ታጋይ እውቀትም ሆነ ግምት አልነበረውም። ሰፊው የህዝባዊ ግንባር ታጋይ ይህንን ልዩነት ለማወቅ እንዳይችል ኢሳያስ የጠበቀ ቁጥጥር ማድረግ ነበረበት፤ አደረገም። ለዚህም ነው ታጋዮቹ ከተራ ዜጎችና ከጀብሃ ታጋዮች ጋርስ ይቅር እርስ በርሳቸውም ለመነጋገር  የማይፈቀድላቸው የነበረው።

በአሁኑ ጊዜ የኢሳያስ መንግስት በኤርትራ ውስጥ እያካሄደ ያለው አፍራሽ እንቅስቃሴ ከውጭ ላይ ላዩን ብቻ ሲታይ ፈጽሞ በውል ያልተደራጀ! የተንዛዛና አዝጋሚ መስሎ ይታያል። ሀቁ ግን በተቃራኒው ነው። የሁኑ እንቅስቃሴ የተደራጀና ንቁ አካሄድ ነው። አካሄዱም ልክ በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የነበረ ዓይነት “የትግራይ ትግርኚ” አላማ ማስፈጸሚያ ነው። የኢሳያስ ስልት ባሁኑ ጊዜ ምንድን ነው? ወጣም ወረደም የኢሳያስ ስልት ተጠቃልሎ ሲታይ፡ ኤርትራ በአፍሪቃ ቀንድ ቀጠናም ሆነ በዓለም ላይ የተጠላችና የማትከበር ሀገር እንድትሆንና፡ ህዝብዋም በሀገሩ መኩራት ተስኖት፡ ማንኛውንም ጸረ ሃገራዊ ዕቅድ ያላንዳች ተቃውሞ እንዲቀበል ማድረግ ነው።

ኢሳያስ የሚፈልገው ነገር ይህ እስከሆነ ድረስ በኤርትራ ውስጥ አሳረ-መከራ እየከረረና እየተባባሰ መሄድ አለበት። ይህ ማለት የመብራት: የውሃ: የምግብ: ወዘተ እጥረት እንዲኖር፣ ስራም ሆነ ትምህርት እንዲታጣ፣ ሕገ ወጥነትና ፍትሕ አልባነት እንዲነግስ ሆኖ፡ ወጣቱ ብድግ ብሎ ሀገሩን ለቆ በመሄድ ደብዛው መጥፋት አለበት ማለት ነው። ስለዚህ፡ በኤርትራ ውስጥ ያለው ጋጥወጥ ሁኔታ ሆን ተብሎ የተጠነጠነ፡ የተስተጋባና የተደራጀ ጉዞ ነው። የሚዘገንነው፡ ኩላሊት የመቀማትን ጉዳይ በሚመለከት ያለው - አስመራ ውስጥ ሳይቀር ኮሎኔሎችና ጀነራሎች የሚገኙበት - ሰንሰለታዊ ትስስር የተደራጀ ወንጀል ብሩህ አብነት ነው። ያሁኗ ኤርትራን ገሃነም ያደረገ ብክለት ይሁን ሌላ ወንጀል፡ የሰብአዊ መብቶች መጣስና አሳረ መከራ ሀገራችንን የመበታተን ዓላማን ከግብ ለማድረስ ሆን ተብሎ እየተደረገ ያለው የተደራጀ አሰራር ነው።

የኢሳያስ አፍወርቂ እኩይና አውዳሚ ዕቅድ በተግባር ላይ እንዲውል ያስቻሉት መሰረታዊና አንኳር ምክንያቶች የራሱ ልዕለ አምባገነናዊ ባህሪያትና አካሄድ: የህዝባዊ ወያኔ ጥቅምና ሚና፡ የመላ ታጋዮቹ የዋህነትና ድክመቶች እንዲሁም ተ. ሓ. ኤ. ውስጥ የነበሩ እጥረቶችና ችግሮች ናቸው።

## ፭፡ በ ተ . ሓ . ኤ . ውስጥ የነበሩት ድክመቶችና ችግሮች

ቀደም ሲል ደካማ የሀገራዊነት ስሜት በ"ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ (ተ.ሓ.ኤ) ውስጥም ችግር ፈጥሮ እንደነበረና ኢሳያስም ይህንን ድክመትና ችግር በሚገባ እንደተጠቀመበት ጠቅሼ ነበር። በ60ዎቹ ገደማ ብዙ ውጣ ውረድን አልፎ የመጣው ተ.ሓ.ኤ (ጀብሃ) በ1971 የመጀመሪያ ጉባኤውን ካከናወነ በኋላ፡ ያደገ ሀገራዊ ድርጅት ለመሆን ተነሳ። በተለይም ከ1975 ሁለተኛ ሀገራዊ ጉባኤው ወዲህ፡ ከሌሎቹ ድርጅቶች ጋር ህብረት የመፍጠርን ጉዳይ በሚመለከት፡ በጥቅልሉ ሲታይ፡ የጠራ ሃገራዊነት በመራውና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ጉዞውን ቀጠለ።

ተ.ሓ.ኤ እንደነ ዓብደላ እድሪስንና መልአከ ተክሌን የመሳሰሉ አንቱ የሚባሉ ሰዎች የነበሩት ቢሆንም ቅሉ አንድ አምባገነን የሚቆጣጠረውና የሚያሽከረክረው ድርጅት አልነበረም። የበላይ አመራሩ ሁኔታውን በጥብቅ በተደራጀ አገባብ አልያዘውም ነበር፤ የስለላ መረቡ ከህዝባዊ ግንባር ጋር ሲነጻጸር ጠንከር ያለና መፈናፈኛ የሚያሳጣ ሳይሆን በጣም ልል ነበር። ከህዝባዊ ግንባር ጋር ስናወዳድረው ጀብሃ ውስጥ መድረኩ ለተለያዩ አስተያየቶችና አቋሞች ክፍት ነበር።

የጀብሃ የአስተዳደር ስርዓት ወይም ምሕዳር ብዙም የሚደነቅ አልነበረም። ሰንሰለታዊ ማእከልነትንና ውህደትን በተመለከተ ጉድለት ነበረው። ዘገምተኝነትና ሌሎች ከማሕበረ ሰባዊ ኋላቀርነት የመነጩ ቅጥ-የለሽነትም ነበሩት።

በጀብሃ ውስጥ በየጊዜው ብቅ ብቅ የሚሉ ከሀገራዊነት ዝቅ ባሉ ወይም ጸረ-ሃገራዊ በሆኑ ዝንባሌዎች የሚታወቁ አንዳንድ አንስተኛ ቡድኖች ነበሩ። በተረፈ የጀብሃ አመራር፡ ባጠቃላይ ሲታይ፡ ሀቀኛ ሃገራዊ ስለነበረ ሀገራዊነቱን ተማምኖ ነበር የሚጓዘው። አመራሩ፡ እንደ ኢሳያስ አፍወርቂ ድብቅ አጀንዳ ስላልነበረው ሰፊው የጀብሃ ታጋይ እንዳያውቀው ብሎ ያን ያህል የሚፈራበትና የሚሰጋበት ጉዳይ አልነበረውም። ስለዚህም የአደረጃጀቱን ዘይቤ ደረቅና የከረረ እንዲያደርግ የሚያስገድደው ጉዳይ አልነበረም። ባጭሩ ጀብሃ - ከ75 ጉባኤ በኋላ የነበረው ጀብሃ ማለቴ ነው - ኢሳያስ አፍወርቂ በግሉ ከሚቆጣጠራትና እንደፈለገ ከሚያሽከረክራት ህዝባዊ ግንባር ጋር ሲነጻጸር እውነቱን ለመናገር መቻቻል የሰፈነበት (ሊበራል) ድርጅት ነበር ማለት ይቻላል።

በተወዳጁ ሊቀ-መንበር በነብስ-ሄር አሕመድ መሓመድ ናስር የሚወከለው የጀብሃ መቻቻልነት (ሊበራሊዝም)፡ እንደ ደንቡ ከሆነ ጎጂ መሆን አልነበረበትም። ግን ምን ይደረግ!! ጀብሃ፡ ኢሳያስ አፍወርቂ የሚባል ጸረ-ሃገራዊ አጀንዳ ያነገበ ልዕለ አምባገነን የሆነ ተቃናቃኝና ባላንጣ ነበረውና!! ኢሳያስን የመሰለ ምሕረት አልባና ጨካኝ የሆነ ጠላት አጠገብህ ቆሞ በነበረበት ሁኔታ ላይ ቻይ (ሊበራል) በመሆን ቤትህን ክፍት ማድረግ ምን ያህል አደገኛ እንደነበር መገመቱ አያዳግትም። የጀብሃ ሊበራል መሆን በእርግጥ ኢሳያስን ጠቀመ።

የጀብሃ ፓለቲካዊ ሁኔታና ምሕዳር ቻይ ወይም ሊበራል በመሆኑ የታጋዮቹ ሀገራዊነት ከህዝባዊ ግንባር ታጋዮች በጣም የላቀ ነበር ማለት ይቻላል። ለምሳሌ የጀብሃ ታጋዮች የስምረት ጥያቄን በተመለከተ ሀቀኛ ሀገራዊ አቋም ይዘው በጽናት ታግሏል፡ ተሰውቷልም። ይህንን የስምረት ጉዳይን በሚመለከት የድርጅታቸው አመራርን ሳይቀር ጠንክረው የተሟገቱበትና እንዲታረም ያደረጉበት ጊዜም ነበር።

ይህ እውነት ቢሆን እንኳን፡ የጀብሃ ታጋዮች ሀገራዊነት ከኤርትራ የሀገራዊነት ዕድገት ደረጃ ራሱ የጎላ ወይም ያደገ ሊሆን አይችልም ነበር። የኤርትራ ሀገራዊነት በደልዳላ የዕድገት መሰረት ላይ የተገነባ አይደለም፤ በጀብሃ ታጋዮችም ይህንን እውነታ የሚያንጸባርቁ ድክመተቶችና እጥረቶች ነበሩ።

በመሆኑም፡ የጀብሃ ታጋዮች ከድርጅታቸው አመራር ጋር ይህንን ዓይነት ደካማነት መገለጫው የሆነ ችግር ነበራቸው። ከነሱ ውስጥ የተወሰኑ፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፡ ህዝባዊ ግንባርን የሚመጻደቁ ነበሩ። ይባስ ብለው!! ጥቂቶቹም የኢሳያስ አምላኪዎች በመሆን ብዙ ችግር በመፍጠር ለራሳቸው ከስረው ድርጅታቸውንም አክስረዋል። ይህ ሲባል ግን የጀብሃ አመራር ከታጋዮች ጋር የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት ይከተለው የነበረ ዘዴ ሁሉም ትክክል ነበር ማለት አይደለም። ለምሳሌ እንደ ብዙዎች ታዛቢዎች አመለካከት ከሆነ: በ1977 ከተከሰተው “አፈንጋጭ” (“ፋሉል”) ብሎ ከሰየመው እንቅስቃሴ ጋር የነበረውን ቅራኔ በተመለከተ የጠመንጃ እርምጃ ለመውሰድ ሰይቸኩል ትእግስትና መቻቻል በተሞላበት አኳሃን በውይይት ሂደት ብቻ መወሰን ነበረበት።

ጀብሃ ውስጥ የነበረውን ክፍተትና ድክመት ኢሳያስ በተለያየ ስልትና መንገድ በሚገባ ተጠቀመበት። ኢሳያስ ከተከተላቸው ዓበይትና ዋና ዋና ስልቶች አንዱ “5ኛ ረድፍ” (5ይ መስርዕ) ማደራጀትና ማሰማራት ነበር።

5ኛ ረድፍ ማለት ምን ማለት ነው? የኢሳያስ መንግስትና ተከታዮቹ ህግደፋውያን “አምሰተኛ ረድፍ” የሚለውን ስነ ቃል ወይም ሐረግ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ነው የሚጠቀሙበት። ተቃዋሚ ሃይሎችን ነው 5ኛ ረድፍ ብለው የሚጠሩዋቸው። መንግስቱ እንኳን ለተንኰል ብሎ ነው እንጂ 5ኛ ረድፍ ምን ማለት እንደሆነ ጠፍቶት ሊሆን አይችልም፤ ሌሎቹ ጀሌዎቹና ተከታዮቹ ግን “5ኛ ረድፍ” ስለሚባለው ነገር የሚያውቁት የላቸውም።

“5ኛ ረድፍ” ማለት ባጭሩ በውስጥህ ሆኖ ለጠላት የሚያገለግል ቡድን ማለት ነው። በአንድ ሀገር ወይም በአንድ ድርጅት ውስጥ ሆኖ በጠላትነት ተሰልፎ ለሚዋጋህ መንግስት ወይም ድርጅት በተለያየ መልክና መንገድ የሚያገለግል ቡድን 5ኛ ረድፍ በመባል ይጠራል። “5ኛ ረድፍ” ተልእኰውን ለማሳካት የሚያከናውናቸው ተግባራትም በይፋ ሳይሆን በሚስጢር ነው።

“5ኛ ረድፍ” የሚለው ሓረግ የተፈለሰፈው በ1936 በስፐይን ነው። በዚያን ጊዜ በሀገሪቱ ውስጥ በተካሄደው ምርጫ ላይ ፖፑላር ፍሮንት ተብሎ የሚጠራው ግራ ዘመም ቡድን ወግ አጥባቂውን ፓርቲ አሸነፈ። ፍራንሲስኮ ፍራንኮንና ሌሎች ጀነራሎች እምብዛም በተሟላ መልኩ ያልተሳካለት መፈንቅለ መንግስት አደረጉና፡ በታሪክ የስፐይን የእርስ በርስ ጦርነት ተብሎ የሚጠቀሰው ውግያ ተጀመረ። የፋሺስት ኃይሎችና የሌሎች ወግ አጥባቂ ድርጅቶች ድጋፍ የነበረው ጀነራል ፍራንሲስኮ ፍራንኮ የመፈንቅለ መንግስት ያካሄደው ሰራዊት አዛዥ ሆነ። በተካሄደው ጦርነት ላይ ረፑብሊካውያን የተባሉ ተራማጅ ኃይል የጀነራል ፍራንኮን ሰራዊት ድል በመምታት ከተማ ማድሪድን ተቆጣጠሩ። አንድ ጀነራል ኤሚሊዮ ሞላ የተባለ የፍራንኮ መኰንን ረፑብሊካውያኖቹን ለማጥቃት አራት የሰራዊት ረድፎች አዘጋጅቶ ነበር። በተጨማሪም አንድ ጀነራል ፍራንኮን የሚደግፍ “5ኛ ረድፍ” በረፑብሊካውያኑ ውስጥ አሰርጎ በማስገባት አደራጀ። 5ኛው ረድፍ የተደራጀበት ዋናው አላማ ቀደም ብሎ በውጭ የተደራጁት አራት የሰራዊት ረድፎች ረፑብሊካውያኖቹን ለማጥቃት ውጊያ ሲጀምሩ በውስጥ ሆኖ እንዲያጠቃ በሚል ዕቅድ ነበር። እንደታሰበውም

ዕቅዱ ተሳካ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ “5ኛ ረድፍ” የሚል ሐረግ “በውስጥህ ሆኖ ለጠላት የሚያገለግል ሚስጢራዊ ቡድን” የሚል ትርጉም ያዘ።

የኢሳያስ መንግስት ወይም ህግዲፍ አንድን አካል “5ኛ ረድፍ” ብሎ መጥራት የሚችለው ያ አካል በውስጡ ሆኖ ለተቃዋሚዎች ወይም ለሌላ ጠላት የሚያገለግል ከሆነ ብቻ ነው። አሁን ያሉት የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች፡ በግልጽና በይፋ ጸረ ኢሳያስ (ጸረ ህግዲፍ) የሚንቀሳቀሱ ጠላቶቹ ናቸው። በኢሳያስ መንግስት ውስጥ ሆነው በሚስጢር የሚንቀሳቀሱ አይደሉም። ስለዚህ “5ኛ ረድፍ”መሆን አይችሉም። እንዲያውም በተቃራኒው “5ኛ ረድፍን” ቀደም ሲል በጀብሃ እያሰረገ የነበረና፣ ዛሬሞ በተመሳሳይ በተቃዋሚ ኃይሎች ውስጥ እያሰረገ ያለው ራሱ ኢሳያስ ነው።

አሁን ጋሃድ እየሆነ እንደመጣ ሁሉ፡ በትጥቅ ትግሉ ዘመን በተ. ሓ. ኤ. ውስጥ - በአመራሩም ሳይቀር - በሚስጢር የሚንቀሳቀሱ የህዝባዊ ግንባር ደጋፊዎችና አባላት ነበሩ። እነዚህ የህዝባዊ ግንባር አባላት ተ.ሓ.ኤን. በተለያዩ መንገዶች እንቅፋቶች ፈጠሩባት፡ ጐዱዋትም። የድርጅቱን ዕቅዶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ እያከሸፉ፡ የህዝባዊ ግንባር ፕሮፓጋንዳ በጀብሃ ውስጥ እንዲስፋፋና እንዲሰራጭ እያደረጉ፡ አስተዳደራዊ ድክመቶችን እየለቀሙ በማጉላት የጀብሃን አመራር ስም እያጠፉ፡ የጀብሃን እንቅስቃሴ በነቂስ እየተከታተሉ ለህዝባዊ ግንባር መረጃ እያስተላለፉ የኢሳያስ ዕቅዶች እንዲፋጠኑ አድርጓል። በኤርትራ የትግል ታሪክ ውስጥ እስካሁን ድረስ እንደሚታወቀው፡ ለጀብሃ የሚያገለግሉ እነዚህን የመሰሉ ሚሲጢራዊ ቡድኖች በህዝባዊ ግንባር ውስጥ አልነበሩም።

በአንጻሩ፣ በዚሁ ጽሑፍ ላይ ወደኋላ እንደምናየው፡ በአሁኑ ጊዜም የኢሳያስ መንግስት “5ኛ ረድፍ” የማቋቋም ስልቱን ተቃዋሚ ኃይሎችን ለማደናገርና ለማዳከም ሲባል አሁንም እየተገለገለበት ይገኛል።

በድምሩ ሲታይ የህዝባዊ ግንባር (ሻዕቢያ) የጠነከረ ድርጅታዊ ማእከልነት፡ የጀብሃ አመራር ሊበራላውነትና ለአደጋ የተጋለጠ አካሄድ፡ የ5ኛ ረድፍ ሚና ብቻ ኢሳያስን የትግል ሜዳን በሞኖፓል ለመቆጣጠር አላስቻሉትም። ኢሳያስን የትግል ሜዳውን ለመቆጣጠር ያስቻለው ሌላው ተጨማሪና ትልቁ ነገር የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በኤርትራ ትግል ላይ ጣልቃ መግባት ነበር። የወያኔ ጣልቃ ገብነት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተከሰቱት ለውጦች ወይም ዕድገቶችና የምዕራውያን መንግስታት ፖሊሲ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ይህንን ነጥብ ባለፉት የተለያዩ መድረኮች በዝርዝር ያብራራሁት ስለሆነ እዚህ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም። የዚህ ጽሁፍ ዋና ቁም ነገር ግልጽና ብሩህ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ ግን ነጥቡን፡ ለማስታወስ ያህል ብቻ፡ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቢካተት ያግዛል የሚል እምነት አለኝ።

ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ - እንዲያውም ከ40ዎቹ - ጀምሮ የኤርትራ ፖለቲካ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ጋር ተዛምዶ ነው ሲታይ የነበረው። ባላት ቁልፍ ስትራተጂያዊ አቀማመጥ ምክንያት ኤርትራን ለመቆጣጠር ፍላጎትና ምኞት ያላቸው የባዕድ ኃይሎች፡ ኤርትራን በሚመለከት ስትራተጂያቸውን ሲቀርጹና ሲነድፉ በኢትዮጵያ ምን ዓይነት መንግስት እንደነበረና ከነርሱ ጋር ምን ዓይነት ዝምድና እንደነበረው ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር።

በ70ዎቹ አጋማሽ ላይ፡ በኢትዮጵያ ንጉሳዊ ሥርዓት ተወግዶ ስነ-ሓሳባዊና ፓለቲካዊ ምርጫው ጸረ ምዕራባዊያን የሆነ መንግስት ሲቋቋም፡ ወያኔ በኤርትራ ትግል ላይ ጣልቃ ለመግባት የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጠረለት። ምዕራባውያን ኃይሎች፡ የኤርትራን ትግል

የራሳቸውን ጥቅም ማስፈጸሚያ ለማድረግ ሲባል፡ ሀገራችንን በረጅም ጉዞ የሚገነጣጥል ስትራተጂ ቀየሱ። በተነደፈው ዕቅድ መሰረት፡ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለማሳካት የኤርትራ የትግል ሜዳ ሂዶ ሂዶ በኢሳያስና በወያኔ የበላይነት ቁጥጥር ስር እንዲውል አደረጉ። ሁለቱንም በተለያዩ መንገዶች እየረዱ በተራዘመ ሂደት ላይ፡ እንደተመኙት፡ የነሱ ጠላት የነበረ የአዲስ አበባው መንግስት እንዲወድቅና እንዲወገድ አደረጉ።

አዎ፡ ሌሎች ክስተቶችና አጋጣሚዎች የራሳቸው የሆነ ሚና የተጫወቱ ቢሆንም፡ ኢሳያስን የኤርትራ የትግል ሜዳውን በበላይነት ለመያዝ ያስቻለው ትልቁ ነገር ወያኔ የተጫወተው ሚና ነው። ወያኔ ከኢሳያስ ጋር አብሮ ጀብሃን በመምታት፡ ከትግል ሜዳ እንዲወጣ አደረገ፤ ይህም በኤርትራ ህዝብ ላይ የፈጸመው የመጀመሪያ ትልቁ ወንጀል ነበር።

ወያኔ ይህንን እኩይ ድርጊት ሲፈጽሙ፡ አላማቸው የኤርትራን ህዝብ ጥቅም ለማስከበር እንዳልነበረ ግሃድ ነው። አላማቸው የኤርትራን አብዮት ጠልፈው የጥቅማቸው መገልገያ ለማድረግ ነው የነበረው። ጥቅማቸው ደግሞ፡ የደርግን ስርዓት በመገርሰስ፡ ኢትዮጵያን በሁሉም መስክ መቆጣጠር ነው የነበረው። የወያኔ ዕቅድና ሕልም ግን፣ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፡ በኢትዮጵያ ለመንገስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ከዚያ በላይ ነበር።

## ፮፡ ኢሳያስና ወያኔ እንደ መንግስታት፤ አለመግባባትና ጦርነት

ኢሳያስና ወያኔ መርዘኛ የሆነ የጋራ ዕቅድ ይዘው በ90ዎቹ መጀመሪያ ደርግን ካስወገዱ በኋላ ከመጠን ያለፈ የትብብር ዝምድና ነበራቸው። በዚያን ጊዜ ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዕቢያ) በኢትዮጵያ ውስጥ ያላንዳች ገደብ እንደፈለገ ያደርግ ነበር። በተለይም በኢኮኖሚውና በንግድ መስክ፡ ሕጋዊና ፍትሓዊ ባልሆኑ መንገዶች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ያደርግ ነበር። ለምሳሌ፡ እንደ ቡናና፣ ሰሊጥ የመሳሰሉትን የእርሻ ምርትና የተፈጥሮ ሀብቶች በኢትዮጵያ ብር ገዝቶ መልሶ ወደ የተለያዩ ሀገሮች በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ (hard currency) ያገኝ ነበር[35]።

በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የኢሳያስ መንግስት እንቅስቃሴ በኢኮኖሚ ዝርፊያ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በፖለቲካው መስክም ማንንም ሳይጠይቅ በገዛ ፈቃዱ በሰዎች ላይ ሕጋዊ ያልሆኑትን እርምጃዎች ይወስድ ነበር። ለምሳሌ በወቅቱ እንደነ ግራዝማች ተስፋሚካኤል ጆርጆ፡ ዳኒኤል ገብረኪዳን፡ ገብረብርሃን ዘርኤና፡ ዘካርያስ ንጉሰ በመሳሰሉት በአዲስ አበባና በተለያዩ ክፍሎች ይኖሩ በነበሩት ብዙ ኤርትራውያን ላይ የግድያና የዓፈና እርምጃ ወስዷል። እነዚህ የግድያ እርምጃ የተወሰደባቸው ሰዎች በኢሳያስ መንግስት ዘንድ የሚጠሉና የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ። በወቅቱ ወያኔ፡ በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ የነበረ መንግስት በመሆኑ ይህ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከልና ሕግ ማስከበር ይገባው ነበር፡ ከተፈጸመ በኋላ ደግሞ ወንጀል የፈጸሙትን ሰዎች ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረብ ይገባው ነበር፤ ግን አላደረገም። ይሉቁንም ከኢሳያስ ጋር በመተባበር፡ የጥቃቱና የግድያው ተባባሪ ነበረ። ይህ በኤርትራውያን ላይ የተፈጸመ ዘግናኝ ግፍ ነበር።

35. አረጋሽ አዳነ! በዮናስ በላይ አበበ! ገጽ 86

ከዚህ የግድያና የአፈና ግፍ የባሰና የከበደ በደል በኤርትራ የወደፊት ዕድል በሚወስን የኤርትራ ሪፈረንደም ላይ የተፈጸመ ሴራ ነበር። ወያኔ በ1991 መንግስታዊ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ፡ በኤርትራ ላይ የተካሄደው ሪፈረንደም በአግባቡ የሁሉም ኤርትራዊ ተሳትፎ ያረጋገጠ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሓዊ እንዲሆን ማድረግ ሓላፍነት ነበረው። የረፈረንደሙ ሂደት ሀቀኛ "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን" ምርጫ እንዲሆን የተመቻቹ የዴሞክራሲ ሁኔታዎች እንደ ቅድሙሁኔታ መፈጠር አለባቸው፤ የተለያዩ የኤርትራ የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች ደግሞ የየራሳቸውን አቋም፡ በነጻና በግልጽ መግለጽና ማራመድ መቻል አለባቸው ብሎ መወሰን ነበረበት። ይህ ግን አልተደረገም። ረፈረንደሙ ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሂደት ተከናውኖ ቢሆን ኖሮ፡ ህዝቡ ኤርትራ ሉዓላዊ ሀገር ትሁን ብሎ እንደሚወስን የሚያጠራጥር አልነበረም።

ወያኔ የሪፈረንደሙን ሂደት ዴሞክራስያዊ እንዲሆን ባለማድረጉ እኛ ኤርትራውያን በሁለት መንገድ ተጎድተናል። በመጀመሪያ ሪፈረንደሙ ሕጋዊ ባልሆነ አግባብ በመካሄዱ፡ ብዙዎች ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ ተቀባይነት የለውም እንዲሉ መሰረት - ቢያንስ ሰበብ ወይም ማስመሰያ - ሆኗል። በተጨማሪ፡ ወያኔ ትክክለኛ ያልሆነ ረፈረንደም እንዲካሄድ በመፍቀድ ኤርትራን እንዳለች ከነነብሷ ለኢሳያስ አስረክቧታል። ሌሎች የፓለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ህዝቡ በጠቅላላ በሀገሪቱ ጉዳይ ላይ በነጻ ለመሳተፍ መብት እንደሌላቸውና እንደባዕድ ተቆጥረው የኢሳያስን አምባገነናዊ ስርዓት በኤርትራ ውስጥ እንዲተከል አድርጓል። ለምን?

ኤርትራ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሪፈረንደም በማካሄድ ነጻነትዋን ያለጥርጥር ማረጋገጥ እየቻለች፡ ወያኔ ለምንድን ነው ትክክለኛ ያልሆነ ረፈረንደም እንዲካሄድ ያደረገው? ወያኔ እንዲህ ያደረገበት ዋናው ምክንያት፡ የሪፈረንደሙን ሂደት ያየው ከኤርትራ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን ከራሱ ጥቅም አኳያ በመሆኑ ነው። እንዴት? ታስታውሱ እንደሆነ፡ ወያኔ የኤርትራን ረፈረንደም በሚመለከት ህዝቡ ነገ ምን ይለናል ብለው ትንሽ እንኳን ሳያፍሩ ነበር ቅስቀሳ ያደርጉ የነበሩት። ልክ እንደ የራሳቸው የግል ጉዳይ አድርገው በመውሰድ ነበር በሰፊው የተሰማሩበት። ለምሳሌ ሪፈረንደሙ በአዲስ-አበባና በሌሎች ቦታዎች በተካሄደበት ጊዜ፡ ብዙ ኤርትራውያን ነዋሪዎችን ሂዱና ነጻነት ምረጡ እያሉ ይጎተጉቱና አልፎ ተርፎም ያስገድዱ እንደነበረ የታመኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

አሁን ወደኋላ መለስ ብለን ስናየው፡ ወያኔ ረፈረንደሙን - ማለት የኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል - እንደ ራሳቸው የግል ጉዳይ አድርገው ቢሰማሩበትና በፌሯሯጡበት የሚያስገርም አይደለም። አዎ!! ለነገሩማ የነሱ ጉዳይ እኮ ነበር ማለት ይቻላል። ወያኔን በሪፈረንደሙ ድራማ ላይ የበለጠ ተዋኒያን ሆነው እንዲንቀሳቀሱ የገፋፋቸው ዋናው ጉዳይ ሂዶ ሂዶ በመጨረሻ ትግራይን ለብቻዋ ገንጥሎ የራስዋን ሪፓብሊክ የማቋቋም የሩቅ ዕቅድ ነበር። ይህ በዋናነት ከኢሳያስ አፍወርቂ ጋርም የሚያዛምዳቸው ዕቅድ እንዲሳካ፡ ከሁሉም በፊት ኤርትራ ለነሱ በሚያገለግል ሁኔታ ከኢትዮጵያ የግድ መገንጠል ነበረባት። በመሆኑም ኤርትራ እንዳለች ከነነብሷ ለኢሳያስ ብቻ ለማስረከብ ሲባል የውሸት ረፈረንደም እንዲካሄድ አድርጓል። ባጭሩ ሲታይ፡ ረፈረንደም በሚል ስም የተካሄደው የይስሙላ ሂደት ትግራይን ከኢትዮጵያ መገንጠል ለሚል የረጅም ጊዜ ዕቅድ መንገድ የሚያመቻችና የሚጠርግ እንጂ፡ የኤርትራን ህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር ተብሎ በቅንነት የተቀናጀና የተደራጀ አልነበረም።

ሪፈረንደሙ በተካሄደበት ጊዜ የኢሳያስ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ግና እንደፈለገ የሚንቀሳቀስበትና የፈለገውን ነገር ሲያደርግ የነበረበት ወቅት ነበር። በዚያን ጊዜም በወያኔ መንግስት የስብሃት ነጋና መለስ ዜናዊ ቡድን የበላይነት ነበረው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መጠቀስ ያለበት ነጥብ አለ። ከሁሉም የወያኔ አመራር በተለየ መልኩ ከኢሳያስ ጋር የቅርብ ግንኙነትና ዝምድና የነበራቸው ያው ስብሃት ነጋና መለስ ነበሩ። ከሁለቱ ደግሞ ከድሮ ጀምሮ ለኢሳያስ በጣም ቅርብ የነበረው ስብሃት ነጋ ነው[36]።

ሪፈረንደም ከተጠናቀቀ ጥቂት ዓመታት በኋላ፡ የኢሳያስ መንግስት እንቅስቃሴዎች፡ የተወሰነውን የወያኔ አመራር ክፍል - በተለይም እነ ገብሩ አስራትን ጨምሮ በትግራይ አካባቢ የነበሩትን - ማስቆጣት ጀመረ። በመጨረሻም ይህ ቡድን የኢሳያስ መንግስት እንደለመደው በኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ የፈለገውን ከማድረግ እንዲከለከል አደረገ። በዚህ ምክንያት፡ እየሻከረና እየተባባሰ የመጣው ቅራኔ ዞሮ ዞሮ የባድመን ጦርነት አስከተለና ያ ሁላችንም የምናውቀው ውድመትና እልቂት ደረሰ።

ለባድመ ዉጊያ ዝግጅት ሲደረግ በነበረበት ጊዜ ያ ጸረ ኢሳያስ የነበረው የወያኔ የአመራር ክፍል ቀደም ሲል የበላይነቱን ይዞ የመጣውን በመለስና ስብሃት ይመራ የነበረውን ቡድን አሸንፎት ነበር ማለት ይቻላል። በዚሁ ሁኔታ እንዳሉ ነው የወያኔ መሪዎች ከኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ለመተባበርና ዝምድና ለመመስረት የፈለጉት። የወያኔ መሪዎች የኢሳያስ መንግስትን በመቃወም ለመተባበር ዝግጁ ነን ብለው፡ ከብዙ የኤርትራ ድርጅቶች ጋር ዝምድናውን ተግባራዊ ለማድረግ ስምምነት ላይ ደረሱ። ለምሳሌ በነብስሄር ዓብደላ ኢድሪስ ይመራ ከነበረው የተ. ሓ. ኤ. ድርጅት ጋር፡ ለወታደራዊ ስልጠናና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በሚመለከት ስምምነት ላይ ተደርሶ፡ በመጠኑም ቢሆን ተግባራዊ እንቅስቃሴም ተጀምሮ ነበር።

በ2001 ግን በወያኔ አመራር ውስጥ አዲስ ሁኔታ ተፈጠረ። አመራሩ - መላ ድርጅቱም ማለት ይቻላል - ውስጥ ውስጡን እየተብላላ መጥቶ በመጨረሻ ለሁለት ተከፈለ። የመንግስት ስልጣኑም ተመልሶ በስብሃት-መለስ ቡድን እጅ ገባ። ይህ ስልጣን የጨበጠው ቡድን የኢሳያስ መንግስት እንዲመታበት አይፈልግም ነበር። አሁን ያለው የባድመና የዳር ድንበሩን ማካለል የሚመለከት ሁኔታ የዚሁ ቡድን መንፈስን የሚያንጸባርቅ ነው[37]።

---

36. ገብሩ አስራት፡ ገጽ 222

37 .በሄግ የተሰየመው ፍርድ ቤት፡ የባድመን ውጊያ በሚመለከት ከሰጠው ውሳኔ በዚሁ ጽሑፍ ለምናቀርበው መልእክት አስፈላጊ የሆኑት ነጥቦች ሶስት ናቸው። እነሱም 1. ለውጊያው መጀመር ጠንቅ የሆነቺው ኤርትራ ናት፣ 2. ባድመ የተባለቺው ጎጥ በኤርትራ ግዛት ውስጥ ናት፣ 3. የዳር ድንበር መካለል እስከሚደረግ ድረስ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል ከዳር ድንበሩ 25 ኪሎ ሜትር ወደ ኤርትራ ግዛት ዘልቆ የሚገባ ነጻ ቀጠና (buffer zone) እንዲኖር የሚሉ ናቸው። የወያኔ መንግስት እስካሁን ድረስ ከባድመ አልወጣም። የሆነ ሰንካላ ምክንያቶችን እየፈጠረ የዳር ድንበር መካለል እንዳይኖርና ተግባራዊ እንዳይሆን ለመተባበር ፈቃደኛ አልሆነም። የኢሳያስ መንግስትም በበኩሉ የተከለለውን የሰላም ቀጠና - (buffer zone) በማፍረስ በቁጥጥሩ ስር አስገብቶት ይገኛል። ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሁለቱን ባለንጋራ መንግስታት ሲወቃቀሱና አንዱን በሌላው ላይ ሲያሳብብ ይሰማል እንጂ ወደ ዉጊያ የሚያመራ ነገር አላየንም። ወደ ውጊያ የሚገቡም አይመስሉም።

ከ2001 መጨረሻ ጀምሮ በስብሃተ-መለስ ቡድን በሞኖፖል የተያዘው የወያኔ መንግስት፡ ከኤርትራ ተቃዋሚዎች ጋር ተጀምሮ የነበረውን የኢሳያስ መንግስትን በጋራ የማጥቃትና የማዳከም ዕቅድ ክዶ፡ ትርጉም ያለው እርዳታ ማድረግ አቋረጠ። ዞሮ ዞሮም በተለያየ ስልትና የተንኰል ጥበብ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶችን አደከማቸው፤ አኰላሻቸውም። አሁንም እያዳከመና እያኰላሸ ይገኛል። ይህ አሁን ያለውን ሁኔታ ለመረዳት የሚያግዘን መረጃ ነው። እንዲያውም ይህንን እውነታ በብቃትና በአግባቡ ሳትረዳ አሁን ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች በብቃት ለመተንተን የሚቻል አይሆንም።

## ፯፡ ኤርትራ፣ የወያኔና-ኢሳያስ ወቅታዊ ፖሊሲ

አሁን ያለው የወያኔ መንግስት ምን ዓይነት ስርዓት ነው? በደፈናው አሁን ያለው የወያኔ ስርዓት በዓይነቱ ምርጫዊ አምባገነንነት (electoral authoritarianism) ተብሎ የሚገለጽ ነው። በሌላ አነጋገር ምርጫዊ መልክ ወይም የምርጫ ሽፋን ያለው አምባገነናዊ ስርዓት ማለት ነው። ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች የወያኔን ስርዓት በዚሁ ዓይነት ነው የሚገልጹት[38]፤ እኔም በዚሁ አገላለጽ እስማማለሁ። በኢትዮጵያ በየአምስት ዓመቱ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት ተሳትፎ ያለው የሚመስል ምርጫ ይካሄዳል። ነገር ግን በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ መንግስት፡ ሁሉንም ዓይነት ስልትና ተንኰል እየተጠቀመ እሱ ብቻ እንዲያሸንፍ ያደርጋል[39]። ለምሳሌ፡ በ2010 በነበረው የምርጫ ውድድር ወያኔ 99.6% ወንበር አሸንፈናል በማለት ፓርላማውን በሞኖፖል ተቆጣጠረው። ይህ ሰሚውን የሚያስደምም ስሞታና ዓይን ያወጣ የማጭበርበር ድርጊት ብቻ አልነበረም፤ ለህዝቡ ያለው ንቀትንና ማንአለብኝነትንም ጭምር የሚያንጸባርቅ የወጣለት የዝርፊያ ተግባር እንጂ!!

እውነቱን ለመናገር፡ ወያኔዎች በስልጣን ላይ ያሉት በጉልበት ወይም በጡንቻ ነው እንጂ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ስለወደዳቸው አይደለም። ህዝቡን የተቆጣጠሩት በማስፈራራት ነው። ወያኔ ብልጣ--ብልጥ ስለሆኑ ግን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የለየለት አምባገነናዊ ስርዓታቸው በተወሰነ ጎኑ ሊበራል መልክ እንዲኖረው ያደርጋሉ።

---

የባድመንና የጻር ድንበሩን ጥያቄ በሚመለከት ሁኔታ "አይ ሰላም አይ ጦርነት" ሆኖ እንዲቀጥል ሁለቱ በየራሳቸው ምክንያት የሚፈልጉት ይመስላል። የኢሳያስ መንግስት ወያኔ መሬታችንን ይዟል፡ ሉዓላዊነታችንን ደፍሯል እያለ የህዝቡን የዴሞክራሲና የፍትሕ ጥያቄ ላለመመለስ እንደ ማዘናግያና ማደናገሪያ ሽፋን እየተጠቀመበት ይገኛል። የወያኔ መንግስትም በበኩሉ ለሁለት ነገሮች ሲጠቀምበት ይታያል። በአንድ በኩል በሰሜን ጥቃት ሊደርስብን ይችላል እያለ ዘመናዊ ጦር መሳሪያ፡ ወታደራዊ ንዋትና ተቋማት ወደ ትግራይ ለማጓጓዝ ይጠቀምበታል። በሌላ መልኩ ደግሞ በሀገሪቱ በተለይ በትግራይ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን ባጠቃላይ የህዝቡን ነጻ እንቅስቃሴ ለመገደብ እየተጠቀመበት ይገኛል። ስለዚህ የባድመንና የጻር ድንበሩን ጥያቄ ሁለቱ መንግስታት ስልጣናቸውን ለማራዘምና ለማደላደል እየተጠቀሙበት ነው ማለት ይቻላል።

38. Merera Gudina (2011)
39. በምርጫ ጊዜ ተቃዋሚ ኃይሎች እንዳያሸንፉ የወያኔ መንግስት ሆን ብሎ ከሚጠቀምባቸው ርትዓዊና ፍትሓዊ ያልሆኑ ስልቶች ውስጥ ኤርምያስ ለገሰ ኖቬምበር 1, 2014 በከተማ ሲያትል ዋንሸንግተን በሰጠው መግለጫ ላይ በዝርዝር ተቀምጧል። ሙሉ መግለጫውን ለመስማት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ይጫኑ። http://www.ethiomedia.com/15store/4247.html

እንዲህ በማድረግ ብዙን ሰው - ኤርትራውያንን ጨምሮ - አሳስተዋል፣ ገናም እያሳሳቱ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ፡ ህዝቡ ለወያኔ ያለው ጥላቻና ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛና እየሰፋ በሄደ ቁጥር በዚያው መጠን መንግስቱ በህዝቡ ላይ የሚያደርሰው ጭቆናና ጫና በአግባቡ እየጨከነ በመሄድ ላይ ነው። በየጊዜው እየታሰሩ ያሉት የፓለቲካ ተቃዋሚዎች፡ ጋዜጠኞች፡ የሰብአዊ መብት ተሟጓቾች ወዘተ እየጨመሩና እየተበራከቱ በመሄድ ላይ ናቸው። ይህ ጫናና ዓፈና በትግራይም ጭምር ከመጠን በላይ እየከፋ ነው።

ወያኔ ስልጣን ደመ ነብሳቸው ስለሆነ በፍላጎታቸው (ማለት በሰላም) ስልጣንን መልቀቅ አይፈልጉም። እንደ ብዙዎቹ የአፍሪቃ ገዢዎች፡ *"በደም የተገኘ ስልጣንን ያለ ደም መልቀቅ"* አይታሰብም በሚለው ኋላቀር የስልጣኔ ደረጃ ላይ ነው ያሉት[40]። በመጨረሻ እንኳን፡ ልክ እንደ ሌሎቹ አምባገነኖች፡ እነሱም መውደቃቸውና ማለፋቸው አይቀሬ ነው። ነገር ግን፡ ከስልጣን ከወረዱ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም የሚኖሩ አይመስሉም። ታሪካቸው እንደሚያሳየውና እንደነ ስብሃት ነጋ ከመሳሰሉት መሪዎቻቸው እንደሰማነው፡ ስልጣን ላይ ከሌሉ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚፈቅደውን ሕገ መንግስታቸውን ተጠቅመው፡ ትግራይን ከኢትዮጵያ በኃይል ለመገንጠል ሊሞክሩ ነው። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ፡ አስቀድመው የቀረቿውን ኢትዮጵያ በረቀቀ መንገድ መበታተን፡ አሊያም የህዝብዋንና የግዛትዋን አንድነት የሚያዳክምና የሚያላላ ተግባር ከመፈጸም ወደኋላ አይሉም። ከዚያም በኋላ ቀደም ሲል እንደገለጽነው ከኤርትራ አንዱ ክፍል ጋር በማበር አንዲት የራስዋ የሆነ ወደብ ያላት ሀገር የመመስረት ህልማቸው ተግባራዊ ለማደረግ መሞኮራቸው የማይቀር ነው። ሆኖም በብሄረሰባዊ ማንነቱ የሚኰራ የትግራይ ህዝብ፡ በኢትዮጵያዊነቱም የጸና ስለሆነ፡ የወያኔ የረጅም ጊዜ ዕቅድ በመጨረሻው ቀን ይከሽፋል። ከመክሸፉ በፊት ግን ብዙ ውድመትና እልቂት ሊያስከትል ነው።

አስቀድሞ እንደተገለጸው በነ ስብሃት ነጋ የሚመራው የወያኔ አንዱ ክፍልና የኢሳያስ መንግስት ኤርትራን የሚበታትን የጋራ የሆነ የሩቅ አላማ አላቸው። ሁለቱም በኤርትራና በኤርትራውያን ላይ እያካሄዱት ያሉት ፓሊሲ - ማለት እነ ኢሳያስ በኤርትራ በኩል እነ ስብሃት ደግሞ በኢትዮጵያ በኩል ሆነው - ለሩቅ የጋራ አላማቸው የሚያሳካ ተግባር ነው።

ወያኔ የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎችን በሚመለከት ያለው ፓሊሲ ከዚሁ አላማና ዕቅድ ጋር የተቀራኘና ይህንን አላማ የሚያገለግል ነው። የኢሳያስ መንግስትም በበኩሉ፡ የኤርትራ አስተዳደርን ይሁን ከሱ ጋር የተዛመዱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችን በሚመለከት ያለው ፓሊሲ፡ በዚህ አላማ የሚመራና ለዚህ አላማ ያቀና ነው።

ገዳዩን በበለጠ ዘርዘር አድርገን ለማየት እንዲመች፡ የኢሳያስ መንግስት ኤርትራ ውስጥ በሚተገብረው ፓሊሲ እንጀምር። አስቀድሜ እንደገለጽኩት፡ ኢሳያስ ኤርትራን በተጨባጭ በዕቅድ እየገደላት ነው ያለው[41]። ኤርትራን በዕቅድ በመግደል፡

40. መረራ ጉዲና (አዲስ አበባ፡ ነሐሴ 2006 E. C.) ገጽ፡ 202

41. ይህንን ሀቅ ኢሳያስ ራሱም ቢሆን እያመነበት ነው ማለት ይቻላል። ዓንደብርሃን ወልደጊዮርጊስ

*ኤርትራውያንን በሀገራቸው እንዳይኰሩ እያደረጋቸው ይገኛል። በሃገራቸው መኩራትና ተስፋ ማድረግ ካቆሙ ደግሞ፡ ይህችን ሀገር ለግዛት አንድነትዋንና ሉዓላዊነትዋን ሊከላከሉላት በወኔ ሊነሳሱ አይችሉም። ስለዚህም፡ ማንኛውም ጸረ ሀገራዊ ዕቅድ የማይጎዳ መስሎ ታይቶዋቸው በየዋህነት ሊቀበሉት ይችላሉ።*

*ኤርትራን እያጠፋና እያደማ ያለው የኢሳያስ መንግስት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የሚታገሉ ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ኃይሎችን ሊጠቅምና ሊረዳ አይችልም። የራሱን ህዝብ በኃይል እየጨቆነ ያለው ጨካኝ ልእለ አምባገነን በአጓራባች ህዝቦች ላይ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ለመተባበርና ለመተጋገዝ ባህሪያቱ አይፈቅድለትም። በመሰረቱም፡ ኢሳያስና ወያኔ፡ ሂዶ ሂዶ በመጨረሻ ኤርትራን የሚበታትን የጋራ የሩቅ ጊዜ ዕቅድ ስላላቸው፡ ኢሳያስ የሚፈልገው ወያኔን በስልጣን ላይ እንዲቆይለት እንጂ እንዲወገድ አይደለም። ነገር ግን፡ ኢሳያስ አላማውንና ስትራተጂውን ለመደበቅ ሲል፡ ጸረ ወያኔ የሚታገሉትን የኢትዮጵያ የፓለቲካ ተቃዋሚ ኃይሎች የሚረዳ መስሎ ለመታየት ይሞክራል። እነዚህ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ወያኔን ለመጣል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ ከኢሳያስ የሚያገኙት የረባ እርዳታ እንደሌለ ከመሪዎቻቸው አንዳንዱ ይገልጻሉ፤አሁን አሁንማ፡ በተለይም የግንቦት 7 ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታፍኖ ከተወሰደ ወዲህ፡ የኢሳያስ መንግስት፡ በማንኛውም መልኩ ዘላቂ የትግል አጋራቸውና ደጋፊያቸው ሊሆን እንደማይችል በውል እየተገነዘቡ ናቸው።*

*በተመሳሳይ መልኩ፡ ወያኔስ እውነት የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች ደጋፊ መሆን ይችላሉ? ኢሳያስ ከማንአለብኝነት በመነሳት፡ በወያኔ ላይ ብዙ የማንኳሰስ ተግባራትና ግፍ ፈጽሟል። ኢሳያስ እንደ ግለ ንብረቱ አድርጎ የያዘው ህዝባዊ ግንባር የተባለው ድርጅትም መንግስትም*

*በቅርቡ ባሳተመው መጽሐፍ፣ ኢሳያስ ሲሰክር "እኔ በሌለሁበት ዓጋመ እያላችሁ እንደምታሙኝ አውቃለሁ፣ ግን ክንዴን አሳያችኋለሁ። ይችን ሀገር እንዳመጣኋት ድምጥማጧን አጠፋታለሁ" ብሎ ይዝት እንደነበረ ነግሮናል።* Andebrehan Woldegiorgis *ገጽ* 322 *የግርጌ-ማስታወሻ* 329።

*ዓንደብርሃን ይህን መረጃ ስላካፈለን ለስነ-ስርዓቱ እናመሰግነዋለን። ከዚህ በተረፈ ኢሳያስ - ርእሰ ብሄርና መራሂ መንግስት ተብሎ - ኤርትራን አጠፋታለሁ ብሎ በግልጽ ሲናገር እየሰሙ ዓንደብርሃንና ሌሎች የኢሳያስ አገልጋዮች ምን ሲያደርጉ ነበር? የሚል የክስ መልክ ያለው ጥያቄ ማንሳት የግድ ይላል። ይህ ነገር ራሱን የቻለ ጉዳይ ስለሆነ አሁን እንዲሁ በጨረፍታ ብቻ ጠቅሼው ልለፍ። ይህንን እና ሌሎች ተዛማጅ አርእስቶችን ለሌላ አጋጣሚ በግርድፍ ልተዋቸው መርጫለሁ። ያሁኑ ዋና ነጥቤ የሚያተኩረው በሚከተለው ነው።*

*የኢሳያስ ንግግር ብቅል ያወጣው የማይጎዳ ትርጉም-የለሽ አባባል ነው በማለት ችላ ተብሎ የሚታለፍ አይሆንም። ኢሳያስ ምንም ቢሰክርም እንደዚህ ዓይነት ንግግር ዝም ብሎ እንደመጣለት ይጥላል ብዬ አላምንም። ረጅም የማታለልና ተንኰል የመሸረብ ተሞክሮ ያለው ሰው ነው። እንደምንሰማውና እንደምናነበው ከሆነ ደግሞ የአልኮሆል መጠጥን የመቋቋም ዓቅሙ እንዲሁ ቀላል አይደለም!! ኢሳያስ ይህንን ዓይነት ፉከራ ያሰማው ከነጻነት በኋላ እንደሆነ ብቻ እንጂ፡ በትክክል መቼ እንደሆነ አልተነገረንም። የሆነ ሆኖ መታወቅ ያለበት እውነታ ኢሳያስ ኤርትራን ማጥፋት የጀመረው ድሮ - የትግራይ ትውልድ እንዳለው እንኳን የማይተወቅበት በነበረ ጊዜ ነው። ኢሳያስ ለምን አሁን ደርሶ ይህን ቃል ያነሳል? እንዲሁ ዓጋመ ስለተባለ ሊሆን አይችልም፣ ዓጋመ የሚሉት ሰዎች ካሉ። ደግሞ "ዓጋመ" የሚለው ቃል ያን ያህል ከባድ ስድብ ሆኖ ሀገርን ያህል ለማጥፋት ምክንያት ሊሆን!! የማይመሰል ነገር ነው። ኢሳያስ 'ሃገርን አጠፋለሁ' ብሎ ሲፎክር፡ ያም ሆነ ይህ አላማው ባይገድም፡ አሁን በዓይን የሚታይ፣ ከሁሉም ተባባሪዎቹ ጋር በመሆን ኤርትራን እየገደላት እንደሆነ ራሱም ጭምር እስከማመን ደርሷል ማለት ይቻላል።.*

በትጥቅ ትግሉም ሆነ በዘመነ "ነጻነት" ወያኔንና የትግራይ ህዝብን በጠቅላላ አናንቋቿል፣ አጥቅቷቸዋልም። በ80ዎች በትግራይ አስከፊ ድርቅ አጋጥሞ በነበረበት ጊዜ፡ ህዝባዊ ግንባር በሚቆጣጠረው ነጻ መሬት በኩል፡ በረሃብ ለተጠቁ ተጋሩ የውጭ እርዳታ እንዳያልፍ ከልክሏል፣ የወያኔ ታጋዮች ሻዕቢያን ለመርዳት በሳሕል ግንባሮች ተሰልፈው በነበሩበት ጊዜ፡ ከሁለቱ ድርጅቶች ስምምነት ውጭ በሆነ መልኩ፡ ታጋዮቹን በህዝባዊ ግንባር የውጊያ መስመር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ፡ አስፈላጊ ያልሆነ መስዋእትነት እንዲከፍሉ አድርጓል፣ መኪናዎችንና ሌሎች ንብረቶችን በአመጽ ወስዷል[42]። ይባስ ብሎ ደግሞ፡ የባድመን ጦርነት በመለኰስ ቁጥር ስፍር ለሌለው እልቂትና ውድመት ምክንያት ሆኗል[43]። ይህ ለምሳሌ ያህል የቀረበ እንጂ በደሉ ከዚያም በላይ ነው። ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት፡ ወያኔ ኢሳያስን ለማስወገድ፡ የኤርትራ ተቃዋሚዎችን ለማገዝና ለማደራጀት ደስተኞችና ዝግጁ ይሆናሉ ብሎ መጠበቅና ማሰብ ርትዓዊ ነው። ካላደረጉ ግን፡ ከውስጥ ሌላ ከበድ ያለ ምክንያት አላቸው ማለት ነው። እንዲያውም ወያኔ ይህን ባለማድረጋቸው፡ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ኤርትራ በኢሳያስ ቁጥጥር ስር ሆና እንድትቀጥል የተለየ ፍላጎት አላቸው በማለት ብቻ ነው ነገሩን መደምደም የሚቻለው።

ኢሳያስ ትልቅ እገዛ ያደረገላቸው መሆኑን ራሳቸው ወያኔዎች ጠንቅቀው ያውቃሉ። ኢሳያስ፡ የኤርትራ የነጻነት ትግል፡ ደርግን ለማውደቅ አላማ እንዲጠለፍ አድርጎ፡ ወያኔን በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲነግሱ አስችሎዋቸዋል። በተጨማሪም፡ ዞሮ ዞሮ በይዘቱና በድምር ውጤቱ፡ ከትውልዳዊ ሐረግ በማይወጣና በማያልፍ የብሄር-ብሄረሰብ ጽንሰ-ሀሳብ የሚመሩት ወያኔ፡ ሌላ ቀርቶ ኢሳያስ እኮ "ወዲ ላሕምና" (*"የወንዝ ልጃችን")* ነው በማለት በቀላሉ እንደማይጨክኑበት መገመት ይቻላል። ዋናውና ትልቁ እውነታ ግን፡ ቀደም ሲል በተገለጸው የሩቁ ዕቅድ፡ ኢሳያስ ሸሪካቸውና አጋራቸው ስለሆነ ያስፈልጋቸዋል። ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት፡ ወያኔ ኢሳያስ ከስልጣን እንዲወገድ የማይፈልጉ መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

አዲስ ዘመን የተባለ ጸሐፊ፡ መረጃ.ኮም ተብሎ በሚጠራ ድሕረ ገጽ (ዌብ-ሳይት) ላይ ይህንን ነጥብ በሚመለከት አሳማኝ የሆነ ሀሳብ አስቀምጧል። "የትግራይ-ትግርኚ ፓለቲካ" በሚል ርእስ ስር በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከጻፈው አንቀጽ ውስጥ እንዲሚከተለው ይላል።

> "Eritrean opposition groups are now armed and trained in northern part of Ethiopia to fight the regime in Asmara. Similarly, Ethiopian opposition groups are also managed and financed by Isayas Afeworki to fight the regime in

42. ገብሩ Aስራት ገጽ 115-123

43. ጀነራል ዑቕበ ኣብርሃ ለዳን ኮነል በሰጠው ቃለ መጠይቅ ኤርትራ ወደ ባድመ እንድትገባ ማን እንደወሰነ በግልጽ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ጠቅሷል። የባድመን ጉዳይ ከፍተኛ ባለስልጣናት በጋራ ተሰብስበው እንዳልወሰኑትና የሚያውቁትን ነገር እንደሌለ ጨምሮ ይጠቅሳል። እንዲያውም ስለባድመ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የሀገሪትዋን ጸጥታና ድሕንነት በሚመለከቱ ገዳዮች ሌሎች ባልደረቦቹን ሳያማክር በተግባር ራሱ ኢሳያስ ለብቻው እንደሚወስን በሰጠው ቃለ ምልልስ አክሎ ገልጸዋል። (ዳን ኮነል: ገጽ 101) ጴጥሮስ ሰሎሞንም በበኩሉ፡ ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ግጭት በሚመለከት፡ ከጀነራል ዑቕበ አባባል ጋር የሚስማማ ምስክርነት ሰጥቷል። ለምሳሌ በ1995 መጀመሪያ ላይ ኤርትራ ከሱዳን ጋር የነበራትን ዲፕሎማስያዊ ዝምድና ስታቋርጥ፡ ጴጥሮስ ሰሎሞን፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሆኖ ለስራ ጉዳይ በውጭ በነበረበት ጊዜ እንደህዝበ ዓለሙ በወሬ ብቻ ነበር የሰማው። (ዳን ኮነል: ገጽ 128)

Addis. <u>This is in fact another trap</u>! It is meticulously designed by Tigray-Tigrinya leaders to control, monitor and finally sabotage the activities of both opposition groups before they strike. In the last ten years or so opposition group's agenda of freedom and democracy has not moved an inch forward due to the manipulation of Tigray-Tigrinya security agents. TPDM (DMHIT), whose main task is to protect and serve the empire of Tigray-Tigrinya, is the only group who is making a substantial progress in power and number. TPDM has been training in a secret location in Eritrea for the last 20 years since 1991 and is directly financed by Isayas Afeworki."[44]

**በአማርኛ ሲተረጎም፤**

> *"የኤርትራ ተቃዋሚ ቡድኖች ጸረ የአስመራ መንግስት ለመዋጋት በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በመሰልጠንና በመታጠቅ ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችም በተመሳሳይ በአዲሰ አበባ ያለውን መንግስት ለመዋጋት በኢሳያስ አፍወርቂ መመሪያና የገንዘብ ድጋፍ ሲንቀሳቀሱ ይገኛሉ። <u>ይህ ወጥመድ ነው።</u> ይህም እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች ጥቃት ከመፈጸማቸው በፊት፡ የሁለቱን ሀገሮች ተቃዋሚ ቡድኖች እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር፡ በመጨረሻም ለማደናቀፍና ለማኰላሸት ተብሎ በትግራይ ትግርኚ መሪዎች በጥንቃቄ የተቀየሰ ነወ። ላለፉት አስር ዓመታት ያህል፡ ስውር የትግራይ-ትግርኚ ሰላዮች በፈጠሩት መሰናክል ምክንያት፡ ተቃዋሚዎች የሚያካሂዱትን የነጻነትና የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ፡ አንድ ስንዝር እንኳን ወደፊት መራመድ አልቻለም። በቁጥርም ሆነ በኃይል ትልቅ ዕድገትና ግስጋሴ እያሳየ ያለው ቡድን ደምህት ብቻ ነው። የደምህት ዋና ተግባር (ተልእኮ) ደ ግ ሞ ፡ የትግራይ-ትግርኚን ግዛት መጠበቅና ማገልገል ነው። ደምህት፡ ከ1991 ጀምሮ ላለፉት 20 ዓመታት በአንድ ባልታወቀ የኤርትራ ቦታ ሲሰለጥን የቆየ ሲሆን፡ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ የሚያገኘው በቀጥታ ከኢሳያስ አፍወርቂ ነው።"*

ከላይ የተጠቀሰው የአዲስ ዘመን አባባል መሰረትና ቁም ነገር ያለው ነው። ትግራይ-ትግርኚ የጋራ ዕቅድና አላማ አድርገው የሚጓዙ፡ ኢሳያስና ወያኔ በየበኩላቸው የኢትዮጵያንና የኤርትራን ተቃዋሚ ቡድኖች በቅርብ በመቆጣጠር መራመድ የማይችሉ ሽባ ሆነው እንዲቀሩ እያደረጉዋቸው ይገኛሉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ፡ ምናልባት ግን አይታወቅም፡ በሂደት የኢሳያስና የወያኔ ግንኙነት መስተካከል ያስፈልገው ይሆናል። ኢሳያስ ብርቱ የስልጣን ስስ ያለበት ሰው ነው፤ ስልጣን ለኢሳያስ የዓይን ብሌን ነው። በዚህ ምክንያት ከወያኔ ጋር ችግር ሊፈጠር ይችላል። ችግሩ ከባድ ሆኖ ወያኔ ኢሳያስን ከመንበረ ስልጣኑ ለማስወገድ ቢገደዱ የትግራይ-ትግርኚን ዕቅድ የሚቀበሉ ከሃዲያን ኤርትራውያን እንደ አማራጭ መልምለው ካዘጋጁ በኋላ ብቻ ነው። እንዲያውም እንዲህ የመሰሉትን ቡድኖች እያዘጋጁ ናቸው የሚል ጭምጭምታ እየተናፈሰ ይገኛል። ይህንን ዝግጅት የሚያጅቡ ከፖለቲካ ንቅናቄዎች ነጻ ነን

44. Addis Zemen

የሚሉ የትግርኛ ተናጋሪ የሆኑት ኤርትራዉያንና ተጋሩ ስብስቦች እየተሰማሩም ይመስላሉ[45]።

ወጣም ወረደም! መሰረታዊ ቁም ነገርና ዋናው ነጥብ አንድና አንድ ብቻ ነው። እሱም የወያኔ መንግስት፡ የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች ነጻ ሆነው በመንቀሳቀስ፡ ኢሳያስን ከስልጣን እንዲያስወግዱ የሚያስችልና ወንዝ የሚያሻግር ድጋፍ ለማድረግ አይፈልግም። ከ2001 ጀምሮ በተጨባጭ ያየነውና የታዘብነውም ይህንን ነው የሚያረጋግጠው።

## ፰፡ የወያኔ መንግስትና የኤርትራ ተቃዋሚዎች ዝድምና

የወያኔ መንግስት በረቀቀና ጥበብ በተሞላበት አኳሃን የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ሽባ ሆነው እንዲቀሩ አድርጓቿል። በ1998-9 ተደርሶ የነበረውን ስምምነትና መረዳዳት ከድቶ፡ ድርጅቶቹን ከቁጥጥሩና ከራሱ ፈቃድ ውጭ አንድ ስንዝር እንኳን ወዲፊት ሊራመዱ የማይችሉ፡ ረጭ ብለው የሱን ትእዛዝ ተቀባዮች እንዲሆኑ አድርጓቿል።

(1) የወያኔ መንግስት እነዚህ የተለያዩ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች በመካከላቸው ደልዳላ አንድነት እንዳይፈጠርና የኢሳያስ መንግስትን የመቃወም ዓቅማቸው እንዳይጠነክር፣ ጨካኝና ሰይጣናዊ ስልቶቹን በረቀቀ መላ ተግባር ላይ አዋለ። አፍራሽ ተግባራቱን እውን ለማድረግ ከተጠቀመባቸው ስልቶች ውስጥ ትልቁ፡ ከላይ ከውጭ ስታየው የአንድነትን መንገድ የሚመስል፡ በተግባር ግን ድርጅቶቹን የሚበታትኑ፡ ቅራኔን የሚያባብሱና የተቃውሞ ጎራውን እየዋለ እያደሩ እንዲከስም የሚያደርጉ፡ የተለያዩ ጉባኤዎችንና ስብሰባዎችን ማዘጋጀትና ማሰማራት ነው።

ይህ የወያኔ ስልት፡ በመልኩ አንድ የግሪኮች አፈ-ታሪክ የሆነን አባባል ያስታውሰናል። ይህ የግሪካውያን አፈ-ታሪክ፡ በአንድ "ሲሲፉስ" በተባለ ንጉስ ላይ የተፈጸመ ከባድ ቅጣትን የሚያወሳ ነው። በንጉሱ ዘመን፡ የግሪክ ህዝብ ጣዖታትን ያመልክ ነበር፤ በወቅቱ ትልቁና ሐይለኛው ጣዖት ዘዩስ ይባል የነበረው ነው። ንጉስ ሲሲፉስ፡ ስልጣኑን ለመጠበቅ ሲል፡ ብዙ በደሎች ፈጽሞ ስለነበረ በጣዖት ዘዮስ ከበድ ያለና ልዩ ቅጣት ተበየነበት። እሱም ንጉስ ሲሲፉስ፡ ትልቅ የአለት ፍላጭ ከአንድ ዘምበል ካለ ተራራ ስር እየገፋ ወይም እያንከባለለ ወደ ተራራው ጫፍ እንዲወስደው ነበር። ሲሲፉስ፡ እንደተፈረደበት አለቱን እየገፋ በተራራው ጫፍ ላይ ካደረሰው በኋላ፡ ጣዖት ዘዩስ በነበረው መለኰታዊ ኃይል አለቱን ተመልሶ ወደታች እንዲንከባለል አደረገ። ሲሲፉስም፡ እንደገና አለቱን ከስር ወደላይ እየገፋ እተራራው ጫፍ አደረሰው። በጣዖት ዘዩስ ኃይል፡ አለቱ እንደገና ተመልሶ ወደታች ተንከባለለ። ደጋግሞ ሲሲፉስ ወደ ላይ ይገፋል፡ አለቱም ደጋግሞ ወደ ታች ይንከባለላል። ይህ ዓይነት የድግግሞሽ ሁኔታ፡ ለሲሲፉስ ትዕግስት አስጨራሽ ሆነ።

45. በ2010 ገደማ በትግራይ የተቋቋመው 'የትግርኛ ቤተ-ሰቦችና አጎራባች ብሄሮች የሰላምና የወንድማማችነት ማሕበር" የሚባል አካል የዚሁ ስብስብ ማሳያ ተደርጎ ሊጠቀስ ይቻላል። የዚሁ ማሕበር አባላት ሊሆኑ የሚችሉ የ"ብሄረ ትግርኛ ሰዎች መሆናቸው የሚታወቅ ኤርትራውያንም ኢትዮጵያውያንም" ናቸው ሲል የማሕበሩ ሕገ ደንብ ያስረዳል። በሕገ ደንቡ መሰረት የብሄረ ትግርኛ "ቋሚ ጥምረት" አመርቂ እንዲሆን ጥረት ከሚደረግላቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። "የትግርኛ ቤተሰቦችና አጎራባች ብሄሮች የሰላምና የወንድማማችነት ማሕበር" (2010)

ንጉሱ ማለቂያ በሌለው እየተደጋገመ ወደኋላ በሚመለስ ጥረት ተበሳጭቶና ተስፋ ቆርጦ፡ ኩምትር ብሎ ቀረ። ከዚሁ አፈ-ታሪክ በመነሳት ማለቂያ የሌለውና፣ ይቀናል ሲባል እንደገና መልሶ መላልሶ ወደኋላ የሚንከባለል ወይም መፍትሄና መውጫ የሌለው አዙሪት ነገር፡ ሲሲፋዊ (sysphean) ተብሎ ይገለጻል።

እነዚህ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሲሲፈያን ዓይነት ስልት ሰለባ ሆኗል። ስምረት ወይም ሕብረት ለማድረግ ተቃርቧል ይባልና ከትንሽ ጊዜ በኋላ መነሻው ይህ ነው ተብሎ በማይታወቅ ነገር፡ አለመግባባትና ንትርክ ይፈጠራል። ስለዚህም፡ ተጀምሮ የነበረው መቀራረብና መሰባሰብ ይበተናል። እንደገና ደግሞ ጉባኤ ኮንፈረስ ጂኒ ጃንካ ተብሎ መሰባሰብ ይደረጋል፤ ተመልሶ እንደተለመደው ብትንትን ይላል። የዚሁ የመሰባሰብና መልሶ የመበታተን አዙሪት፡ ከሂደቱ በስተጀርባ ሆኖ የሚያሽከረክረው ደግሞ ያው ዞሮ ዞሮ ወያኔ የተባለው ኃያል ጣዖት ነው። በተጨባጭ ለመናገር፡ ወደኋላ መለስ ብለን ከ1999 ጀምሮ ያለውን የኋሊት ጉዞና ውጣ ውረድ ስናየው፡ ቀደም ሲል ህብረት ("ምሕዝነት") ተቋቋመ፤ በኋላ ህብረቱ ፈርሶ 4+1 መጣ፤ ቆይቶ 4+1 ፈርሶ ኪዳን የሚባል መጣ፤ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ኪዳንም ተፈረካከሰ፤ ከዚያም እንደገና በማደስና በማስተካከል ሌላ አዲስ ኪዳን መጣ፤ ይህ አዲስ ኪዳንም ጨርሶ ባይጠፋም እየተዳከመና እየከሰመ ሄደ፤ ከኪዳን መዳከም በኋላ፡ የሀገራዊ ጉባዔ ኮሚሽን ሞቅ ባለ ዳንኪራ ታጅቦ ብቅ አለ፤ እሱም እንዴ ብቅ ብሎ ጠፋ። ከዚህ ሁሉ ጥረትና ውድቀት በኋላ ባይቶ የሚባል መጣ፤ ባይቶም እንጃ፡ የተስተካከለና የተረጋጋ አካሄድ ተከትሎ እየተጓዘ አይመስልም፤ ምናልባት ቀደም ብለው የነበሩትና የከሰሙት ስብስቦች ዕድል ሳያጋጥማው አይቀርም። ይህ የመሰባሰብና የመፈረካከስ አዙሪት የተቃዋሚ ኃይሎችን ጎራ በጣም ጎድቶታል። አንድ የተጀመረ ስብስብ ሲፈርስ ብዙ ሰው ተስፋ በመቁረጥ ትግሉን ይተዋል። ይህ ዓይነቱ ችግር ሲደጋገም፡ ትግሉ እየከሳና እየተመናመነ ሄዶ በመጨረሻ ይከስማል። ይሞታልም።

(2) ከዚህ ስልት ጋር ተያይዞ አንድ የግድ መጠቀስ ያለበት ክስተት አለ። እሱም የድርጅቶች መከፋፈልና መራባት ነው። ድርጅቶቹ በየጊዜው እርስ በራሳቸው እየተራቡ እየተራቡ መጥተው በአሁኑ ጊዜ ትርኪ-ምርኪውን ጨምሮ በቁጥር ከ30 በላይ ሆኗል። ይህ የድርጅቶች መራባት በሽታ፡ የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎችን የሚያዳክም ስለሆነ ወያኔም ይፈልገዋል። እንዲያውም ይገርማችኋል!! አንዳንድ ድርጅቶችንማ ራሳቸው ወያኔ ናቸው በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር አሰባስበው የሚጠፈጥፏቸውና የሚያደራጇቸው። ወያኔ ረዘም ላለ ጊዜ በነዚህ የኤርትራ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች መካከልም አድልዎ እያደረጉ መጥቷል። ለምሳሌ የኤርትራን አንድነትና ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል፡ የብሄር ብሄረ ሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚል አጀንዳ አንግበው የሚንቀሳቀሱ አናሳ ድርጅቶችን ልዩ ትኩረት በመስጠት የተለየ ድጋፍና መተባበር ያደርጉላቸዋል። በአንጻሩ፡ ሕብረ ብሄራዊ (ሀገራዊ) መልክና አቋም ያላቸው ኤርትራውያን ድርጅቶችን ደግሞ ዝቅተኛ ግምት በመስጠት ይጐዷቸዋል። እነዚህ ድርጅቶች በጥቃቅን፡ መለስተኛ ጉዳዮችና ችግሮች ላይ እንዲጠመዱ ለማድረግ፡ ወያኔ የሚፈጽመውን ሴራ ብዙ ተዋኒያን አስተውለውታል። አሁንማ ይባስ ብሎ ታች የወረደ አውራጃዊና ጎጣዊ ይዘት ያለው በሚመስል መስመር፡ አንዳንድ ድርጅቶች እየተከፋፈሉ መሆናቸውን ስንመለከት በእውነቱ እያፈርን እያዘንና እየሰጋን ነን።

ወያኔ፡ ይህን ዓይነቱን ተንኰል እየሰራ የሚገኝበት ዋናውና ትልቁ ምክንያት፡ ከላይ አስቀድሜ በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት ሁሉ የኤርትራን ነጻነት፡ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚቃረን ዕቅድ ስላለው ነው። በመሆኑም!! በዚሁ ጉዳይ ላይ በማያወላዳ መልኩ በግልጽ መነገር ያለበት አስፈላጊ ነጥብ አለ። እሱም፡ ከወያኔ ጋር ስትራተጂካዊ ዝምድናም ሆነ ቅርበት አለን በማለት የወያኔ ግንባር ቀደም ደጋፊዎች ሆነው ከጎናቸው ተሰልፈው እየሰሩ ያሉት ኤርትራውያን ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኢሳያስ መንግስትንም እየደገፉ፡ ከዚያም በላይ ደግሞ የሀገር ክህደትም እየፈጸሙ መሆናቸውን ሊያውቁት ይገባል።

አንዳንድ የነዚህ አፍቃሬ ወያኔ የሆኑት ድርጅቶች አባላት፡ ወያኔ ሲደግፉን ለራሳቸውም ጥቅም ብለው ነው በማለት ያምናሉ። የወያኔ ተግባራትን ተቀባይነት እንዲኖራቸው ልባስ ለመስጠት ሲባል፡ ሌላ ውሃ የማይቋጥር የመከራከሪያ ምክንያት ያመጣሉ። ምን ይላሉ? "ማንኛውም መንግስት ወይም ሌላ የተደራጀ አካል እርዳታ ሲሰጥህ ሁሉ ጊዜ የራሱን ጥቅምም እያየ ነው፤ ወያኔም ሲያግዙን ለጥቅማቸው ብለውም ቢሆን የሚያስገርም አይሆንም፤ ፖለቲካ ያው እንደዛ ነው" ይላሉ። ይህ አባባል ለራሱ ሌላ አንድ አስፈላጊ ነጥብ የሚያሰነሳ ነው የሚሆነው። እውነት ነው፡ አንድ መንግስትም ሆነ ድርጅት ለራሱ ጥቅምም ብሎ ነው እርዳታ የሚሰጥህ፤ ይሁን እንጂ፡፡ እንዲዚህ ዓይነት የመረዳዳት ዝምድና፡ ተቀባይነትና ብልህነት የሚኖረው የእርዳታ ሰጪው መንግስት ጥቅም ፍትሓዊ - ላንተም ሆነ ለሌላ ወገን የማይጎዳ - ሲሆን ብቻ ነው። ወያኔ ለነዚህ ድርጅቶች እርዳታ ብሎ የሚጠራውን ትንሽ ትንሽም ቢሆን ሲለግስላቸው፡ የራሱ ጥቅምስ ምንድን ነው? ጥቅሙስ ፍትሓዊ ነው ወይ?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠታችን በፊት በቅድሚያ ወያኔ ኤርትራውያን ተቃዋሚዎችን ሲያግዝ ጥቅሙ ምን መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልገናል። ወያኔ የሚያገኛቸው ዋና ዋና ጥቅሞች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያውና መሰረታዊ የሆነ ጥቅሙ፡ የኢሳያስ መንግስትን የሚመለከት ነው። ወያኔ ለነዚህ ድርጅቶች "እገዛ" እየሰጠ በቁጥጥሩ ስር በማስገባት፡ ኤርትራን የሚመለከት የሩቅ አላማውን በሚነካ መንገድ ጸረ የኢሳያስ መንግስት እንደማይንቀሳቀሱ አድርጓቿል። በሌላ አነጋገር የሩቅ ዕቅዱን በሚያናጋ አገባብ የኢሳያስን መንግስት በጠነከረ ወይም ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዳይታገሉትና እነሱም ከማንም ተጽዕኖ ነጻ ህልውና ይዘው በመንቀሳቀስ፡ በኤርትራ ስልጣን ለመያዝ እንዳይችሉ አድርጓቿል። ይህ ጥቅም ፍትሓዊ አይደለም። ኤርትራ ምንም ለውጥ ሳይኖራት፡ አሁን እንዳለቺው ገሃነም ሆና እንድትቀጥል የሚያደርግ ነው።

ሁለተኛው ጥቅሙ፡ እነዚህ የኤርትራ ድርጅቶች፡ የኢትዮጵያን ውስጣዊ ጉዳይ በሚመለከት፡ ለወያኔ የሚረዳ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ መሆናቸው ነው። የነዚህ ድርጅቶች ከፍተኛ ካድሬዎችና ተራ አባላት፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ለወያኔ በስለላ ስራ የተሰማሩ እንዳሉ የታመኑ መረጃዎች አሉ። በዋናነትና በአመዛኙ የተሰማሩት ግን፡ በፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ስራ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን "ትምክሕተኞች" እያሉ ስም የሚያጠፉ አንጋፋ ኤርትራውያን ካድሬዎች አሉ። ለምሳሌ ወያኔ ሶማሊያን በወረረበት ጊዜ "እነዚህ ጂሃዳውያንን አሳይቷቸዋል" እያሉ ወያኔን ሲያወድሱ የተሰሙ አንዳንድ የኤርትራ ድርጅቶች መሪዎች አሉ። ከዚህም አልፈው፡ የወያኔ ወይም የኢሕአዴግ አፈ ቀላጤ በመሆን "ኢሕአዴግ" ዲሞክራስያዊ ነው፤ የልማት ዕድገት እያመጣ ነው፤ በተለይም የትግራይ ህዝብ ህይወት እየተለወጠ ነው፤ ወዘተ እያሉ

ለወያኔ የፓለቲካ ምሕዳር ጥብቅና በመቆም፡ ጮኽ ብለው የሚያወድሱና የሚንቀሳቀሱ አሉ። ለምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከኤርትራውያን ድርጅቶች ውስጥ በአመራር ደረጃ ላይ የነበረ አንድ ሰው "በትግራይ ያለው ዕድገት አስቀናኝ፤ 99% የትግራይ ልጆች በትምህርት ገበታቸው ይገኛሉ" ሲል ተሰምቷል። ስለዚህ፡ እነዚህ ተቃዋሚ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያሰራጩት ፕሮፓጋንዳና የሚያካሂዱት ስለላ፡ ወያኔን በስልጣን ላይ ለማቆየት የሚረዳ ነው።

ወያኔ በስልጣን ላይ ተቀምጦ ምን እያደረገ ነው ያለው? የሚያደርገውስ ፍትሃዊ ነውን?

ብዙዎች የወያኔ ደጋፊ የሆኑ ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄዱ ያሉትን የመሰረተ ልማት ስራዎች - ማለት መንገዶችንና ህንጻዎችን የመሳሰሉ - በመጥቀስ ትልቅ ዕድገት ተመዝግቧል እያሉ የወያኔን መንግስት አጉልተው ያመጉሳሉ። አንዳንዱማ፡ ዴሞክራሲንና የሰብአዊ መብት አያያዝን በሚመለከትም፡ ወያኔ የሚወቀስበት ነገር የለውም ለማለት ይቃጣል። እውነት ነው፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚመሰገን የመሰረተ ልማት ስራ እየተፋጠነ ይገኛል፤ ነገር ግን ይህንን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት፡ ሁለንትናዊ ዕድገት አለ ብሎ በደፈናው መናገር ቀላልና ያልበሰለ ፍርድ ነው። ከዚህ ተነስቶ የወያኔን መንግስት ማወደስ ደግሞ፡ እንደየሁኔታው፡ ዓቢይ ስህተት ወይም ለሰሚ ማደናገር ነው።

የመሰረተ ልማት ስራ ራሱ በባህሪው ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፡ የሚሰራው ሁሉ ለህዝቡ ጥቅም ተብሎ ነው ለማለት አይቻልም። አውሮጳውያን፡ በአፍሪቃ ቅኝ ግዛታቸውን ለማስፋፋትና ለመትከል ሲሉ ባህር ተሻግረው በመጡበት ጊዜ፡ አንዳንድ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲዘረጉ አድርጓል። ለምሳሌ፡ ኢጣሊያኖች በኤርትራ ለጥቅማቸው ሲሉ ከተሞችና መንገዶች ሰርቷል። እኛ - ማለት የኤርትራ ህዝብ ግን - የዘረኝነት ሰለባ ሆነን በተወሰነ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር ልንጠቀምባቸው አይፈቀድልንም ነበር።

በአንድ አገር የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ ስላለ የዴሞክራሲ ጥያቄ መነሳት የለበትም ማለት አይደለም። የህዝቡ ኑሮ ተሻሽሏል ማለትም አይደለም። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እውነታም የሚያሳየን የአብዛኛው ህዝብ ኑሮ በጣም ዝቅተኛና በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ እንዳለ ነው። በሕብረተ-ሰቡ ውስጥ ያለው ድህነት የመጨረሻ የከረፋ ነው። ለምሳሌ፡ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ እንደ ደንቡ መጣል የሚገባው ከምግብ ቤቶች የሚጠራቀመው ፍርፋሪ ለድሆች እንደሚሸጥ ይታወቃል[46]። ስለዚህ፡ ተጨባጭ ሁኔታው እንዲህ እያለ ተተከለ የተባለው የመሰረተ ልማት ስራ ለሰፊው ህዝብ ብዙም ትርጉም የለውም።

---

46. ኤርምያስ ለገሰ በቅርቡ ባሳተመው መጽሓፉ ውስጥ ከምግብ ቤቶችም ሆነ ከሌላ ተጠራቅሞ መጣል የሚጋባው የምግብ ፍርፋሪ የሚሸጥ መሆኑን አስመልክቶ እንደሚከተለው ይላል፤ "መሀል መርካቶ ጉርሻ ይሸጥ የለ። እጅ ሞላ ያለ አንድ ብር፤ እጀ ጎደሎ ደግሞ ሀምሳ ሳንቲም!!.... የሁለት ምርጫዎች ወግ' የአፍሪካ ነብር !' ብሎ የሰየመሽ አዲሲቷ ኢትዮጵያ የት ነው ያለሽው? ይህን ውርደት ሰምተሽ ይሆን?" ኤርምያስ ለገሰ፡ ግንቦት 2014 (ግንቦት 2006 ግ.አ.) ገጽ 94።

በተጨማሪም አንድ መረዳት ያለብን ትልቅ ነጥብ አለ። እሱም፡ በመካሄድ ላይ ነው የተባለው የመሰረተ ልማት ስራ፡ ወያኔ ስልጣኑ ተቀባይነት እንዲኖረው ወይም ስልጣኑን በሞኖፖል ለመያዝ እንደ አሳማኝ ምክንያት የሚጠቀምበት መሆኑ ነው። ስለዚህ፡ ባንድ በኩል ሲታይ፡ ይህ የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ ስኬት፡ ወያኔ ህዝቡንና የውጭ ሀገር ታዛቢዎችን ለማታለልና አምባገነናዊ ስርአቱም ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀምበት የማታለያ መሳሪያ ሆኖ ይገኛል።

ወያኔ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ስልጣን በሞኖፓል ይዞ በመግዛት፡ ማንኛውንም አገባብና ስልት ተጠቅሞ ገደብ የሌለው ሀብት ለማከማቸትና ለመዝረፍ ነው ፍላጎቱ። ይህን ገደብ አልባ ፍላጎቱን ለሟሟላት ደግሞ፡ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች መሰረታዊ መርሆችን በአስገራሚ መልኩ እየጣሰ ይገኛል[47]። እያካሄደ ያለው ዓይን ያወጣ የሙስና ብክለት፡ (ኮራፕሽን) ምን ያህል የሚያንገሸግሽ መሆኑን ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ፡ እንደዛ ለግልጽነት የቆመው ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የመሳሰሉ አለምአቀፋዊ ጸረ-ብክለት ድርጅቶችም፡ አጋልጠውታል[48]። ይህ ብቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ድንግል መሬት፡ በተለይም በኦሮሚያና በጋምቤላ የሚገኘውን፡ በጣም አነስተኛ በሆነ ኪራይ ለባዕዳን ኩባንያዎች ሽጠው ሀገር-ብቀል የሆነውን ነዋሪ ህዝብ አፈናቅለው የኑሮውን መሰረት ነጥቀውታል[49]።

ወያኔ የኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነትንም እየሸረሸሩት ነው። በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ክፍል የሚገኘው የሚታረስ ለም መሬት፡ ለሱዳን ለማስረከብ እንደወሰኑ እነሱም ራሳቸው አምኗል። ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማርያም ደሳለኝ፡ ታሕሳስ 3, 2013 ወደ ካርቱም ሄዶ በነበረበት ጊዜ፡ ባለ13 ሰነድ ውሎች ፈርሟል። ከ13ቱ ሰነዶች ውስጥ አንዱ፡ በሱዳን "ፋሻጋህ" ብለው የሚጠሩት 250 ካሬ ኪሎ ሜትር የሚያህል ስፋት ያለውና ቀደም ሲል ይዞታው በኢትዮጵያውያን እጅ የነበረ የእርሻ ለም መሬት ለሱዳን እንዲሰጥ ይደረጋል[50]። ሌሎች ኢትዮጵያውያን ግን፡ ለሱዳን እንዲሰጥ የተባለው መሬት ስፋቱ ከ250 ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ እንደሆነ ይጠቁማሉ[51]።

የውጭ ዲፕሎማሲን በሚመለከት ደግሞ የወያኔ መንግስት በዋናነት የኢምፔሪያሊዝም ተላላኪና ጉዳይ ፈጻሚ በመሆን፡ ጸረ ሽብርተኝነት በሚባለው ጉዳይ ተሰማርቶ ይገኛል። ይህንን የወያኔን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት፡ ሪቻርድ ደውደን የሚባል ጸሐፊ፡ ነብሰሄር መለስ ዜናዊን በአፍሪቃ ቀንድ እንደ የአሜሪካ "ዘበኛ" ወይም "ፖሊስ" አድርጎ

47. . Rene Lefort, "Ethiopia: a Leadership in disarray",
48.. በ 2013 ብልሹነትን በሚመለከት በትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል አማካኝነት በተደረገው ግምገማ መሰረት ከ175 ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ 111ኛ ሆና ተገኝታለች፣ ኢትዮጵያ፡ 160ኛ ሆና ከተገመተችው ኤርትራ የተሻለች ብትሆንም፡ በብልሹነት ከተበከሉት አገሮች አንዷ ናት ተብላ ነው የተገመተችው። Transparency International 2013: Corruption Perceptions Index
49. ሪቻርድ ደውደን በግንቦት 2012 በጻፈው አንቀጽ ላይ የመለስ መንግስት ከ 4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ለም መሬት ለውጭና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አከራይቷል ይላል። Richard Dowden May 21, 2012
50. ሪቻርድ ደውደን በግንቦት 2012 በጻፈው አንቀጽ ላይ የመለስ መንግስት ከ 4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ለም መሬት ለውጭና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አከራይቷል ይላል። Richard Dowden May 21, 2012
51. የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ፡ ለሱዳን የሚሰጠው መሬት ርዝመቱ 1000 ኪሎ ሜትር: የጎን ስፋቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር መሆኑን ይገልጻል። የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ፡ መግለጫ ግንቦት 1 2000 ዓ. ም. *አ. ግዕዝ* (May 9, 2008).

ይገልጸዋል[52]። በኢትዮጵያ ውስጥ ልዩ ስሙ አርባ-ምንጭ የሚባል ከተማ የአሜሪካ "ድሮንስ" (ሰው-አልባ ተዋጊ አውሮፕላን) ጦር ሰፈር ሆኖ ይገኛል። የጥቁር ህዝብ ኩራትና የነጻነት ተምሳሌት ተደርጋ ስትታወቅ በነበረችው ኢትዮጵያ፡ ይህን ዓይነት ወራዳ ክስተት ማየት እጅጉን የሚያሳዝን ነው።

ወያኔዎች የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት እየዘረፉ፡ እንዲሁም ለውጭ ዓለም አዛገሮቻቸው በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት በእርዳታ መልክ የሚያገኙትን ገደብ የሌለው የገንዘብ መጠን - በዓመት እስከ 4 ቢሊዮን የሚገመት የአሜሪካ ዶላር - በመሰብሰብ ሀብት አከማችቷል[53]። እንዲሁም ከወያኔ ጋር የቅርብ ትስስር ያላቸው ጥቂት ተጋሩ፡ በጉቦና በስርቆት በተከማቸ ሀብት በቁጣን ተይዘው እንዳሉ ብዙ ሰው ያውቀዋል። ነገር ግን፡ ምንም እንኳን ትግራይ፡ እንደ መንገዶች፡ ህንጻዎችና ከተሞች የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት ዕድገቶች አወንታዊ ገጽታ የሚታይበት አካባቢ ቢሆንም፡ አብዛኛው የትግራይ ሰፊው ህዝብ፡ ልክ በሌላው የኢትዮጵያ ክፍሎች እንደሚኖረው ህዝብ፡ የከፋ ህይወት እየገፋ ነው ያለው።

ወያኔ፡ ከኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በጎን ልዩ ዝምድና የመሰረተበት ምክንያት፡ ከላይ የተጠቀሱትን ገንዘባዊና ፓለቲካዊ ጥቅሞች ለመጠበቅ ሲል ነው። እነዚህ ጥቅሞች ፍትሓዊ እንዳልሆኑ ደግሞ እሙን ነው። ስለዚህ፡ እነዚህ ፍትሓዊ ያልሆኑትን ጥቅሞች የሚያገለግል እስከሆነ ድረስ፡ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከወያኔ ጋር ያላቸው ዝምድና የሚደገፍ አይደለም።

አስቀድሞ እንደተገለጸው፡ ወያኔ በህዝብና በሀገር ላይ እየፈጸመ ባለው ግፍና ዓይን ያወጣ ዝርፊያ ምክንያት፡ በኢትዮጵያ እጅጉን እየተጠላ በመሄድ ላይ ያለ ነው። ከዚህ የተነሳ ብዙዎች እስካሁን ድረስ ወያኔን በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው መታገል ያለብን ሲሉ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች፡ በአሁኑ ጊዜ ሀሳባቸውን እየቀየሩ ናቸው። በሰላማዊ ትግል ምክንያት ብቻ ወያኔ ስልጣኑን ለሌላ አካል ለማስተላለፍ ፈጽሞ ፍላጎት የለውም ብለው ደምድሟል። ከዚሁ ድምዳሜ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት የሚቻለው ሰላማዊና የትጥቅ ትግል በማጣመር ሲካሄድ ነው እያሉ ይገኛሉ[54]።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች - እንዲያውም በሀገሪቱ የሚኖሩ ኤርትራውያን በጠቅላላ - በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ የወያኔ ስርዓት ተከታዮችና አገልጋዮች ተደርገው ነው የሚታዩት። ለምሳሌ ሩቅ ሳንሄድ፡ ትግራይ ውስጥ ካሉት ኤርትራውያን መሀከል የወያኔ ተቀናቃኝ የሆነውን "የዓረና ትግራይ ፓርቲ" አባላትን በማጥቃት ላይ ተሳትፏል ተብለው የተከሰሱ አሉ[55]። ይህ ውሎ አድሮ ለኤርትራውያን እጅግ አደገኛ ነው።

---

52. Richard Dowden ዝኒ ከማሁ
53. ሪቻርድ ደውደን ዝኒ ከማሁ
54. ለአብነት ያህል Messay Kebede (August 27, 2014) ተመልከት።
55. ዓረና ትግራይ ፓርቲ ቅጻሜ ጥር 17 ቀን 2006 ዓ.ም. (በግእዝ አቆጣጠር) ማግስት በዓዲ ግራት ህዝባዊ ስብሰባ በሚቀጥለው ቀን ለማካሄድ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ እንቅስቃሴ ይደረግ በነበረበት ጊዜ ዓቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆችና ወጣቶች ተሰባስበው እነ አቶ አስገደ ገብረስላሴና አቶ አብርሃ ደስታ የሚገኙባቸው የፓርቲውን አንጋፋ አባላት በድንጋይና በዱላ አጠቁዋቸው። የከተማው ፓሊሶች በቅርብ ርቀት ሆነው ድርጊቱን ሲመለከቱ የነበሩ ቢሆንም፡ በአጥቂ ቡድኖች ላይ

ከወያኔ ጋር ሊኖር ስለሚገባው ዝምድናን የሚመለከት አንድ መሰረታዊ ነጥብ አለ። እሱም ከአንድ መንግስት ወይ ድርጅት ጋር የምታደርገው ዝምድና፡ ጥቅም ለማግኘት ብለህ መሆኑ ነው። በሌላ አነጋገር የሚደረገው ዝምድና የመተባበር ነው። ይህ ማለት ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ጥቅሞቻቸውን ለማራመድ ይተጋገዛሉ ማለት ነው። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ፡ በወያኔና በኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች መሀከል ያለው ዝምድና ግን፡ ይህንን መሰረታዊ መርሕ የተከተለ አይደለም። በግልጽ ለመናገር! የወያኔና የኤርትራ ድርጅቶች ዝምድና ባህርያት የባለቤትና የጥገኛ ወይም የጌታና የሎሌ ዓይነት ነው። ዝምድናው በእኩልነትና በጋራ ተጠቃሚነት መርሕ ላይ የተመሰረተ አይደለም። በአጠቃላይ የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች በወያኔ ቁጥጥር ስር የገቡ፡ ከወያኔ ፈቃድ ውጭ የማይንቀሳቀሱ አውቶኖሚ ወይም ነጻነት የሌላቸው ናቸው።

ይህንን ሀቅ ማመን አቅቷቸው፡ "ያን ያህል ወድቀናል እንዴ " የሚሉ አንዳንድ ኤርትራውያን አይታጡም ይሆናል። ግን በእርግጠኝነት ወድቀናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ መጠቀስ ያለበት ሌላ መሰረታዊ ነጥብ፡ ወያኔ እጅጉን እንደናቀን ነው። ይህ እሬት እሬት የሚል መራራ ቃል ቢሆንም፡ ወደድንም ጠላንም መቀበል ያለብን ሀቅ ነው። ወያኔ እኛ ኤርትራውያንን ቢንቁ እውነታቸው ነው። ከኛ 14 ዓመት ቆይተው የትጥቅ ትግል ጀምረው፡ ተ. ሓ. ኤ. (ጀብሃን) ከኢሳያስ ጋር አብረው ከኤርትራ የትግል ሜዳ አባርረው፡ ትግላችንን ጠልፈው ይህው በአቋራጭ በኢትዮጵያ ነገሱ። አሁን ደግሞ ይባስ ብለው፡ ብዙ የኤርትራ የፓለቲካ ድርጅቶችንና ተዋንያንን የራሳቸው አገልጋዮች፡ ተላላኪዎችና ቅጥረኞች አድርጓቸው ይገኛሉ። ታዲያ፡ ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ!! ወያኔ እኛ ኤርትራውያንን ካልናቁ ሌላ ማንን ይናቁ!!

የወያኔ መሪዎችና ወኪሎቻቸው በኛ ላይ ያላቸውን ንቀት በተለያየ መልክ ያንጸባሩቁታል። አቶ ስብሃት ነጋማ በኤርትራውያን ላይ ያለውን ንቀት በጋሃድ ነው የሚናገረው ማለት ይቻላል። በተለያዩ አጋጣሚዎች፡ በይዘቱ "ለኤርትራ እኛ ነን ጥብቅና የቆምንላት፣ ለኤርትራ ነጻነት ከኤርትራውያን ድርጅቶች በላይ ታግለናል፣ ኤርትራ በኛ ትግልና ጽናት ነው ነጻነቷን የተጎናጸፈቺው፣" የሚል አነጋገር እኮ፡ ያላንዳች ይሉኝታና ሕፍረት አሰምቶናል!! ይህ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን፡ ለኤርትራ ህዝብም ንቀት ነው ማለት ይቻላል። በተለይ አሁን አሁንማ፡ አልፎ ተርፎ፡ የኢሳያስንና የህግዲፍን ገመናና ወንጀል በተመለከተ፡ ተጠያቂነቱ ለኤርትራ ህዝብ ለማሸከም ጣቱን የቀሰረ ይመስላል። ለምሳሌ የካቲት 2010 በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ፡ የአርትራን መገንጠል በሚመለከት ተጠይቆ በሰጠው መልስ፡ "ሓላፊነቱን የሚሸከመው የኤርትራ ህዝብ ነው" በሚል አገላለጽ ጀመረ፤ በመቀጠልም "የኢሳያስ እና የሻዕቢያ መበላሸት ተጠያቂው የኤርትራ ህዝብ ነው"[56] ብሏል። የፈረደበት ህዝበ-ኤርትራ! እንዴት ብሎ ነው ለኢሳያስና ለህግዲፍ ብልሽት ተጠያቂ የሚሆነው!! ያ እየተገደለ፡ እየተገፋ፡ እየተራበ፡ እየታሰረና እየተሰደደ

---

ተገቢዉን እርምጃ አልወሰዱም። ከነበሩት አጥቂዎች አብዛኞቹ ኤርትራውያን ስደተኞች እንደነበሩ በመጥቀስ አብርሃ ደስታ እንደሚከተለው ብለዋ። "ከእሁድ በሁዋላ በደረሰን መረጃ መሰረት የድንጋይ ውርወራ ፖለቲካው የተቀነባበረው በህወሓት ጽህፈት ቤት ሁኖ ደብዳቢዎቹም የአዲግራት ተወላጆች ያልሆኑና ከሌላ አካባቢ ተቀጥረው፡ ተከፍለዋቸው የተደራጁ፡ የተሰለፉ ናቸው። አብዛኞቹ ደብዳቢዎች ኤርትራውያን ስደተኞች ነበሩ። ህወሓት ኤርትራውያን ስደተኞችን ተቃዋሚ ፓርቲ ስብሰባዎችን ለመረበሽ ማቀዱም ሰምተናል።" አቶ አብርሃ ደስታ Februry 2, 2014 (G. C.)

56 . ዮናስ በላይ አበበ፣ ገጽ 51

*በአስከፊ ሲቃይ ላይ የሚገኝ ሚስኪን ህዝብ ተጠያቂ ሊሆን! ይኼማ በእንግሊዝኛ ቋንቋ* “victim blaming” - “*ሃያላንን ትተው ግፉአንን መውቀስ*” - *ተብሎ የሚገለጸው ፍርደ-ገምደልነት ነው። አቶ ስብሃት፡ ያላንዳች ሃፍረትና ይሉኝታ፡ እንደ መጣለት ያቀረበው ሸረኛ ወቀሳ ለህዝባችን ቅንጣት ታህል ከበሬታ እንደሌለው የሚያሳይ ነው።*

*ታዲያ*! *የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅቶች እጅጉን ዝቅ አድርጎ ከሚያየንና ከሚንቀን ወያኔ ጋር ዝምድና በማድረጋቸው ምን ጥቅም አገኙ? የኢሳያስ መንግስትን ለመጣል በሚመለከት፡ ያገኙት እገዛ የለም። በአመራር ላይ ያሉት የተወሰኑ ግለሰቦች የሚያገኙት የሆነ ጥቅም ሳይኖር አይቀርም*!! *ሆኖም የዝምድናው ይፋዊ ቁም ነገር የግለ ሰቦችን ጥቅም ለማረጋገጥ ሳይሆን፡ የኤርትራን ህዝብ ከኢሳያስ የጭቆና አገዛዝ ለመገላገል ነው የነበረው። እነዚህ ድርጅቶች ጸረ የኢሳያስ መንግስት በአመርቂነት ለመታገል ከወያኔ የሚያገኙት መተባበር ከሌላቸው፡ ዝምድናው ትርጉም የለውም ማለት ነው። እንዲያውም በኋላ ኋላ፡ በኢትዮጵያ ሁኔታዎች ሲቀያየሩ፡ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ጉዳይ ነው።*

*ተጠያቂነትን ማስከተሉም የግድ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም የነዚህ ድርጅቶች ዝምድና ከወያኔ ጋር እንጂ ከኢትዮጵያ ህዝብ አለመሆኑ ነው። ለምሳሌ ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ውስጠ አዋቂና ለወያኔ ቅርብ የሆነ ኤርትራዊ “መለስ ዜናዊ ለነዚህ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ግንኙነታችሁ ከኢትዮጵያ መንግስት ሳይሆን ከኛ ከህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ጋር ብቻ መሆኑን እንድታውቁ፣ ብሏቸው ነበር” ሲል ሹክ በማለት ገልጾልኛል። አዎ*! *መለስ የተናገረው እውነትነት ነበረው። የድርጅቶቹ ዝምድና ከወያኔ ጋር ነው። ከኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ከሌሎች የኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ጋር ፈጽሞ ዝምድና የላቸውም። ሌላ ቀርቶ ከሌሎች የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ጋር እንኳን ግንኙነት የላቸውም።*

*በአሁኑ ጊዜ የኤርትራ ድርጅቶች ሁኔታ በጣም ውስብስብ እየሆነ መጥቷል። የመወሳሰቡ ዋና ምክንያት ደግሞ፡ አሁን ተቃዋሚዎች ነን የሚሉ የህዝባዊ ግንባር የአመራር አባላትና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት የነበሩ ወደ ተቃውሞ ጎራው ስለተቀላቀሉ ነው።*

## ፱፡ የህዝባዊ ግንባር አባላት በተቃዋሚ ኃይሎች ጎራ

*ወደዚሁ ንኡስ ርእስ ከርሰ ጉዳይ ከመግባቴ በፊት፡ ታጋዮች የነበሩ ሁሉ የነበራቸውን ሚና በሚመለከት ላሰምርበት የምፈልግ አስፈላጊ ነጥብ አለ። አብዛኞቹ በተጋድሎ ሓርነት ኤርትራም ሆነ በህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ በፍላጎታቸው የተሰለፉት ታጋዮች፡ “ሀገራችንንና ህዝባችንን ነጻ ለማውጣት” ከሚል ሕልና እንደነበር እቀበላለሁ። የተሰዉትም፣ የቆሰሉትም፡ አካል ጉዳተኛ የሆኑትም ሁሉ፡ ዕጣው የደረሰባቸው ለሀገርና ለህዝብ ተቆርቋሪነት ባነሳሳው የትግል ተሳታፊነታቸው ስለሆነ፡ ትልቅ ምስጋናና ክብር የሚገባቸው መሆኑን ከልብ አምናለሁ።*

*ይህ መሰረታዊ እምነቴ እንደተጠበቀ ሆኖ፡ አሁን አሁን ከህዝባዊ ግንባር እየወጡ ወደ ተቃውሞው ኃይሎች ጎራ ተቀላቅለው የሚንቀሳቀሱትን የሚመለከት ግን ያለኝን ትዕዝብት እንሆ እደሚከተለው እገልጻለሁ።* <u>*በዚሁ ንኡስ ርእስ የማቀርበው ትእዝብትና*</u>

<u>አስተያየት በመሰረቱ በከፍተኛ አመራር ዙሪያ የነበሩትን ባለስልጣናትንና ሹማምንትን እንጂ፡ ተራ ታጋዮች የነበሩትን የሚመለከት እንዳልሆነ፡ አንባቢዎችና አድማጮች ሁሉ በቅድሚያ እንዲረዱልኝ እማጸናለሁ።</u>

የነዚህ ከህዝባዊ ግንባር ወጥተው በተቃውሞ ጎራ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ሰዎች አመለካከትና አቋም ብዙ ድክመቶችና ችግሮች አሉባቸው። አብዛኛዎቹ ድክመቶቻቸው፡ ከኋላ ታሪካቸውና አመጣጣቸው ጋር የተያያዙ ናቸው። ከነሱ ውስጥ በከፊል የሚከተሉት ናቸው።

1. ብዙዎቹ ያለውን ችግር ሲገልጹ "ችግሩ የተፈጠረው ከነጻነት በኋላ ነው - ማለት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች በኋላ - እንጂ በትጥቅ ትግሉ ዘመን ኢሳያስ ጥሩ ነበረ፡ የህዝባዊ ግንባር አካሄድም ቀናና ገንቢ ነው የነበረው" ይላሉ። ይህ በመሰረቱ ስህተት ነው፤ የወጣለት ውሸት ነው ሊባልም የሚችል ነው። በትግርኛ *"ቆርበት ተባላሽዩ ኣብ ምልፋዓ፣ ኣይ ኣብ ምልፋዓን ኣብ ምጥባሓ"* ማለት፡ "ቆዳው ተበላሸ ሲለፋ፣ አይደለም ሲገፈፍ እንጂ" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አለ። ኢሳያስ አፍወርቂ ገና ከጅምሩ ሲነሳ ነው፡ የኤርትራን ህዝብ ለማጥፋት ያለመ መስመር ይዞ የተጓዘው። ነ ባ ር ታጋይ የማነ ተክለገርግስ እንደገለጸው፡ ኢሳያስ ወደ ትግሉ ሜዳ የገባው ወይም ከጀብሃ የተገነጠለው፡ ለኤርትራ ካለው ፍቅር ወይም ለህዝብ ካለው ተቆርቋሪነት ተነሳስቶና ተገፋፍቶ አይደለም። ዋናውና ትልቁ ውስጣዊ ፍላጎቱ ስልጣን ነው የነበረው። ይህንን የስልጣን ጥማቱን ለማርካትና ለማሟላት ሲል፡ ገና ከጥዋቱ ጀምሮ ብዙ ገመናዎች እየፈጸመ መጥቶ፡ እነሆ ዛሬ ሀገሪትዋን አጠፋት። ከላይ የተጠቀሱት የህዝባዊ ግንባር አባላት የነበሩ ብቻ ሳይሆን፡ ኤርትራውያን ባጠቃላይ ይህንን ሓቅ ሊረዱትና ሊቀበሉት ይገባቿል።

2. ከህዝባዊ ግንባር ተነጥለው ወደ ትግሉ ጎራ በመቀላቀል በእንቅስቃሴ ላይ ካሉት እንዳንዶቹ፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ጨምርው ሲገልጹ፡ "ነጻነትማ አምጥተናት ነበር፤ ኢሳያስ ግን ያመጣናትን ነጻነት እያኰላሻትና እያከሰማት ይገኛል" ይላሉ። በሌላ አነጋገር፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስለተገነጠለች ብቻ ነጻነት ተረጋግጧል እያሉን ነው ማለት ነው። ለነገሩ ይህንን ዓይነት አባባል የሚቀበል ኤርትራዊ፡ በአሁኑ ጊዜ በቁጥርም ቢሆን በጣም እየቀነሰ መጥቷል። ምንም እንኳን ሰፊው ታጋይ ሀገሬንና ህዝቤን ነጻ ለማውጣት በሚል ንጹህ ሕልና የታገለ ቢሆንም፡ አንግቦት የተነሳ አላማና ራእይ ግን ገና አልተረጋገጠም። እንዲያውም በአንጻሩ፡ ህዝቡ ለመገመቱ አዳጋች የሆነ አስከፊ ችግር ላይ ይገኛል። በዚህ ምክንያት፡ ብዙ ተራ ታጋዮች የነበሩት፡ "ያ ሁሉ ትግላችንና መስእዋእትነታችን ብላሽ ሆኖ ቀረ" በማለት ሀዘናቸውን በምሬት እየገለጹ እንደሆነ የሀገራችን ውስጣዊ ሁኔታ በቅርብ የሚከታተሉ ታዛቢዎች ይመሰክራሉ።

3. በአሁኑ ጊዜ፡ ተቃዋሚዎች ነን ከሚሉ አካላት ውስጥ የተወሰኑ በከፍተኛ አመራር ላይ የተቀመጡ ሰዎች - እንዲያውም አንዳንዶቹ በህዝባዊ ግንባር ውስጥ - እንደ ድርጅትም ሆነ እንደ መንግስት - ባለስልጣናት የነበሩ ሲሆን፡ የኢሳያስን ትእዛዝ ተቀባዮች በመሆን ብዙ ወንጀሎች የፈጸሙ ናቸው። እስካሁን ድረስ ግን፡ እነዚህ ሰዎች የፈጸሙትን ወንጀል አምነው ይቅርታ እንኳን አልጠየቁም። አሁን ለዴሞክራና ለፍትሕ መታገል አይችሉም ማለት አይደለም፤ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፡ በትግሉ

ጎራ ተቀላቅለው እንደ ተቃዋሚ ኃይል ተቀባይነት ከማግኘታቸው በፊት፡ ያን ሁሉ ዘመናት ከኢሳያስ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ኤርትራንና ህዝብዋን ሲገድሉ የቆዩ መሆናቸውን በግልጽ አምነው መጸጸት አለባቸው። የፈጸሟቸውን ወንጀሎች በዝርዝር ገልጸው፡ ህዝቡን ከልብ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። ካልሆነ ግን፡ ረዘም ላለ ዓመታት ሲቃወሙትና ሲያጥላሉት የቆዩት የተቃውሞ ጎራ፡ በእርግጠኝነት የህዝብ ወገን መሆናቸውን አምኖ ከልብ ሊቀበላቸው አይችልም። ገመናቸውን ሳያምኑ፣ በሰሩት ወንጀል ሳይጸጸቱና ይቅርታ ሳይጠይቁ፡ እነዚህን ሾላ በድፍን የሚቀበሉዋቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች ካሉ፡ እነሱም ራሳቸው ሀቀኛ ተቃዋሚ ናቸው ለማለት አስቸጋሪ ነው።

4. በትጥቅ ትግሉ ዘመን ኢሳያስ በባለቤትነት የያዘውና የሚቆጣጠረው የህዝባዊ ግንባር ድርጅት በአሜሪካና ሌሎች ጸረ ሶሻሊዝም በሆኑ ምዕራብ መንግስታት፡ በረቀቁ ስልቶች አማካይነት እየታገዘ፡ ከወያኔ ጋር በመሻረክ የኤርትራን ትግል ጠልፎ ለጸረ ህዝብ አላማ እንዲውል አድርጎታል። ዛሬም፡ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ የኢሳያስ ተባባሪዎችና አገልጋዮች የነበሩት፡ አሁን ግን ተቃዋሚዎች ሆነናል የሚሉ ከአንዳንድ ምዕራባውያን መንግስታት ጋር ዝምድና መሳይ ፈጥረው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ብቅ ብቅ እያሉ ይገኛሉ።

ይህ እጅግ አስገራሚ ነገር ነው። በትግርኛ *"ክሰርቀኒ'ዩ ዝረአኽዎስ ክመልሰለይ ነይኣምኖ"* ማለት *"ሲሰርቀኝ ያየሁትን መልሶ ሲሰጠኝም አላምነውም"* የሚል አነጋገር አለ። ከነዚህ ራሳቸውን ከፍ ክፍ አድርገው ወጣ ወጣ ካሉት ተንቀሳቃሽ አካላት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ የተለዩና የታወቁ፡ ግንባር ቀደም የኢሳያስ አገልጋይ ምሁራን ሆነው "ህዝባዊ ግንባር ሶሻሊስት ድርጅት ናት፣ ድርጅታችን ዴሞክራሲያዊት ናት" እያሉ በሐሰት የወደሱ፡ ስንት ምሁራንንና ብርቅዬ ዜጎቻችንን አሳልፈው ለግፍ የሰጡ ናቸው። ከጀብሃ - ተ. ሓ.. ኤ ጋር ስምረት ለማድረግ የሚለውን ሀሳብ በመቃወም ይካሄድ በነበረው ትምክህተኛ ዘመቻ በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው አፍራሽ ሚና የነበራቸው ናቸው። ከ"ነጻነት" በኋላም፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፡ የኢሳያስ አፈ ቀላጤና ወኪሎች በመሆን፡ አረሜናዊ ተግባራቱን ሲከላከሉለት የነበሩ ናቸው። አረ ስንቱ!! በሀገራችን አሁን ያለው ገሃነማዊ ሁኔታ እንዲፈጠር እጅ ነበራቸው ብቻ ሳይሆን ከተከሰተ በኋላም ተቀብለው እንዲጸድቅ አድርገው የነበሩ ናቸው[57]።

---

57. ዶ/ር ኣብርሃም ጳውሎስ፣ ስለ ህዝባዊ ግንባር ምሁራን የጻፈው ሃተታ እነዚህ ቡድኖችንም የሚመለከታቸው ነው። ኣብርሃም እንደሚከተለው ይላል፣

"…… የህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ተከታይ የሆኑት ምሁራን ቀድሞም ቢሆን በሳሕል በረሃ የድርጅታቸው መሪዎች የጀግኖች ታጋዮች ደም ሲጠጡ በነበሩበት ጊዜ ድርጅታችን ሀቀኛና ዴሞክራሲያዊት ናት እያሉ የቆዩ ናቸው። ከነጻነት ኤርትራ በኋላም ቀደም ሲል ከነበራቸው ትምክሕትና ማንአለብኝነት ሳይላቀቁ እንደገና ኢሳያስን ሲወዱሱና ሲያሞጉሱ ይገኛሉ።….. በእነዚህ የሻዕቢያ (ህ . ግ . ሓ . ኤ) ምሁራን አባላት ክሕደትና አድር ባይነት ምክንያትም፡ የእነሱ ለኢሳያስ ወዳሴና ሞጎስ ውጤት በአሁኑ ጊዜ የኤርትራ ህዝብ ለመኮላሸትና ለስደት ተዳርጎ የተናቀ ህዝብ ሆኖ ይገኛል፡፣" ኣብርሃም ጳውሎስ፡ ገጽ 526

እነዚህ አካላት፡ ካሁን በፊት በኤርትራ ህዝብ ላይ በፈጸሙት ገመና በመጸጸት ፈንታ፡ ዛሬ ደግሞ ይባስ ብለው በአንዳንድ አመሪካውያን፣ አውሮጳውያን፣ ወዘተ ታዋቂነት አለን ምንትሴ እያሉ በጎን በጓሮ በኩል በመግባት፡ በኤርትራ ዳግም ለመንገስ ሲንጠራሩ ይታያሉ።

ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ሊገነዘቡት የሚገባ አስፈላጊ የሆነ ነጥብ አለ። ዛሬ፡ አያንዳንዳችን የየራሳችን ታሪክ አለን፤ በየራሳችን ም ግ ባ ረ - ታሪክም ይኸውና በ ግ ል ጽ አ ደ ባ ባ ይ እየተፈረድን እንገኛለን። አመሪካውያን፣ ወይም እንግሊዛውያንም ሆኑ ሌሎች አውሮጳውያን፡ ለኛ ለኤርትራውያን መሪዎች ከውጭ አምጥተው ከላይ በፓራሹት ሊጥሉልን ወይም ሊመርጡልን አይችሉም። የኤርትራ ህዝብ፡ የያንዳንዳችን ታሪክ መርምሮ ሕጋዊ ፍርዱን የሚሰጥበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡ አዎ!! ንጹሃት፣ ብቁና ቅን የሆኑ ልጆቹን በዘንበባ ተቀብሎ ሊሾማቸው ነው። በአንጻሩ ደግሞ ወንጀለኞች የሆኑትን፡ በህዝባዊ ሃያልነቱ በሚገባ ይቀጣቿል። ስንት ወንጀል ከፈጸምክ በኋላ አሁን በመሸ ሰዓት አመሪካውያን፡ አውሮጳውያን ያድኑኛል ብሎ ተስፋ ማድረግ ጊዜው ያለፈበት መወራጨት ነው። ዛሬ ሁኔታዎች እንደተለወጡና ህዝባችንም ከተሞኮረው ብዙ ወጣ ወረድ የተማረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለዚህ፡ እነዚህ ባለፈው ታሪካቸው ከኢሳያስ ጋር ሆነው ህዝባችንን የበደሉ ሁሉ ምዕራባውያን መንግስታትንና አንዳንድ ባለስልጣናትን ሙጡኝ ብሎ ከማጎብደድ ይልቅ፡ ከወገኖቻቸው ጋር በትሕትናና በግልጽ በመግባባት፡ ከህዝባቸው ምሕረት መጠየቅ ይገባቿል። ይህንንና ይህን ሲያደርጉ ብቻ ነው የህዝቡን አሜኔታና ተቀባይነት አግኝተው፣ ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ሆነው፣ ለሀገራችን ኤርትራ ትንሳኤ በሚካሄደው ትግል የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት የሚችሉት።

5. 5ኛ ረድፍ ማደራጀት ኢሳያስ ተ. ሓ. ኤን. - ጀብሃን - ለመሸርሸርና ለማዳከም ከተጠቀመባቸው ስልቶች አንዱ መኖሩን ቀደም ብሎ ተገልጸዋል። ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ፡ የኢሳያስ መንግስት 5ኛ ረድፍን ተጠቅሞ፡ ተቃዋሚ ኃይሎችን እያሰናከለ መሆኑን የሚያሳዩ በቂ ምልክቶች አሉ። በቀላል አነጋገር፡ በተቃዋሚው ኃይሎች ጎራ ውስጥ ሰርገው በመግባት ትግሉ መልክ እንዳይዝና እንዳይጠነክር እንቅፋት በመፍጠርና ጋሬጣ በመሆን ለኢሳያስ መንግስት የሚያገለግሉ ቡድኖች አሉ። የነዚህ ቡድኖች አንዳንድ መሪዎች በኢሳያስ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣኖች የነበሩ ሲሆን አሁን ተቃዋሚዎች ሆነናል የ ሚ ሉ ናቸው። የተወሰኑ ደግሞ፡ ቀደም ሲል ተ. ሓ. ኤ. ውስጥ የነበሩ፡ ነገር ግን ካለፉት በርካታ ዓመታት ጀምረው ከኢሳያስ መንግስት ጋር በስጥ-ለውጥ ወይ በሰጥቶ መቀበል ላይ የተመሰረተ የፓለቲካ ሽፍጥ በመጫወት በጓሮ ለመታረቅ የሚፈልጉ ናቸው።

እነዚህ ከህዝባዊ ግንባር አመራር የመጡና እነዚያ ቀደም ሲል ተ. ሓ. ኤ. የነበሩት ቡድኖች ዛሬ በተቃዋሚ ኃይሎች ውስጥ ሆነው፡ በተግባር የተቃውሞ ሐይሉን የሚያዳክም ፓለቲካ እያራመዱ ይገኛሉ። ብዙዎች እንደሚሉት፡ እነዚህ የ5ኛ ረድፍ ስራ እየፈጸሙ ያሉት ቡደኖች የመጨረሻ ግባቸው ጠቅላላ አመራሩን በእጃቸው ቁጥጥር ስር በማስገባት፡ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ለኢሳያስ እንዲንበረከኩ ለማድረግ ነው። እነሱ የማይመሩትንና የማይቆጣጠሩትን የተቃውሞ ኃይል ስብስብ እንዲኖር አይፈልጉም። ደግነቱ፡ እስካሁን

ድረስ አመራሩን ለመቆጣጠር አልቻሉም። ስለዚህ፡ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የእንቅስቃሴያቸው ቀዳሚ አላማ የተለያዩ ማደናገሪዎችንና ንትርኮችን እየፈጠሩ በተግባር የተቃዋሚ ኃይሎች አንድነት እነዳይሳካ ማድረግ ሆኗል። ቀደም ሲል በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል ተደራጅቶ የነበረው ህብረት ሲፈርስ፡ ቀጥሎ የተቋቋመው ኪዳን ደግሞ ሲዳከም፡ እነዚህ ቡድኖች ትልቅ ሚና ነበራቸው። አሁንም ቢሆን፡ በማንኛውም መልኩ በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል መተባበርና ስምረት እንዳይሳካ፡ የገንዘብ ኃይል በሚያንጸባርቅ አገባብ ሳይታክቱ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

## ፲፡ ኤርትራ ትኑር - አትኑር?

የህይወት አድን ጥያቄ!! በአሁኑ ጊዜ ለኛ ለኤርትራውያን አጋጥሞ ያለ ፈተና መሰረታዊ ነው። ሀገር እየወደመች ነው፣ ሕብረተ-ሰብዋም መንምኖ እየፈረሰና ጨርሶ ደብዛው እየጠፋ ነው። በፊት ለፊታችን ላይ የተደቀነው መሰረታዊና አንገብጋቢ ጥያቄ "ኤርትራ እንደ ሀገር ትኑር ወይስ አትኑር?" የሚለው ነው። ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ሁሉ፡ ለቀረበው የህይወት አድን ጥያቄ አወንታዊ ምላሽ በመስጠት፡ ለኤርትራ ህላዌ ሲል የትግል ድርሻውን እንዲወጣ ይጠበቅበታል።

ለቀጣዩ የኤርትራ ህላዌ እንደ አንድ ጂኦግራፊያዊት አካል አደጋ እየታለመ ያለው በዋናነት የብሄር ብሄረሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚለውን የወያኔ መርህ (ወይም ሰረተ-እምነት) በመሞርኰዝ ነው። ህዝባዊ ወያኔም ሆኑ ታዛዦቻቸው የሆኑት ኤርትራውያን ቡድኖች፡ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን የምትባለውን ከባድ ጽንሰ-ሀሳብ ቀላልና የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት፡ "ከፋፍለህና በታትነህ ግዛ" ለሚለው አላማ መገልገያ አድርገው እየተጠቀሙባት ይገኛሉ። የኤርትራ ብሄሮች ጥያቄንና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጽንሰ-ሀሳብና ትርጉሚን በተመለከተ፡ ካሁን በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች አስተያየቴን ሰጥቼ ነበር። አሁንም፡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ያለኝን ግንዛቤና ድምዳሜ አጠር ባለመልኩ እነሆ ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ።

በእውነቱ የብሄር ብሄረሰቦች ጥያቄ ረጋ ባለ ሁኔታ መግባባት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ካሁን በፊት በተለያዩ ጽሑፎቼ እንደገለጽኩት፡ እኔ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ዴሞክራሲያዊ መብት መሆኑን እቀበላለሁ። ይሁን እንጂ፡ በራስ መወሰን ሲባል አመጣጡ የጭቆና ስርዓትን ለማስወገድ ከሚካሄደው ትግል ጋር የተያያዘ ሆኖ፡ ሁለት መልክ እንዳለው ብዙ ጊዜ የሚረሳ ይመስለኛል። አንዱ ባዕዳዊ ጭቆናን - ማለት external form of national oppression፡ ሁለተኛው ደግሞ ውስጣዊ ጭቆናን - ማለት internal form of national oppression - የሚመለከት ነው። ባዕዳዊ ጭቆና፡ አንድ ሓያል ወይ ኃይል የተሰማው መንግስት ሌላን ህዝብ ወሮ በሚይዝበት ጊዜ፡ የህዝቡ ክብር (status) መገሰሱን ወይም መደፈሩን የሚያመለክት ነው። በራስ የመወሰን ትርጉም መሰረት፡ ክብሩንና ነጻነቱን የተደፈረው ህዝብ፡ ጭቆናውን ለማስወገድ ለታገለና በሚያደርገው ትግልም ሙሉ ድጋፍ ለማግኘት መብት አለው። ውስጣዊ ጭቆና ደግሞ፡ አንድ ህዝብ ውስጣዊ ህይወቱን በሚፈልገው አገባብ ለመምራት ሲከለከል የሚኖረውን ሁኔታ የሚያመላክት ነው። አንድ ህዝብ ራሱ የመረጠውን ፓለቲካዊ ስርዓት፡ ምጣኔ-ሃብታዊ ስርዓት፡ ባህላዊ ፖሊሲ፡ ያስተዳደር ዘይቤ ወዘተ. ከሀገሪቱ ሕገ-መንግስት ጋር፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከአለም-አቀፋዊ ሕግጋት ጋር በተጣጣመ አገባብ፡ ለመተግብር መብት አለው።

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርሕ መሰረት፡ የኤርትራ ብሄር ብሄረሰቦች ውስጣዊ አስተዳደራቸውን፡ በሀገሪቱ የሚደነገገውን ሕገ መንግስት በማይጻረር አገባብ፡ በመረጡት መንገድ ማካሄድ ይችላሉ። ውስጣዊ መብቶቻቸውን መጣስ ወይም መድፈር - ለምሳሌ ባህላቸውን፡ ቋንቋቸውን፡ ም ጣ ነ - ሀ ብ ታ ዊ ስርዓታቸውን፡ ባጠቃላይ ያኗኗራቸው ዘዴን በሚመለከት - በደል መፈጸም፡ ብሄረሰባዊ ጭቆና ነው። ይህንን ዓይነት ጭቆና ለማስወገድ ትግል ማካሄድ መብት አላቸው።

የመገንጠል መብት ስለምትባለው ነገር ግን፡ በተለይም በሶስተኛ ዓለም ሀገሮች፡ ጥንቃቄ የተሞላበት ግንዛቤ ያስፈልጋል። አንድ ብሄር ከመጠን በላይ ከተጨቆነ - ለምሳሌ ህዝቡን ለመጨረስ ወይም በህዝቡ ላይ የዘር ማጥፋት እ ር ም ጃ ሆን ተብሎ የሚወሰድበት ሁኔታ ከተፈጠረ - ህልውናውን ለማረጋገጥ ሲል የሚያደርገው ትግል አግባብነት አለው። ትግሉ እስከ መገንጠል እንዲደርስ ለማድረግ የሚገደድበት ሁኔታም ሊመጣ ይችላል። አለም-አቀፋዊ ማሕበረ-ሰብም ሁኔታውን በመረዳት ሊደግፈው ይችላል። ከዚህ በተረፈ ግን፡ አንድ ብሄር ወይም በብሄሩ ውስጥ የሆነ ቡድን ወይም ቁንጮዎች (ኤሊት)፡ አንዳንድ ሰበብ ፈጥሮ አቧራ በማንሳት ብቻ መገንጠል እንፈልጋለን ቢል፡ አግባብነት የለውም፤ መገንጠልም አይችልም። እንግዲህ! የኛ ኃላፊነት መሆን ያለበት ብሄረ-ሰቦቻችን እንዳይጨቆኑ - ማለት ማንም ብሄር ሌላውን ብሄር ወይም መንግስቱ አንድ የተለየን ብሄር ወይም የተለዩ ብሄሮችን፡ እንደ ብሄሮች እንዳይጮቁን - መጠንቀቅና መከላከል ነው።

እኛ ኤርትራውያን፡ እንደ ሌሎቹ ህዝቦች ሁሉ የተለያዩ የማንነት ደረጃዎች (ወይም እርከኖች) አሉን። በመንደር፡ በወረዳ፡ በአውራጃና በሃገር ደረጃዎች ማንነቶች አሉን። እነዚህ በየደረጃው ያሉን ማንነቶች ግን የተነጣጠሉ አይደሉም። ሶስተኛ ዓለም በመሆኑ በጣም የጠነከረ አይደለም እንጂ፡ ሀገርን መሰረት ያደረገ ፒራሚዳዊ ቅርጽ ያለው እርስ በርሱ የተሳሰረ ማንነት ነው። እንደዚሁም ጐሳዊ ማንነት፡ ብሄረሰባዊ ወይም ብሄራዊ ማንነት፡ ሃይማኖታዊ ማንነት፡ ጾታዊ ማንነት፡ ወዘተ. አሉን። ይህ የተለያየ ዓይነት ማንነት፡ የየራሱ ልዩ የሆኑ ጥቅሞች፣ አስፈላጊነቶችና ጥያቄዎች አሉት። እነዚህ ጥቅሞችና ጥያቄዎች ደግሞ ዴሞክራሲያዊ እስከ ሆኑ ድረስ ሳይገደቡ መሟላት አለባቸው፡ - በተለይም በሰላም ጊዜ።

ይህ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት በሰላም ጊዜ የአኗኗር ህይወትህ በሚጠይቀው ሁኔታ መሰረት፡ ሕግን ሳትጥስ፡ የፈለግከውን የማንነት ደረጃ ማጉላት አግባብነት አለው ማለት ነው። ስትፈልግ መንደርክን፡ ስትፈልግ ወረዳህን፣ ስትፈልግ አወራጃህን፣ - የሌሎቹን ማንነት በማይገፋና በማይቃረን መልክ - ታደምቃለህ። በአጻንሩ፡ በጦርነት ጊዜ ግን፡ ፈተናው (ወይም ግዴታው) በሀገር ደረጃ ነው የሚያጋጥመው፣ ትግሉ የሚካሄደውም በሀገር ደረጃ ነው። እንግዲያውስ፡ ሀገርን ለማዳን የሞት ሽረት ትግል በሚካሄድበት ጊዜ፡ ጎልቶ መታየት ያለበት ማንነትና ስሜት ሀገርን የሚመለከት እንዲሆን ፍጹም አስፈላጊ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ፡ እኛ በሀገር ደረጃ - ማለት ሃገር ጨርሳ እንዳትጠፋ በማለት - እየተጨነቅንና እየታገልን ነን። ይህ ከሆነ ያለው እውነታ፣ ቀዳሚው ጉዳይ ሀገርን ማዳን ሲሆን፡ ከሁሉም በላይ ጎልቶና ደምቆ መታየት ያለበት ማንነት ደግሞ የሀገር ደረጃው ነው። ሌሎች የማንነት መገለጫዎችና ስሜቶች እንደ ብሄር፣ አውራጃ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ የመሳሰሉት ሁሉ በድምቀታቸው ካልአዊ ወይም ሁለተኛ ደረጃ መሆን አለባቸው።

*በዚሁ ጉዳይ ላይ ጠለቅ ብለን ማየትና መረዳት ያለብን ነጥብ አለ። እንዴ!! አሁን እኮ ኤርትራ በእርግጥ ጠላት የሚቆጣጠራት ግዛት* (enemy occupied territory) *ናት። እኛም እንደ ህዝብ፡ እንደ ኤርትራውያን ነው ሁላችንም የችግሩ ሰለባ ሆነን ተጨቁነን ያለነው። እንደ የተለዩ ብሄሮች ወይም እንደ የተለዩ አውራጃዎች ወይም እንደ ሃይማኖታዊ ቡድኖች አይደለም የተጨቆንነው። ሁሉም ብሄሮች፡ ሁሉም አውራጃዎች፡ ሁሉም ሃይማኖታዊ ቡድኖች ተጨቁኗል። አብዛኛው ጊዜ - ወይም ሁሉ ጊዜ ማለት ይቻላል- ብሄራዊ ጭቆና በሚኖርበት ሁኔታ፡ ጨቋኝ ብሄር አለ፣ ተጨቋኝ ብሄር ወይም ተጨቋኝ ብሄሮች አሉ። አሁን፡ ኤርትራ ውስጥ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን፡ ሁላችንም ጭቁኖች ነን። ይህ ብሄር ወይም ያ ብሄር የተለየ ጥቅምና ክብር አለው ብሎ መናገር አይቻልም።*

*እንዲያውም አስከፊ ጭቆናና ዱብ ዕዳ ያለው በሀገር ደረጃ ነው። ሕብረተሰባችን እየመነመነ ነው፤ ሃገራችን እየፈረሰች ናት። ሀገር ስትፈርስ ስትወድምና ጨርሶ ደብዛዋ የሚያጠፉ የጋራ ጠላት ሲኖር፡ ሁላችን እሱዋን እንደ እናት-አገር ቆጥረን ማድመቅና ማዳን አለብን። ያኔ ብቻ ነው በጽናትና በብቃት ልንታገልላት የምንችለው። በሌላ አነጋገር፡ ማንነታዊ ስሜቱ፣ ተቆርቋሪነቱና ፍቅሩ ከነሙሉ መንፈሳዊ ሓይሉ የሀገሪትዋ ድርሻ መሆን አለበት። ትሕተ-ሃገራዊ ማንነት - አውራጃዊም ሆነ ብሄረ-ሰባዊ ማንነት የሀገርን ፍቅር መሻማት የለበትም።*

*የኤርትራ ህላዌ ለሁላችንም እኩል የሚደርሰን ጥቅም ስለሆነ፡ ሁላችን - ልዮነቶች እያሉንም - ለጋራ ሀገራዊ ጥቅም መተባበር አለብን ማለት ነው። ይህ ከሆነ ሀቂና በመሬት ላይ ያለው እውነታ፣ አሁን የሚፈለገው ያደረጃጀት ዓይነት “መላ ህዝበ ግንባር - All People's Front -” ነው። በዚሁ መልክ ተደራጅተን ስንታገል ብቻ ነው የኤርትራን ትንሳኤ ለማረጋገጥ የምንችለው።*

*በአሁኑ ጊዜ፡ ተራራን የሚያህል የጋራ ጠላት ተቀምጦ እያለ በምንም መልኩ በብሄር እንበለው፣ በአውራጃ እንበለው፣ ወይንም በሌላ ዓይነት ትሕተ-ሃገራዊ ደረጃ መደራጀትና መንቀሳቀስ በሃገር ደረጃ ስለሃገር የሚደረገውን ጥረት አደናቅፎ ለጠላት የሚያገለግል ነው። በዚሁ መሰመር እጓዛለሁ የሚል ሁሉ፡ በተግባር፡ የኢሳያስና የወያኔ አካል ነው።*

## *፲፩፡ ትግል ለሀገር ትንሳኤ፤ ተባባሪዎቻችን እነማን ናቸው?*

*ለሀገር ትንሳኤ የሚካሄደው ትግል የሁሉም ሀገራዊ ኃይሎችን አመርቂ ትብብር የሚጠይቅ ነው። ከዚሁ ጋር በተያይዘ፡ በጥልቀት መገንዘብ ያለብን አንድ መሰረታዊ ነጥብ አለ፤ እሱም የሞተች ሀገር ዳግም ትንሳኤዋን ለማረጋገጥ በሚደረገው ትግል ላይ፡ ትልቁን ሚና ሊጫወት የሚችል ኃይል፡ በሀገር ውስጥ የሚደራጀው እንቅስቃሴ መሆኑን ነው። ይህ እንቅስቃሴ በጠላት ጉያ ተሆኖ የሚካሄድ ትግል ስለሆነ፡ ሁኔታው በጣም ከባድና መስዋእትነትን የሚጠይቅ ነው። በአጎራባች ሀገሮችም ሆነ በሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ሀገራውያን ኃይሎች፣ ሀገር ውስጥ ለሚካሄደው እንቅስቃሴ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው በሁሉም መስክ መተባበርና መርዳት አለባቸው።*

ለሀገር ትንሳኤ የሚካሄደው ትግል በመጨረሻ በአሸናፊነት መጠናቀቁ አይቀሬ ቢሆንም፣ በጣም ከባድ ነው። የሃገራዊያን ኃይሎች መተባበር ለብቻው በቂ አይሆንም፤ ከዚያም አልፎ በአለም-አቀፍ ደረጃና በቀጠና ደረጃ የመንግስታትና የንቅናቄዎች ድጋፍ ይጠይቃል። ይህ ትግል ፍትሓዊ ነው። በመሰረቱ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ውስጣዊ ገጽታን ለማረጋገጥ የሚካሄድ ትግል ነው። በመሆኑም፡ ትግሉን የውጭ ኃይሎችም ሞራላዊና ንዋታዊ ድጋፎቻቸውን ቢለግሱለት ሕጋዊ ነው። ይህ ማለት ደግሞ የራስህን ነጻነት ሳይጥሱ፡ እገዛ ለማድረግ ብቃትና ፍላጎት ካላቸው ኃይሎች ጋር ግንኙነት መመስረት ርትዓዊና ጠቃሚ ነው ማለት ነው። በቅርብም ይኑር በሩቅ፡ የሚከተለው ሃይማኖትና የሚናገረው ቋንቋ ማንኛውም ቢሆን፡ ነጻነትህን አክብሮ እገዛ ለማድረግ ዝግጁ እስከሆነ ድረስ ከምስጋና ጋር መቀበሉ አግባብነት ያለው ነው።

ለኤርትራ ህላዌ በምናካሄደው ትግል፣ በቀጠናችን፣ ከልብ የመነጨ ሀቀኛ ድጋፍ ሊያደርጉልን የሚችሉ መንግስታትና ንቅናቄዎች አሉ ወይ? ከኤርትራ ጋር በየብስ በቀጥታ የሚዋሰኑ ኩታ-ገጠም የሆኑ የጎረቤት ሀገሮች ጂቡቲ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ ናቸው። ለነዚህ ሶስት ጎረቤት ሀገሮች መንግስታት ለእኛ ከልብ የመነጨ ድጋፍ ማድረግ ለጥቅማቸውና ለስትራተጂያቸው የሚያገለግል አይደለም።

ጂቡቲ በሞላ ጎደል አውቶኖሚ የሌላት ትንሽ ሀገር ናት። ከወያኔ መንግስት ጋር የጠበቀ ዝምድና ያላት፡ ቀጠናችንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከወያኔ ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም አቋም ለመያዝ የማትችል ተጎታች ነገር ናት።

ሱዳንም፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በሰሜናዊ ምዕራብ ኢትዮጵያ ገደብ የሌለው ለም መሬት ይገባሻል ተብላ፡ አንዳንድ ዘገባዎች እንደሚገልጹት ደግሞ፡ የተወሰነ መሬት ተለግሶላት፡ ለወያኔ መንግስት የምታከብርና የምታመሰግን ሀገር ናት። መሬቱ ለሱዳን የላቀ ስጦታ ወይም ግዙፍ ጉቦ ነው። ይህንን ስጦታ፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን አምርረው እየተቃወሙት ይገኛሉ[58]። በመሆኑም፡ ይህ መሬት የሱዳን ንብረት ነው የሚባለው፡ እስካሁን ድረስ በከፊል በሱዳን እጅ የሚገኘው መሬትም ሊጸና የሚችለው፡ ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ብቻ ነው። ስለዚህ፡ ሱዳን በወያኔ መንግስት ቀጣይነት ዓቢይ ጥቅም አላት። ከዚህ ሸፍጥ በመነሳት፡ ሱዳን የወያኔ በስልጣን ላይ መቆየት ጥቅምዋ ስለሆነ፡ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎች በሱዳን ውስጥ እንዲደራጁና እንዲቀንቀሳቀሱ አትፈቅድም። እንዲሁም ወያኔ የኢሳያስ መንግስት እንዲወገድ የማይፈልግ መሆኑን ስለምታውቅ፡ ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች በሱዳን ውስጥ እንዲኖሩና እንዲንቀሳቀሱ አትፈቅድም።

ወያኔ በሀቅ ሊደግፈን እንደማይፈልግ ቀደም ብሎ ተገልጸዋል። ይህ ነው በቀጠናችን ያለው እውነታ።

አንዳንድ ኤርትራውያን ቃዋሚዎች፡ ከኢትዮጵያ ጨርሶ መውጣት ለትግላችን የሚጠቅም አይሆንም፤ ሌላ ጥቅም ባይሰጠንም፡ በዚያው አካባቢ መኖሩ ለራሱ ጠቃሚ ነው፣ የኤርትራ ተቃውሞ አለ ለማለትም ይጠቅማል ይላሉ። ይህ ምንም ጥቅም የለውም

58 . TheEthiopianBorderAffairsCommittee,LettertoPresidentUmarHassanAhmedAl-Bashir, (Columbus, Ohio,:October20,2011)ርአ

ተብሎ ቢነገራቸው በመጨረሻ ሌላ አማራጭ (alternative) ስለሌለን፡ ከወያኔ ጋር ዝምድናችን ቢቀጥል ጥሩ ነው ይላሉ። ይህ አሳማኝና ውሃ የሚቋጥር ክርክር አይሆንም፣ ተቀባይነት የለውም። በግልጽ ለመናገር፡ የሚከበርም አይደለም። እውነት ነው፡ በአሁኑ ጊዜ እኛን የሚረዳ መንግስት በቀጠናችን የለም። ነገር ግን የሚደግፈን ኃይል ስለሌለ አሁን እንዳለነው ለወያኔ ታዛገሮች ሆነን እንኑር ማለት ስህተት ነው። በወያኔ ስር በመሆን ምንም ውጤታማ የሆነ ስራ ስለማንሰራበት ጨርሶ ፋይዳ የለውም። ስለዚህ፡ በዚሁ ሁኔታ መቀየቱ እንደአማራጭ ሊቆጠርም አይችልም። ለምን? በመሰረቱ አንድ ዝምድና በአሁኑ ጊዜ ለኛ አማራጭ ነው ብለን እንድንወስደው ከሁሉም በፊት የኢሳያስ መንግስትን ከነግሳንግሱ ለመገርሰስ የሚያግዘን መሆን አለበት። ይህን ለማድረግ የማያግዝ ከሆነ ግን አማራጫችን አይደለም። ወያኔ ከቶውንም ሊረዳን አይፈልግም። ስለዚህ አሁን እንዳለነው ከወያኔ ስር ሆነን እንቀጥል ማለት ትግሉን እንተወው፣ እጃችንን እንስጥ ማለት ነው። ነባር ታጋይ ተስፋይ ተምነዎ ይህንን ነጥብ በሚገባ ተገንዝቦ፡ በዋሽንግተን ዲሲ የወጣቶች ስብሰባ ላይ ተገኝቶ እንደሚከተለው ገልጾታል።

> *"የኢትዮጵያ መንግስት የኢሳያስና የቡድኑን ስርዓት የሚቃወም አንድ ጠንካራ ኃይል ያለው የኤርትራ ተቃዋሚ ድርጅት እንዲፈጠር አይፈልግም። ስለዚህ እናንተ ወጣቶቻችን፡ እውነት ኤርትራን ልታድኑዋት ከልብ የምትፈልጉ ከሆነ፡ ከዚሁ ከተገለጸው እውነታ በመነሳት ብቻ ነው ልታድንዋት የሞትችሉ። መፈክራችን "ጉዳያችን!! የኤርትራውያን ጉዳይ በኤርትራውያን" መሆን አለበት።[59]"*

በተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ ካሉት ዐበይትና ተፅዕኖ ፈጣሪ ፖለቲከኞች ይህንን ነጥብ በውል ያልተገነዘቡ ከሆነ፡ ፈጽሞ የፖለቲካ ጭላንጭል የሌላቸው የዋሆች ናቸው ማለት ነው። እኔ እንደሚመስለኝና እንደምታዘበው ግን በአሁኑ ሰዓት ይህ ነጥብ ለሁሉም ግልጽ ነው። ነገሩ ግ ል ጽ እ ያ ለ ከተጠቀሱት ተዋኒያን አማራጭ የለም እያሉ የወያኔ ታዛገሮች በመሆን የሚቀጥሉ ከሆነ፡ በአንዳንድ ትሕተ-ሃገራዊ ቅርጽ በመሳሰሉ መሰሪ አላማ፡ ወይም ደግሞ ብልሹና ጸያፍ በሆኑ ግላዊ ጥቅማ ጥቅሞች ላይ የተሰማሩ ስለሆኑ ብቻ ነው ለሆን የሚችለው።

አማራጭን በሚመለከት ምን ማድረግ ይቻላል? በፖለቲካል ሳይንስ "politics is the art of the possible" ማለት "ፖለቲካ የይቻላል ጥበብ ነው" የሚል አባባል አለ። አባባሉ ቃል በቃል ሲተረጐም፡ ፖለቲካ ሊሆን የሚቻለውን የሚመለከት ብልሃት ነው ማለት ነው። የአባባሉ ይዘት ደግሞ በፖለቲካ ዓለም ገብተህ ስትሰራ አማራጭ መንገዶችን በመዳሰስ የሚቻል የሆነውን ጉዳይ ብልሃት በተሞላበት አኳሃን በማገናዘብ፡ ብቁ በሆነ ስልትና ድንቅ በሆነ ዘዴ ማከናወን የሚለውን ሀሳብ ያመለካክታል። አንዳንድ ተመራማሪዎች ግን "politics is the art of the possible" በማለት ብቻ አያቆሙም፣ "it is also the art of making possible" የሚለውንም ይጨምራሉ። ይህ ፖለቲካ አንድ የሚፈለግ ነገር የሚቻል እንዲሆን የማድረግ ብልሃት ነው ማለት ነው። በቀላል አነጋገር፡ ፖለቲካ ማለት አንድ ጉዳይ አስፈላጊ ነው ተብሎ ከታመነበት፡ በተግባርም የሚቻል እንዲሆን ለማድረግ መላ የመፍጠር ጥበብ ነው ማለት ነው። ወደ ተነሳንበት ነጥብ ልመለስና፡ ጉዳያችንን

59 . ተስፋይ ምነዎ፣ ገጾች 337-338

በሚመለከት፡ በአሁኑ ጊዜ አማራጭ የሌለ እንደሆነ፡ የፖለቲከኞቹ ሃላፊነት ሌላ የፓለቲካ አማራጭ መፍጠር ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፡ ሃላፊነቱ ወይም ፈተናው አዲስ አማራጭ እንዲገኝ ወይም እንዲደራጅ ማድረግ ነው።

እነዚህ ተቃዋሚ ድርጅቶች አሁን አማራጭ የላቸውም። ታዲያ ምን ይደረግ? መደረግ ያለበት እጅ መስጠት ሳይሆን አማራጭ መፍጠር ነው። በተጨባጭ አነጋገር ይህ ምን ማለት ነው? ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ እኛ ከማንም የኤርትራን ሙሉ የግዛት አንድነትና ነጻነት የተቀበለ አካል ጋር ዝምድናና መተጋገዝ መፍጠር መብት አለን። እንደነዚህ ከመሳሰሉት አካላት የሞራል፣ የፓለቲካና ቁሳዊ ድጋፍ መቀበል መብታችን ነው።

ይህን እውን ለማድረግ ከኤርትራ ጋር ለመተጋገዝ ጥቅም ያላቸው - በተለይም ከጎረቤቶቻችን - እነማን ናቸው ብለን መለየት አለብን። ከነዚህ አጎራባች ሀገሮች ውስጥ በኤርትራ ላይ ለህይወት አስፈላጊ የሆነ ጥቅም ያላት ሱዳን አይደለችም፡ ጂቡቲ አይደለችም፡ የመንም አይደለችም። ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ኢትዮጵያ፡ ከኤርትራ ጋር በሁሉም መስክ ለመዛመድ፡ መሰረታዊ የሆኑ ጥቅሞች አሏት። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ብቻ ናት የባሕር በር የሌላት፤ በቀይ ባሕር በኩል የምትዋሰነው ደግሞ ከኤርትራ ጋር ብቻ ነው። ስለዚህ ኤርትራ ለኢትዮጵያ ለ ህ ይ ወ ት አ ስ ፈ ላ ጊ በ ሆ ነ ዓይነትና መጠን ጠ ቃ ሚ ና ት[60]። ይ ህ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለትብብር ዝምድና ጽኑ መሰረት ሊሆን ይችላል።

ይህንን ተከትሎ የሚመጣው ጥያቄ በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛው አካል ነው ለጸረ-ኢሳያስ ትግል ከኤርትራውያን ጋር ሊተባበር የሚችል? የሚለው ነው። ወያኔ እንዳልሆነ አስቀድሞ ተገልጸዋል። ታዲያ እነማን ናቸው? ሆነም ቀረም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ብቻ ናቸው መሆን የሚችሉ።

እነዚህን ኢትዮጵያውያን በ ተ መ ለ ከ ተ ግ ን አንድ ችግር አለ። እሱ ደግሞ፡ ከ ነ ሱ መ ሀ ል ብዙዎች በተለያየ ምክንያት፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠልዋን የማይቀበሉት መሆናቸው ነው። እንዲያውም “ለምንድን ነው እነዚህ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎች የኤርትራን ሙሉ ነጻነትና የግዛት አንድነት የማይቀበሉት?” የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ ከኤርትራውያን ይቀርብልኛል። እውነት ነው! በነዚህ ኢትዮጵያውያን መካከል፡ ጸጸትና ቁጣ የወለደው ግትር አመለካከት ያላቸው አሉ። ከዚህ በተረፈ፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎችም፡ በበኩላቸው ስለ እነዚህ ኤርትራውያን ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚሉት አላቸው። እሱም፡ “ለምንድን ነው እነዚህ ኤርትራውያን ተቃዋሚ ኃይሎች፡ ወያኔ የኢትዮጵያ ህዝብን እየጨቆነ እንደሆነ በዓይናቸው እያዩ የማያምኑና የማያወግዙት? ለምንድን ነው ወያኔን እንደ ዴሞክራሲያዊ መንግስት አድርገው በመቁጠር ጥብቅና የሚቆሙለት?” የሚል ጥያቄ ነው። አግባብ ያለው ጥያቄ ነው።

---

60. ኤርትራም በሁሉ መስክ ከኢትዮጵያ ጋር በመዛመድዋ ለህይወቷ አስፈላጊ የሆኑ ጥቅሞች እንደምታገኝ መታወቅ አለበት። በዚሁ የጽሁፌ ክፍል ኢትዮጵያ በሚኖራት ጥቅም ላይ ያተኮርኩበት ምክንያት፡ በቀጠናችን ከኤርትራ ጋር ተገቢነት ባለው ጥቅም ላይ የተመሰረተ ዝምድና የምትፈልግ አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን ለማሳየት ነው።

*በተጨማሪም እነዚህ ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ተቃዋሚ ቡድኖች የኤርትራውያን ድርጅቶችን እንደ የወያኔ አሽከሮች አድርገው ነው የሚያዩዋቸው። ይህ አመለካከት መሰረት የሌለው አይደለም። እነዚህ የኤርትራ ድርጅቶች የወያኔ አካል ሆነው ነው የሚታዩት፤ ስለዚህም፡ በኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ አሜኔታ የላቸውም። እንግዲያስ ይህ ማለት፡ ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች፡ በኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ አሜነታን ለማግኘትና ከዚያም በኋላ ወደ መተባበር የሚያደርስ ድርድር ለማሳካት ከፈለጉ፡ ከወያኔ ተጽዕኖ ነጻ መሆን ብቻ ሳይሆን ነጻ ሆነውም መታየት አለባቸው ማለት ነው።*

*በአጭሩ፡ በሁለታችንም በኩል መታረምና መስተካከል ያለባቸው አቋሞች አሉ ማለት ነው። በየበኩላችን ያሉንን አቋሞች ለማረም ከልብ እንነሳ። እኛ ኤርትራውያን ለዘላቂ ጥቅማችን ስንል ከወያኔ ነጻ እንሁን፤ ነጻ ህልውና እና ነጻ አቋም ይዘን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለሚደርሰው ግፍ፡ ቢቻል እናውግዘው፡ ካልሆነም ቢያንስ ሽፋን አንፍጠረለት። ይህን ስናደርግ፡ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎች አመለካከታቸውን አርመው የኤርትራ ነጻነትንና ልዓላዊነትን በሚመለከት፡ ርታዓዊና የሚያዋጣ አቋም እንዲይዙ ሊበረታቱ ይችላሉ። በዚሁ አገባብ በኢትዮጵያውያን የተቃውሞ ኃይሎች ዘንድ ያሉትን የኤርትራ “ነጻነት” ያልተቀበሉ አካላት የውይይት መድረክ በመክፈት የኤርትራን ሀቀኛ ነጻነትና፣ የግዛት አንድነት ከልብ እንዲቀበሉ በማድረግ አማራጭ መፍጠር እንችላለን።*

*እውነት ነው፡ ከኢሳያስ መንግስት ጋር ዝምድና ያላቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ቡድኖች አሉ። በአሁኑ ጊዜ እንኳን እንደነዚህ የመሳሰሉት ኢትዮጵያውያን በቁጥር እየቀነሱ መጥቷል። የቀሩ ካሉም ልክ እኛ ከወያኔ ነጻ መሆን እንዳለብን ሁሉ እነሱም ከኢሳያስ ነጻ መሆን አለባቸው።*

*ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ኃይሎች ሲባል ተጋሩንም እንደሚጨምር መገንዘብ ያስፈልጋል። አንዳንድ ተጋሩ የኤርትራን ሁኔታ በሚመለከት በኤርትራውያን ላይ እየደረሱ ያሉትን ተፅዕኖዎችና የተወሳሰቡ ስነ-ልቦናዊ ውጥንቅጦች ለመገንዘብ የሚያስቸግራቸው ያለ ይመስላል። በተጨማሪም፡ በኤርትራ በስልጣን ያለው በኢሳያስ የሚመራው* **ህቡእ** *ቡድን* (cabal)፡ *ዋና ዋና አባላት ትውልደ-ትግራይ መሆናቸው ራሱ ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር እውነታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህ ርእስ ስሜትን የሚያነሳሳ ዓይነት ስለሆነ ጥንቃቄና ኃላፊነት የሚጠይቅ ነው*[61]።

---

61. *ለምሳሌ ዮናስ በላይ አበበ የተባለ ወጣት ደራሲ ይህንን ነጥብ በሚመለከት ትንሽ ችግር ያለው ይመስላል። ዮናስ ስለእኔ የተሳሳተ አመለካከት በመጽሐፉ ላይ አስፍሯል። በ*2012 *ባሳተምኩት ጽሑፍ ላይ የሰፈረቺውን አንዲት ዓረፍተ-ነገር ብቻ በመጥቀስ “ቀድሞ የኢትዮጵያ አንድነት አቀንቃኝ” ነበር ብሎ ዛሬ ግን “የወጣለት አክራሪ ኤርትራዊ ብሄርተኛ” እንደሆንኩ አድርጎ ይገልጻኛል። ዮናስ፣ ገጽ* 201፣ *የግርጌ ጽሑፍ* 168።

*ዮናስ፣ በጽሁፌ ያለውን ዓረፍተ ነገር ይዘትና መንፈስ በትክክል አልተረዳውም። የኔን ጽሑፍ ያነበቡ ኢትዮጵያውያን - እነዚያ አክራሪ ናቸው ተብለው የሚታሙ አማርኛ ቋንቋ የሚናገሩትንም ጨምሮ - “የወጣለት አክራሪ ኤርትራዊ ብሄርተኛ” አላሉኝም። እንዲያውም በአንጻሩ ጽሑፌን ገንቢና የሚያቀራርብ ብለው እንደአደነቁትና እንደተቀበሉት ለወንድሜ ዮናስ በላይ አበበ ደስ እያለኝ ልገልጽለት እፈልጋለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ!! በተለይም ሀቀኛ የኢትዮያዊነት መንፈስ ያላቸው*

*የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከት ተጋሩ ሶስት ዓይነት ሆነው ይታዩኛል። አንደኛው በነስብሃት ነጋ የሚወከለው የወያኔ ክፍል ነው። ይህ ክፍል የብሄሮች መብት እስከ መገንጠል የምትለዋን ጽንሰ-ሀሳብ ከፋፋይና በታኝ ዕቅዱን ለማራመድ እንደ መሳሪያ አድርጎ ለመጠቀም ታጥቆ የተነሳ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውና ከተቻለው፡ ኤርትራን በማፈረካከስ፡ ሃገረ-ትግራይ-ትግርኚን ለመመስረት ሕልምና ምኞት ያለው ነው። ካልሆነለት ደግሞ፡ ኤርትራን በምንም መንገድ የትግራይ ጥገኛ (ማለት "ጓሮ") በማድረግ፡ ለወያኔ የምታገለግል ደካማ ሀገር ሆና እንድትቀር የሚፈልግ ነው።*

*ሁለተኛው ዓይነት ተጋሩ ደግሞ፡ ያልተበረዘ ኢትዮጵያዊ ስሜትና እምነት ያላቸው ናቸው። በነዚህ ዓይነት ተጋሩ መካከልም፡ ልክ እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን፡ የኤርትራን ነጻነት የማይቀበሉ አሉ። ከነዚህ ዓይነት ተጋሩ ጋር፡ ሳ ይ ታ ክ ት ህ በግልጽ መነጋገርና መረዳዳት ያስፈልጋል። ከነዚህና ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር፡ የኤርትራ ሉዓላዊነትና ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡ በሰለጠነ የውይይት ሂደት መረዳዳት ያስፈልገናል።*

*ሶስተኛ ዓይነት ተጋሩ የምላቸው ደግሞ፡ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ስሜትና እምነት ያላቸው ሲሆኑ፡ የኤርትራን ነጻነትና የግዛት አንድነት የሚቀበሉ፡ ዴሞክራስያዊ ስርዓት በኤርትራ እንዲተከል የሚደግፉ፣ በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል በሂደት ጥልቅት እያገኘ የሚሄድ ፓለቲካዊና ሌሎች አጠቃላይ ዝምድናዎችን ማድረግ አስፈላጊና የሚቻል መሆኑን የሚያምኑ ናቸው። እነዚህ ተጋሩ፡ የትግል አጋሮቻችን ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ስለሆነም በቅድሚያ ዋል እደር ሳይባል የምንመሰርተው የትግል ዝምድና ከነዚህ ዓይነት ተጋሩና ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ሌሎች ኢትዮያውያን ጋር ይሆናል።*

*ይህ ነው ትክክለኛና ተግባራዊ ሊሆን፡ የሚችለው የትግል ዘዴ - አማራጭ የሌለው የህይወት መንገድ ለዚያች ለሞተቺው ሀገር!!*

*ይሁን እንጂ፡ ኤርትራን የገደሉ ኢሳያስና ወያኔ፡ አሁንም ለትንሳኤዋ የሚደረገውን ጥረት ለማኮላሸት ሲባል፡ እንደተለመደው የተቻላቸውን ሁሉ ለማደረግ ወደኋላ እንደማይሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ወገኖቼ! የኤርትራን የነገ ዕድል በሚመለከት እኮ፡ ኢሳያስና ወያኔ አንድ አምሳል፡ አንድ አካል ናቸው!! ውስጣዊ አንድነታቸው እምብዛም የጠበቀና ህይወት ያለው በመሆኑ፡ "ጨደር" - ማለት፡* ***ተጣብቀው የተወለዱ ምንትዬዎች*** *- የሚል ቃል በሚገባ ይገልጻቿል[62]። በሌላ አነጋገር፡ የኢሳያስና የወያኔ ዝምድና በለጋ ዕድሜያችን ገና የሰፈር ልጆች እያለን የምንዝናናበት የነበረ የ"ክናና እና ምናና" ተረት ያስታውሰኛል። ክናና እና ምናና ጨደር ወይም የተጣበቁ ምንትዬዎች ነበሩ። አንድ ቀን ምናና ሞተ። ክናና የምንትዬውን የምናናን የጠነባ አስካሬን ተሸክሞ ሲጓዝ፡ በመጨረሻ የአስካሬኑ መጥፎ ሽታ አሳብዶት ገደል ገብቶ ሞተ። አበቃለት።*

---

*የጽሑፌ አንባቢዎች እኔን "የወጣለት አክራሪ ኤርትራዊ ብሄርተኛ" ብለው ሊጠሩኝ አይችሉም። በአሁን ጊዜ፡ የኢትዮጵያና የኤርትራ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ በአፍሪቃ ቀንድ ሀገሮች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ያለኝን አመለካከትና ራዕይ ምን መሆኑን በውል እያወቁ፡ "የወጣለት አክራሪ ኤርትራዊ ብሄርተኛ" እንዲሉኝ የወሰኑ ሰዎች ካሉ፡ የ"ትግራይ-ትግርኚ" አራማጆች ወይም ደጋፊዎች ብቻ ነው ሊሆኑ የሚችሉ።*

62 . *ተጣብቀው የተወለዱ ምንተዬዎች በእንግሊዝኛ* Siamese twins *ይባላሉ።*

**የኢሳያስና የወያኔ የመጨረሻ ዕድልም ልክ እንደ "ክናና እና ምናና" ነው። ማናቸው ነው ክናና፡ ማናቸው ነው ደግሞ ምናና የምናውቀው አንዳቸው ከወደቁ በኋላ ነው።**

# ዋቢ ምንጮች


**አብርሃ ደስታ፣** (Abraha Desta): *የድንጋይ ውርወራ ፖለቲካ በዓዲግራት፣* (Sunday, 2 February 2014), http://tinurabys.blogspot.de/2014/02/by-abraha-desta.html#more

**አብርሃም ጳውሎስ፡** *ዓደይ ዓዲ ጅጋኑ፣ እንበዓል መንየም ሕድሪ ስዉኣት ዝጠለሙ* (ካስል ፣ ጀርመን 2014)

**ኤርምያስ ለገሰ፤** *የመለስ "ትሩፋቶች" ፣ ባለቤት አልባ ከተማ* (www.npabooks.com: **ነጻነት አሳታሚ ድርጅት፡** 2014 - /2006 E. C./ )

**ገብሩ አስራት፤** *ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ* (USA: www.sbpbooks.com, 2014 - /2006 E. C./)

*መረራ ጉዲና፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፣* (አዲስ አበባ፤ 2ኛ ዕትም፡ 2006 E. C.)

*ተስፋይ ተምነዎ፣ ንኣርብዓ ዓመታት ዝተኞብረ ጉድ! 1972-2013፣ 2ይ ሕታም (ሴክ፡ Germany, 02፣ 2014)*

**ማሕበር ሰላምን ሕውነትን ስድራቤታት ትግርኛን ተጻወብቲ ብሄራትን፣** *"መልእኽቲ ንኹሎም ጉዱኣት ሰላም፣ ዓንዲ ሕጊ"* (2010)

**የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ፡** *"የሱዳን ጦር የወረራ ዘመቻውን እያጠናከረ ነው ፣ የወያኔ ድብቅ ሴራ እየተጋለጠ ነው "፡፡* **ግንቦት** 1 2000 **ዓ. ም.**

**ዮናስ በላይ አበበ፤** *የትግራይ ህዝብ፣ ወያኔዎቹና ሸፍቶቹ* (አዲሰ አበባ፣ 2006 ኣ፡ ግ)

Andebrhan Welde Giorgis, *Eritrea at a Crossroads: A Narrative of Triumph, Betrayal and Hope,* (Strategic Book Publishing and Rights Co.: Feb. 2014) (http://sbprabooks.com/AndebrhanWeldeGiorgis/

Aregawi Berhe, *A Political History of Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, Ideology, and Mobilisation in Ethiopia,* (Los Angeles: Tsehai Publishers, 2009)

Herman J. 'Hank' Cohen, "Time to bring Eritrea in from the Cold", http://africanarguments.org/2013/12/16/time-to-bring-eritrea-in-from-the-cold-by-hank-cohen/

Dan Connel, *Conversations with Eritrean Political Prisoners* (Lawrenceville, N.J. ; The Red Sea Press, 2005)

Richard Dowden, "How Meles Zenawi rules Ethiopia", May 21, 2012, African arguments, http://africanarguments.org

Hank Edmondson, "Aristotle on Monarchy: Power, Politics & Tolkien", *http://www.hank-edmondson.com/tolkien/aristotle-on-monarchy.html*

The Ethiopian Border Affairs Committee, *Letter to President Umar Hassan Ahmad Al-Bshire*, (Columbus, Ohio, October 20, 2011).

Ermias Legesse: "EPRDF methods to eliminate opponents ahead of elections", http://www.ethiomedia.com/15store/4247.html, (ethiomedia.com. November 6, 2014)

Merera Gudina "Electoral Authoritarianism and Democratic Governance in Ethiopia", in Mafela, Lily & Herman Musahara (eds.) (2011) ***Setting of New Social Science Research Agendas for Africa in the 21st Century.*** Addis Ababa: OSSREA.

Rod Hague & Martin Harrop, *Comparative Government and Politics: An Introduction (5th Edition) (New York: Palgrave 2011)*

(Diana Hsieh, "Ayn Rand on Dictatorship and Aristotle on Tyranny", www.philosophyinaction, August 30 2014).

*Indian Ocean Newsletter*, No. 1211, March 31, 2007, "A Confidential TPLF Document"

*Indian Ocean Newsletter*, No. 1211, June 28, 2013, "Call for unity between Ethiopian Tigrayans and Eritreans".

René Lefort, "Ethiopia: a Leadership in disarray", opendemocracy.net , 4 July, 2014 *https://www.opendemocracy.net/ren%C3%A9-lefort/ethiopia-leadership-in-disarray*

Vittorio Longhi, "Hidden Oppression in Eritrea", *The New York Times* (OP-ED), Oct. 3, 2014 (online).

Mesay Kebede, "Disengaging from the False Dilemma of Armed or Peaceful Struggle", *satenaw.com* (August 27th, 2014)

Martin Plaut, "Eritrea: Back to the Dark Ages", ethiomedia.com (November 17, 2014)

Martin Plaut, "Conversation with resistance movement from Asmara", October 25, 2014 http://www.zehabesha.com/conversation-with-resistance-movement-from-asmara

Salman Mohamed Ahmed Salman, Halayb and Fashagah between Nile Water Hammer and Renaissance Dam Anvil (1-2)," *Sudan Vision*, Issue No. 3373, 23rd October, 2014

Roger Scruton, *A Dictionary of Political Thought* (London and Basingstoke: Macmillan reference Books, 1982)

David Shinn, "Time to bring Eritrea in from the Cold (But It's Harder than it Sounds) ", http://africanarguments.org/2014/01/13/time-to-bring-eritrea-in-from-the-cold-but-its-harder-than-it-sounds-by-david-shinn/

**Transparency International, http://www.transparency.org/cpi2013/results/**

TPDM (**ዲምህት**)፣ **ዕላማ**፣ www.tpdm.org - AIM

*Copyright © 2014 by Tesfatsion Medhanie.*
*መሰል ደራሲ© 2014 ተስፋጽዮን መድሃኔ*